*የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት*

*ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ*

# *የ2018 በጀት ዓመት*

# *የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅድ*

*ህዳር 2018 ዓ.ም*

*ባህርዳር*

ማውጫ ገጽ

I. መግቢያ ---------- 2

ክፍል አንድ

የነባራዊ ሁኔታ ትንተና እና የዕቅዱ መነሻዎች

1. የነባራዊ ሁኔታ ትንተና ---------- 3
1.1. ክልላዊ ወቅታዊ ሁኔታ ---------- 3
1.2. የክልሉ ከተሞች አጠቃላይ ሁኔታ ---------- 4
1.3. የተቋማዊ አቅም ሁኔታ ---------- 6
1.3.1. የተቋሙ መዋቅራዊ አደረጃጀት ሁኔታ ---------- 6
1.3.2. የተቋሙ አሰራር እና የህግ ማዕቀፎች ሁኔታ ---------- 6
1.3.3. የተቋሙ አመራርና ባለሙያ ሁኔታ ---------- 7
1.4. የተገልጋይና የባለድርሻ አካላት ሁኔታ ---------- 9
1.4.1. የከተማ ነዋሪው ህዝብ ሁኔታ ---------- 9
1.4.2. የከተማው ወጣት ሁኔታ ---------- 9
1.4.3. የግል ባለሀብቱ ሁኔታ ---------- 10
1.4.4. በከተማ ፅዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት የተሰማሩ ማህበራት ---------- 11
1.4.5. ሌሎች ባለድርሻ አካላት ---------- 11
1.5. የልማት አቅሞች ሁኔታ ዳሰሳ ---------- 11
1.5.1. ሰብዓዊ ሀብት ---------- 12
1.5.2. የመሬት ሀብት ---------- 12
1.5.3. የውሃ ሀብት ---------- 12
1.5.4. ታዳሽ ሀይል ---------- 13
1.5.5. ቴክኖሎጅ ---------- 13
1.5.6. ፋይናንስ ---------- 13
2. የዕቅዱ መነሻዎች ---------- 13
2.1. የተቋሙ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም እንደ መነሻ ---------- 13
2.1.1. ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች አፈፃፀም ---------- 13
2.1.2. የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ስራዎች ---------- 14
2.1.3. የህግ እና የአሰራር ማሻሻያ ስራዎች ---------- 16
2.1.4. ተቋማዊ አሰራርን ማዘመን (E- Service) ---------- 17
2.1.5. የተለያዩ የልማትና መልካም አስተዳደር ኢኒሸቲቮች አፈፃፀም ---------- 17
2.1.6. የአበይት ተግባራት እቅድ አፈፃፀም ---------- 18
2.1.6.1. የከተሞች መልካም አስተዳደር አቅም ግንባታ ስራዎች ---------- 18
2.1.6.2. የቤቶች ልማትና አስተዳደር ስራዎች ---------- 20
2.1.6.3. የከተማ መሰረተ- ልማት ስራዎች ---------- 21
2.1.6.4. የከተሞች ጽዳት፣ አረንጓዴ ልማትና ውበት ሥራዎች ---------- 23
2.1.6.5. የከተማ ሴፍቲ ኔትና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ስራዎች ---------- 25
2.1.6.6. የባለብዙ ዘርፍ ስራዎች አፈፃፀም ---------- 26
2.1.6.7. የስራ እድል ፈጠራ ስራዎች ---------- 26

2.1.6.8. ማደማደሚያ ---------- 26
2.2. የክልሉ የ25 ዓመት ፍኖተ ካርታና የ5 ዓመት የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ እንደ መነሻ ---------- 26
2.3. የተቋሙ የ5 ዓመት (2018-2022) የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ እንደ መነሻ ---------- 28
3. የተቋሙ ርዕይ፣ ተልኮ፣ ዕሴት እና ስልጣንና ተግባር ---------- 29
4. የእቅዱ ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች፣ የትኩረት መስኮችና የትኩረት አቅጣጫዎች ---------- 30
4.1. ስትራቴጅያዊ ጉዳዮች ---------- 30
4.2. የእቅዱ የትኩረት መስኮች ---------- 30
4.3. የእቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች ---------- 30

ክፍል ሁለት

ዓላማዎች፣ ግቦች የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት እና ማስፈፀሚያ ስልቶች

2.1 የእቅዱ ዓላማ፣ ግቦችና የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ---------- 30

ክፍል ሶስት

የማስፈፀሚያ ስልቶች፣ ስጋቶች እና እሳቤዎች

3.1 ማስፈፀሚያ ስልቶች ---------- 36
3.2 ስጋቶችና ታሳቢዎች ---------- 37
3.2.1 ስጋቶች ---------- 37
3.2.2 ታሳቢዎች ---------- 37

ክፍል አራት

የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት

4.1 የእቅድ አፈፃፀም ክትትል ስርዓት ---------- 38
4.1.1 መደበኛ የአፈፃፀም ሪፖርት ልውውጥ ማከናወን ---------- 38
4.1.2 የመስክ ክትትልና ድጋፍ ማከናወን ---------- 38
4.1.3 የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ እና ግብረ-መልስ ስርዓት ---------- 39
4.1.3.1 የአፈፃፀም ምዘናና ግብረ-መልስ ማከናወን ---------- 39
4.1.3.2 መደበኛ የአፈፃፀም ግምገማ መድረክ (የሴክተር ጉባኤ) ማካሄድ ---------- 39
4.2 ማጠቃለያ ---------- 39
4.3 የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ ድርጊት መርሃ ግብር ---------- 52

## I. መግቢያ

ከተሞች የዓለማችን ግማሽ ሕዝብ የሚኖርባቸው እና የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ማዕከላት ናቸው፡፡ የሰው ልጅ የማህበራዊ ሕይወቱንና ኑሮውን ለማሻሻል ከተሞችን እንደ ዋና የመኖሪያና የመስሪያ ማዕከልነት የመጠቀም እና የመከተም ፍላጎቱ በከፍተኛ ሁኔታ አድጓል፡፡ ይህም ፈጣን የከትመት ሂደት ከማንኛውም ጊዜ በላይ በከተሞች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት እና አገልግሎቶች አቅርቦት ላይ ከፍተኛ ጫና እየፈጠረ ይገኛል፡፡

የከተማ ልማት ስራ በባህሪው ውስብስብና ባለብዙ ዘርፍ የልማት ስራዎችን ያካተተ ከመሆኑም በላይ መሬት ላይ የሚያርፉ ማንኛውንም ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ መሰረተ ልማቶችንና አገልግሎቶችን እንዲሁም የከተማ-ከተማ እና የከተማ-ገጠር ትስስርንና

ተመጋጋቢነትን አቀናጅቶ መምራት የሚጠይቅ ተግባር ነው፡፡ የምንመራው የአብክመ ከተማና መሰረተ-ልማት ቢሮም በከተሞች ጉዳይ ላይ ቁልፍ ሚና ያለውና ከተሞች የመጭው ዘመን የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ለውጥ ሞተርና ማዕከል እንዲሆኑ እንዲሁም ውብ፣ ጽዱና ለኑሮ ተስማሚ እንዲሆኑ በማድረግ ለክልላችን ብሎም ለአገራችን ብልፅግና ወሳኝ የሆኑ ተግባራት የሚከናወኑበት ነው፡፡

በመሆኑም ቢሮው የክልሉ ከተሞች ዘመናዊ የመሬት አስተዳደር ስርዓት የተከተሉ፣ በፕላን የሚመሩ፣ መሰረተ ልማት የተስፋፋባቸው፣ ውብና ፅዱ፣ የልማትና የአገልግሎት ማዕከል እንዲሆኑ በማድረግ የዜጎችን ተጠቃሚነት ማረጋገጥን እንደ ተልዕኮ ይዞ ባለፉት ዓመታት ባከናወናቸው ተግባራት በርካታ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት በክልላችን በየአካባቢው አዳዲስ ከተሞች መፈጠር፣ ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት እና የነባር ከተሞች ወደ ጎን መስፋት ከተፈጥሮዓዊው የህዝብ ዕድገት ጋር ተዳምሮ የከተሞች ህዝብ ብዛት ከሚጠበቀው በላይ በፍጥነት የጨመረበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይህን ተከትሎም በከተሞች የአገልግሎት አሰጣጡ ተደራሽ እና አርኪ ያልሆነበት፣ ሌብነት በስፋት የሚስተዋልበት፣ የመኖሪያ ቤት እና የመሰረተ ልማት ፍላጎት በእጅጉ የጨመረበት እንዲሁም ሥራ አጥነት እና የከተማ ድህነት የተስፋፋበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ በተለይም በከተሞች የሚታየውን ሌብነት መታገል እና በአገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን መፍታት ልዩ ትኩረት የሚሻው ጉዳይ ነው፡፡

በመሆኑም እነዚህንና ሌሎች በከተሞች የሚስተዋሉ ውስብስብ ችግሮችን በዘላቂነት ለመፍታት ከተቋሙ የ5 ዓመት (2018-2022) መሪ የልማትና መልካም አስተዳደር እቅድ የተቀዳ የ2018 በጀት ዓመት እቅድ የተዘጋጀ ሲሆን በዘርፉ የተቀረፁ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጅዎችንና ፕሮግራሞችን እንዲሁም የስማርት ከተማ ግንባታ ፅንሰ-ሀሳብን መሰረት በማድረግ የተቋሙ አገልግሎት አሰጣጥ የሚሻሻልበትን፤ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች የቤት ባለቤት የሚሆኑበትን፣ በከተሞች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ-ልማቶች የሚስፋፉበትን እንዲሁም ውብ፣ ፅዱና ለኑሮ ተስማሚ የሚሆኑበትን፤ ዜጎች የምግብ ዋስትና እና የስራ እድል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን...ወዘተ ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ ያደረጉ አላማዎች፣ ግቦችና ግቦችን ለማሳካት የሚከናወኑ ተግባራት ታቅደዋል፡፡

## ክፍል አንድ

## የነባራዊ ሁኔታ ትንተና እና የዕቅዱ መነሻዎች

### 1. የነባራዊ ሁኔታ ትንተና

### 1.1. ክልላዊ ወቅታዊ ሁኔታ

እንደ ፕላንና ልማት ቢሮ 2016 ዓ.ም መረጃ የአማራ ክልል በ8º 40' እስከ 14º 50' ሰሜን የኬክሮስ እና በ35º 10' እስከ 40º 20' ምሥራቅ የኬንትሮስ መስመር ውስጥ የሚገኝ ሲሆን የቆዳ ስፋቱ 181,190.16 ካሬ ኪ.ሜ. ወይም 18,119,015.68 ሄክታር ሲሆን በ14 ዞኖች፣ በ8 ሪጅኦፖሊታንት ከተሞች፣ በ77 ከተማ አስተዳደሮች፣ በ153 የገጠር ወረዳ አስተዳደሮች፣ በ3,540 የገጠር ቀበሌ አስተዳደሮች እና በ618 የከተማ ቀበሌ አስተዳደሮች በድምሩ በ4,158 ቀበሌ አስተዳደሮች የተከፋፈለ ነው፡፡ የሚያዋስኑትም በምስራቅ የአፋር ክልል፣ በምዕራብ ሱዳንና ቤንሻንጉል ክልል፣ በሰሜን ትግራይ እና ኤርትራ እንዲሁም በደቡብ የኦሮሚያ ክልል ናቸው፡፡

ክልሉ የአማራ፤ የአገው፤ የአርጎባ፣ የኦሮሞና የሌሎች ብሔረሰቦች በጋራ የሚኖሩበት ሲሆን እንደ ማዕከላዊ ስታስቲክስ ባለስልጣን የክልሉ ህዝብ ብዛት በ1999፣ 2004፣ 2009 እና 2014 ዓ.ም በቅደም ተከተል 17,624,985፣ 19,220,678፣ 21,136,526 እና 22,877,365 መሆኑ ታውቋል። እንደ ፕላንና ልማት ቢሮ በ1999 ዓ.ም የተካሄደውን የህዝብና ቤቶች ቆጠራ መነሻ በማድረግ በተሰራው ትንበያ መሰረት በ2016 ዓ.ም የአማራ ክልል ህዝብ ብዛት 23,548,998 (11,725,424 ወንድ እና 11,823,575 ሴት) እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይሁን እንጅ እንደ UN-Habitat, 2023 ጥናት በክልሉ ከሚገኙ ወረዳ አስተዳደሮች የተሰበሰበው የህዝብ ብዛት መረጃ 30,302,723 ሲሆን በማዕከላዊ ስታስቲክስ ባለስልጣን ከተጠናው በ7,425,358 ከፍ ያለ ነው።

የክልሉ አጠቃላይ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ሲታይ ወቅታዊ የፖለቲካ አለመረጋጋትና የፀጥታ ችግር የሚታይበት ቢሆንም በክልሉ ከፍተኛ የሆነ ወደ ሥራ ሊሰማራ የሚችል የሰው ኃይል፣ ለእርሻና ለእንስሳት እርባታ ተስማሚ የሆነ መሬት፣ የአየር ንብረት፣ የማዕድን ሀብት፣ የቱሪዝም መስቦች እና የውሀ ሀብቶች ያሉት ክልል መሆኑ፤ የክልሉ ህዝብ የመልማት እና የመከተም ፍላጎት እያደገ

መምጣቱ እና ከተሞች የክልሉ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ለውጥ ሞተርና መዳረሻ ማዕከል መሆናቸው እንደ መልካም አጋጣሚ የሚታዩ ናቸው፡፡

እነዚህ ከዚህ በላይ ያሉ መልካም አጋጣሚዎች ያሉ ቢሆንም አሁንም የድህነት ምጣኔው ከፍተኛ መሆኑ እና በተለይም የወጣት ስራ አጥነት ሁኔታ አሳሳቢ መሆኑ እንዲሁም የክልሉ ሰሜን ምስራቅ አካባቢ ዝናብ አጠር ከመሆኑ ጋር ተያይዞም ስር የሰደደ የምግብ ዋስትና ችግር መኖሩ የክልሉ ፈተናዎች ሆነው ቀጥለዋል፡፡ በክልሉ 87 ወረዳዎች የምግብ ዋስትናቸውን ያላረጋገጡ እና በርካታ የህብረተሰብ ክፍሎች በአስከፊ ድህነትና ስር በሰደደ የምግብ ዋስትና ማጣት ችግር ውስጥ እንደሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በመሆኑም የክልሉን ወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታ የመልማት አቅም እና የህዝቡን የኑሮ ደረጃ በጥልቀት በመገንዘን ክልሉን ለረጅም ጊዜ ቀፍድዶ ከያዘው የድህነት እና የግጭት አዙሪት በታቀደና በተደራጀ አግባብ ሁሉን አካታች የልማትና መልካም አስተዳደር እቅድ በማዘጋጀትና በጥብቅ ዲሲፕሊን ተግባራዊ በማድረግ የብልፅግና ጉዞውን ማፋጠን የሚገባ ይሆናል፡፡

## 1.2. የክልሉ ከተሞች አጠቃላይ ሁኔታ

“ከተማ” ማለት ማዘጋጃ ቤት የተቋቋመበት ወይም የህዝብ ቁጥሩ 2,000 እና ከዚያ በላይ የሆነና ከዚህም ውስጥ ቢያንስ 50 በመቶ የሚሆነው ከግብርና ውጭ በሆነ የስራ መስክ የተሰማራ ህዝብ የሚኖርበት ነው፡፡ ይህም ትርጉም ከ1944 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ከተማ ለመሆን እንደመስፈርት ይወሰድ የነበረ ሲሆን የህዝብ ቁጥራቸው ባይሞላም የወረዳ ማዕከላትም እንደ ከተማ እንዲቆጠሩ ሲደረግ ቆይቷል፡፡ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የከተሞች እንደገና ማቋቋሚያ፣ ማደራጃና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 245 /2009 ዓ.ም መሰረት “ከተማ” ማለት 2,000 እና ከዚያ በላይ የሆነ ህዝብ በአንድ ላይ ተሰባስቦ የሚኖርበትና የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት በሚያወጣቸው መመዘኛዎች መሠረት ክልሉ “ከተማ” ብሎ የሚሰይመው ማናቸውም አካባቢ እንደሆነ ተቀምጧል፡፡

በዚህ መስፈርት መሰረትም ባለፉት ሁለት አሥርት ዓመታት ብቻ የኢትዮጵያ ከተሞች ቁጥር ከ980 ወደ 2,550 እንዲሁም የክልላችን ከተሞች ቁጥር ከ193 ወደ 729 ያደገ ሲሆን በአሁኑ ሰዓት በክልላችን 8 ሪጂዮ-ፖሊታን ከተሞች፣ 11 መካከለኛ ከተማ አስተዳደሮች፣ 66 አነስተኛ ከተማ አስተዳደሮች፣ 149 መ/ማዘጋጃ ከተሞች፣ 104 ን/ማዘጋጃ ከተሞች፣ 391 ታዳጊ ከተሞች በድምሩ 729 ከተሞች ይገኛሉ፡፡

### ሰንጠረዥ 1፡- የከተሞች ቁጥር በፈርጅ ደረጃቸው

| ተ.ቁ | ዞን/ከተማ | ከተማ አስተዳደር | | | | ፈርጅ 3 /መሪ ማዘጋጃ/ ቤት/ | ፈርጅ 4 /ንዑስ ማዘጋጃ ቤት/ | ፈርጅ 5 /ታዳጊ ከተማ/ | ጠቅላላ የከተሞች ብዛት | የከተማ ቀበሌ ብዛት | የወረዳ ብዛት | ፕላን ያላቸው ከተሞች | ፕላን የሌላቸው ከተሞች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሪጂዮ ፖሊታን | ክ/ከተማ | ፈርጅ 1 | ፈርጅ 2 | | | | | | | | |
| 1 | ባህርዳር | 1 | 6 | | | 2 | 1 | | 4 | 26 | | 4 | |
| 2 | ጐንደር | 1 | 6 | | | | | | 1 | 25 | | 1 | |
| 3 | ደሴ | 1 | 5 | | | | | | 1 | 18 | | 1 | |
| 4 | ደ/ማርቆስ | 1 | 4 | | | | | | 1 | 14 | | 1 | |
| 5 | ደ/ብርሃን | 1 | 5 | | | | 1 | 1 | 3 | 24 | | 3 | |
| 6 | ኮምቦልቻ | 1 | 4 | | | | | | 1 | 14 | | 1 | |
| 7 | ደ/ታቦር | 1 | 3 | | | | | | 1 | 9 | | 1 | |
| 8 | ወልዲያ | 1 | 3 | | | | | | 1 | 6 | | 1 | |
| 9 | ሰ/ወሎ | | | 2 | 5 | 13 | 7 | 38 | 65 | 37 | 13 | 63 | 2 |
| 10 | ሰ/ሸዋ | | | | 9 | 20 | 9 | 31 | 69 | 54 | 22 | 68 | 1 |
| 11 | ደ/ጎንደር | | | | 7 | 13 | 10 | 36 | 66 | 51 | 13 | 66 | |
| 12 | ሰ/ጎንደር | | | 2 | 1 | 6 | | 22 | 31 | 17 | 8 | 25 | 6 |
| 13 | ማዕ/ጐንደር | | | | 4 | 20 | 10 | 32 | 66 | 40 | 15 | 66 | |
| 14 | ምዕ/ጐንደር | | | 1 | 2 | 5 | 6 | 10 | 24 | 14 | 4 | 23 | 1 |
| 15 | ደ/ወሎ | | | | 9 | 19 | 17 | 53 | 98 | 56 | 20 | 98 | |
| 16 | ሰ/ጎጃም | | | | 3 | 8 | 5 | 19 | 35 | 22 | 7 | 35 | |
| 17 | ምዕ/ጐጃም | | | 1 | 4 | 9 | 5 | 28 | 47 | 28 | 7 | 46 | 1 |
| 18 | ምስ/ጐጃም | | | | 8 | 12 | 10 | 46 | 76 | 68 | 17 | 76 | |

| ተ.ቁ | ዞን/ከተማ | ከተማ አስተዳደር | | | | ፈርጅ 3 /መሪ ማዘጋጃ/ ቤት/ | ፈርጅ 4 /ንዑስ ማዘጋጃ ቤት/ | ፈርጅ 5 /ታዳጊ ከተማ/ | ጠቅላላ የከተሞች ብዛት | የከተማ ቀበሌ ብዛት | የወረዳ ብዛት | ፕላን ያላቸው ከተሞች | ፕላን የሌላቸው ከተሞች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ሪጂዮ ፖሊታን | ክ/ከተማ | ፈርጅ 1 | ፈርጅ 2 | | | | | | | | |
| 19 | ዋግኽምራ | | | 2 | 1 | 6 | 4 | 15 | 28 | 22 | 9 | 26 | 2 |
| 20 | ኦሮሞ | | | 1 | 3 | 3 | 5 | 15 | 27 | 17 | 5 | 27 | |
| 21 | አዊ | | | 1 | 6 | 7 | 8 | 37 | 59 | 35 | 9 | 57 | 2 |
| 22 | ወ/ጠ/ሴ/ሁመራ | | | 1 | 4 | 6 | 6 | 7 | 24 | 24 | 4 | 11 | 13 |
| ጠቅላላ ድምር | | 8 | 36 | 11 | 66 | 149 | 104 | 390 | 728 | 621 | 153 | 700 | 28 |
| | | **85** | | | | | | | | | | | |

ከተማን ከተማ ከሚያስብሉ ምክንያቶች ውስጥ ዋነኛው የተሟላ የከተማ ፕላን መኖር ነው፡፡ ከዚህም አኳያ በክልላችን ከሚገኙ 728 ከተሞች ውስጥ 700 (96.15%) የሚሆኑት በፕላን የሚመሩ ሲሆን 28 (3.85%) የሚሆኑት የተሟላ ፕላን የሌላቸው በመሆናቸው በእቅድ ላይ ተመስርቶ በተሟላ የከተማ ፕላን መምራት ያስፈልጋል፡፡

በክልላችን የከተሞች ህዝብ ብዛት እና የክትመት ምጣኔውም በፍጥነት እያደገ የመጣበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ እንደ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ መረጃ በተለያዩ ሳቢ እና ገፊ ምክንያቶች የክልሉ የከተማ ነዋሪ ሕዝብ ምጣኔ በ1991 ዓ.ም ከነበረበት 8.3 በመቶ በ2013 ዓ.ም 19.6 በመቶ ደርሷል። የተቋሙ አስተዳደራዊ መረጃ እንደሚያሳየው ደግሞ በክልላችን በሚገኙ 729 ከተሞች የሚኖረው ህዝብ ብዛት 7,606,326 ሲሆን ከጠቅላላ የክልሉ ህዝብ 32.3 በመቶ ይሸፍናል፡፡ አመታዊ የክትመት እድገት ምጣኔውም በአለም እጅግ ፈጣን የሚባል 5.4 በመቶ ነው፡፡ ለዚህ የከተሜነት ዕድገት ምጣኔ ፈጣን መሆን ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት እና የከተሞች ተፈጥሯዊ የሕዝብ ዕድገት ዋነኛ ምክንያቶች ሲሆኑ የገጠር ማዕከላት ወደ ከተማነት መሸጋገር፣ የከተማ ወደ ጎን መስፋፋት እንዲሁም አዳዲስ የልማት ፕሮጀክቶችን ተከትሎ የሚኖር የሕዝብ ዕድገት በቅደም ተከተል አስተዋጽዖ አድርገዋል።

ከተሜነት አይቀሬ እና የሥልጣኔ ምልክት ቢሆንም ዕድልም ሥጋትም ይዞ የሚመጣ አለም አቀፋዊ ክስተት ነው። ዓለም ባንክ እ.ኢ.አ መስከረም 2017 "opportunities and challenges of urbanization planning for un precedents future" በሚል ሪፖርቱ ከተሞች ቁልፍ የእድገት ሞተሮች መሆናቸው ቢታወቅም የከተማ ኗሪዎች ቁጥር መጨመር ተስፋም ስጋትም እንዳለው አስቀምጧል፡፡

ይህ ፈጣን የከተሞች መስፋፋትና እድገት ዘመናዊ በሆነ መንገድ ከተሞች ያላቸውን ጸጋ መሰረት ባደረገ ስትራትጂክ እቅድ ከተመራ የስራ ዕድል የተስፋፋባቸው፣ የተሻሻለና ተደራሽ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መሰረተ ልማቶችና አገልግሎቶች ያሏቸው፣ ለነዋሪዎቻቸው ምቹና ማራኪ የሆኑ፣ ከግብርናውና ከኢንዱስትሪው ጋር ተመጋጋቢ የሆነ ጤናማ እድገት ያላቸው ተወዳዳሪ ከተሞችን መገንባት ይቻላል። በአንፃሩ ደግሞ በአግባቡ ካልተመራ ድህነት፣ ስራ አጥነት፣ የመኖሪያ ቤት እጥረት፣ የመሰረተ ልማትና አገልግሎት አቅርቦት ችግር፣ የአካባቢ ብክለት፣ የትራንስፖርት እጥረትና የትራፊክ መጨናነቅ፣ የደህንነት ስጋት እንዲሁም ሌሎች ተዛማጅ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች የከተሞች ስጋት ይሆናሉ፡፡ ለአብነትም በአሁኑ ሰዓት በከተሞች ስር የሰደደ ድህነት (Poverty) እና ስራ አጥነት (Unemployment) ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የመጣበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡

ምንም እንኳን ባለፉት 20 አመታት በተሰሩ ስራዎች በክልላችን የከተማ ድህነትን በ1997 ዓ.ም ከነበረበት 37.8% 2008 ዓ.ም ወደ 11.6% ዝቅ እንዲል ወይም በ26.2% እንዲቀንስ የተደረገ ቢሆንም ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በነበረው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ፣ የክልሉ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት፣ የዋጋ ንረት እና አልፎ አልፎ በሚከሰት ድርቅ ወዘተ ምክንያት የከተማ ድህነት መልሶ የመባባስ ሁኔታ እያሳየ ይገኛል፡፡ በከተሞች ከሚኖረው ከአንድ አራተኛ በላይ የሚሆነው ሕዝብ ከአጠቃላይ የድህነት ወለል በታች የሚኖር እና መሠረታዊ ፍላጎቶችን የመግዛት አቅም ውስንነት ያለበት ነው፡፡ የክልላችን የከተማ ስራ አጥነት ምጣኔም በ2005 ዓ.ም ከነበረበት 13.9% በ2013 ዓ.ም ከአገር አቀፉ የሥራ አጥነት ምጣኔ እኩል ወደ 17.9 በመቶ አሻቅቧል። በተለይም ዕድሜያቸው ከ15 - 29 ዓመት የሆኑ ወጣቶች የሥራ አጥነት ምጣኔ በ2013 ዓ.ም በክልሉ 23.6 በመቶ የነበረ ሲሆን ይህም ከአገር አቀፉ 17.9 በመቶ የወጣት ሥራ አጥነት ምጣኔ በላይ ነው።

ሌላው የክልላችን የዋጋ ግሽበት (Inflation) ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቶ በ2008 ዓ.ም ከነበረበት 10.3% በ2015 ዓ.ም ወደ 33.1% የደረሰ ሲሆን ይህም አሃዝ ከአገር አቀፉ ጭማሬ (ከ9.6% ወደ 32.5%) በላይ ነው፡፡ ይህን የዋጋ ግሽበት ለመቆጣጠር በመንግስት በኩል እየተወሰደ ያለው እርምጃም ከችግሩ ስፋትና ውስብስብነት አንጻር በቂ አይደለም፡፡ ሕብረተሰቡንና ባለድርሻ አካላትን በተቀናጀ መልኩ በማሳተፍ በኩልም ከፍተኛ ክፍተት ይታይበታል፡፡ እንደ ክልል በከተሞች የሚስተዋለውን ድህነትና ስራ አጥነት ለመቀነስ በተለያዩ አካላት እየተደረገ ያለው እንቅስቃሴም የተቀናጀና በችግሩ ስፋት ልክ አይደለም፡፡ ከተሞች የተረጋጋ እና ዘላቂ የኢኮኖሚ መሰረት ከሌላቸው ደግሞ አንዳንድ የኢኮኖሚ፣ የማህበራዊና የፖለቲካ ችግሮች በተፈጠሩ ቁጥር የነዋሪው ተጋላጭነት ይጨምራል፡፡ ይህም በሀገራችንና በክልላችን በተለያየ ጊዜ እያጋጠመን ያለ ችግር ነው፡፡

ስለሆነም የከተሞችን መስፋፋት ጤናማ ለማድረግ በኢኮኖሚ ዕድገት፣ በነዋሪዎች የኑሮ መሻሻል እንዲሁም በድህነት እና ስራ አጥነት ቅነሳ ላይ የተመሰረተ እቅድ በማዘጋጀት የከተሞችን ሁለንተናዊ እድገት በጥብቅ ዲሲፕሊን መምራት ያስፈልጋል፡፡

## 1.3. የተቋማዊ አቅም ሁኔታ

### 1.3.1. የተቋሙ መዋቅራዊ አደረጃጀት ሁኔታ

በዚህ ወቅት እየተመዘገበ ያለውን ፈጣን የከተሜነት እድገት የሚመራው ተቋም የአብክመ ከተማና መሰረተ ልማት ቢሮ በ12 ዳይሬክቶሬቶች (5 ዓላማ ፈፃሚ እና 7 ድጋፍ ሰጭ)፣ በ22 መምሪያዎች (14 ዞን እና 8 ሪጅዮፖሊታን ከተሞች)፣ በ128 ወረዳ ጽ/ቤቶች እንዲደራጅ ተደርጓል፡፡

ይህ ተቋም አሁን ባለው አደረጃጀት እንኳን ከሚያስፈልገው የሰው ኃይል ውስጥ 40 በመቶ የሚሆነውን ይዞ በክልሉ የሚገኙ ከተሞች ግብርናው የሚፈጥረውን የመከተም እድል የሚስቡና የሚሸከሙ፣ መሰረተ-ልማት የተስፋፋባቸው፣ ውብና ፅዱ፣ የልማትና የአገልግሎት ማዕከል እንዲሆኑ፣ የመኖሪያ ቤት ፋላጊዎች የቤት ባለቤት እንዲሆኑ፣ የከተማ ድህነት ቅነሳ እና የስራ እድል ፈጠራ በማስፋፋት የዜጎችን ዘላቂ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጅ ከአደረጃጀት አንፃር ባለፉት ዓመታት ተቋሙ በርካታ ግዙፍ ተግባራትን የተሸከመ በመሆኑ ሊታለፉ የማይገባቸው የተደራሽነትና የውጤታማነት ችግሮች እንዳሉበት በመገምገም ክፍተቶችን ለመሙላት በርካታ ስራዎች የተሰሩ ቢሆንም የተቋሙ መዋቅራዊ አደረጃጀት አሁንም ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ እያደገ እና እየሰፋ የመጣውን ተግባርና ኃላፊነት እንዲሁም ህብረተሰቡ የሚጠይቀውን የአግልግሎት ፍላጎት ሊሸከም የማይችል፣ የተፈጠሩ አደረጃጀቶች በሰው ኃይል አለመሟላታቸው እና ጤናማ የሰው ኃይል ስምሪት (በዘርፉ ተገቢው እውቀት፣ ክህሎት፣ ልምድና ብቃት ያለው የሰው ሀይል) አለመኖሩ፣ ከJEG ፍረጃ ጋር ተያይዞ የስራ መደቦች ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑ እና የሰራተኛ ጥቅማጥቅም አለመሟላት፣...ወዘተ ችግሮች በስፋት የሚስተዋሉ ናቸው፡፡

በመሆኑም ተቋሙ የሚጠበቅበትን ተግባርና ኃላፊነት በጥራትና በብቃት መወጣት እንዲችል በጥናት ላይ የተመሰረተ የመዋቅራዊ አደረጃጀት ማስተካከያ ማድረግ ይኖርበታል፡፡ ከተሞችም ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም ተቋማዊ አደረጃጀት በመፍጠር እና የሚያስፈልጋቸውን የሰው ኃይል በዓይነትም በመጠንም በማሳደግ ውጤታማ የሚያደርጋቸውን የሥራ ስምሪት እንዲፈፅሙ ማድረግ ይጠይቃል፡፡

### 1.3.2. የተቋሙ አሰራር እና የህግ ማዕቀፎች ሁኔታ

ከአሰራር ጋር ተያይዞ የሚታየው ዋናው ጉዳይ ተቋሙ የሚመራባቸው የህግ ማዕቀፎች አግባብነትና ችግር ፈችነት ነው፡፡ ከዚህም አኳያ የነበሩ ችግሮችን በመፍታት የዘርፉን ሥራዎች ለማሳለጥ አጋዥ የሆኑ እና ግልጽነትና ተጠያቂነትን የሚያሰፍኑ ዝርዝር የሕግ ማዕቀፎች (አዋጆች፣ ደንቦች፣ የአፈጻጸም መመሪያዎች) እና ማንዋሎች ተዘጋጅተውና ተሻሽለው ሥራ ላይ እንዲውሉ የተደረጉና ሊያሰሩ የሚችሉ የህግ ማዕቀፎች ያሉ ቢሆንም ተቋሙ የሚመራባቸው አንዳንድ መመሪያዎች የህግ ክፍተት ያለባቸው፣ አግባብነትና ችግር ፈችነት የጎደላቸው፣ ቢሮክራሲ ማራዘም የተጠናወታቸው እና ከወቅቱ ጋር የማይሄዱ በመሆናቸው እያደገ የመጣውን የህዝብ የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄ የማይመልሱ ናቸው፡፡

በመሆኑም በተቋሙ ተዘጋጅተው በወረዱ የአሰራር መመሪያዎች ላይ የክፍተት ትንተና እና የፋይዳ ግምገማ ጥናቶችን በማድረግ እንዲሁም የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ እንዲሻሻሉ እና አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ የህግ ማዕቀፎችም እንዲዘጋጁ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በተቋሙ የሚታየውን ብልሹ አሰራርና ሌብነት ለመታገል እንዲሁም ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋይ እርካታን ለማሳደግ ተቋማዊ አሰራሮችን ማሻሻልና ማዘመን አስፈላጊ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ በልማትና መልካም አስተዳደር ስራዎች ላይ

ህብረተሰቡን በማሳተፍ እና የሚያስከትለውን ሁለንተናዊ አደጋ በውል ተገንዝቦ በዘርፉ ከላይ እስከታችኛው መዋቅር ድረስ ምንጮችን በመለየትና ወደ ሌብነት ተግባር የገቡ አመራሮችንም ሆነ ባለሙያዎችን ታግሎ በማስተካከል ችግሩን ለመቀነስ የሚደረገው ጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቷል፡፡

የቤት መረጃ አደረጃጀትና አስተዳደር ሶፍትዌር በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ለምቶ አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን እስከ አሁን በዞኖችና ከተሞች 22,350 በላይ የመንግስት ቤቶችን ወደ ዘመናዊ የቤት መረጃ ስርዓት (system software) ማስገባት ተችሏል፡፡ ይሁን እንጅ ቴክኖሎጅው በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል እና የቴክኖሎጅ መሰረተ ልማቶችን ለማሟላትና system software ለማልማት ከፍተኛ የፋይናንስ ወጪ የሚጠይቅ መሆኑ፣ እንዲሁም በግል የጥቅም ፍላጎት እና በእውቀት/ግንዛቤ ማነስ ምክንያት በአመራሩና በባለሙያው ዘንድ ቴክኖሎጅን ያለመቀበል እና በዘልማዳዊ አሠራር የመቀጠል ፍላጎት ከወዲሁ በስፋት ይስተዋላል፡፡

ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱ ተግዳሮቶችን በመሻገር የከተማ ልማት ስራን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ እንዲታገዝ ከማድረግ አኳያ የሚሰጡ አገልግሎቶች ከዘልማዳዊ አሠራር ወጥተው ወደ ዲጂታል አሠራር (ወረቀት አልባ አሰራር) ማሸጋገር ያስፈልጋል፡፡ የከተማ ነዋሪዎች የቤተሰብ ሁኔታና አድራሻ፣ የከተሞች የመሬት እና የቤቶች ይዞታ እንዲሁም ሌሎች ወሳኝ የከተማ ነክ መረጃዎች በአይቲ መደገፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም በላይ መረጃዎችም በኔትዎርክ አማካኝነት በአስተዳደር ደረጃዎች እና በተቋማት መካከል ሊተሳሰሩ ይገባል፡፡

**ከክትትል፣ ድጋፍና አፈፃፀም ግምገማ ስርዓት አኳያ፡-** በየበጀት ዓመቱም በርካታ የግንዛቤ መፍጠሪያ የህዝብ ንቅናቄ መድረኮችና ተከታታይነት ያላቸው የአፈፃፀም ግምገማ መድረኮች እና ኩነቶች የተከናወኑ ሲሆን በልማትና መልካም አስተዳደር ስራዎች ላይ የተሻለ አፈፃፀም ላስመዘገቡ ተቋማት፣ ከተሞችና ባለሙያዎችም እውቅና የመስጠት ስራዎች ሲከናወኑ ቆይተዋል፡፡

ይሁን እንጅ የጠራ ግልፅነትና ተጠያቂነት የሚያረጋግጥ አሰራር በመከተል በኩል ክፍተቶች ነበሩ በተለይም የተገልጋይን እርካታ በጥናት በማረጋገጥ እና የማስተካከያ ርምጃ በመውሰድ፣ በዘርፉ ውጤታማ የሆኑ ተሞክሮዎችን በመቀመርና በማስፋት በኩል ሰፊ ክፍተቶች ነበሩ፡፡ ሌላው በየደረጃው የተከናወኑ የአፈፃፀም ግምገማ ሂደቶች በአብዛኛው በተደራጀ መንገድ ከውጤት (outcome) ጋር በማስተሳሰር የተፈፀሙ ሳይሆን ከጥቃቅን ተግባራትና ሂደቶች (processes) ጋር ብቻ የማዛመድ ዝንባሌ የሚታይባቸው ነበሩ፡፡ ይህን ተከትሎ የሚሰጡ ግብረ-መልሶችም ለቀጣይ የሚኖራቸውን ፋይዳ በውል ተገንዝቦ ወደ ዕቅድ እየለወጡና እያካተቱ በመሄድና ከዚህም ትምህርት በመውሰድ በኩል ክፍተቶች ነበሩ፡፡

ከዚህም አኳያ በተለያዩ አስቻይና ፈታኝ ሁኔታዎች ውስጥ በማለፍ የሚፈለገውን የእቅድ አፈፃፀም ውጤት ለማስመዝገብ ውጤታማ የክትትል፣ የድጋፍና የግምገማ ስርዓት በመዘርጋት በጥብቅ ዲሲፕሊን መፈፀም ዋናው ቁልፍ ማስፈፀሚያ ስልት ተደርጎ መወሰድ ይገበዋል፡፡

በአጠቃላይ ተቋማዊ የመፈጸምና የማስፈጸም አቅማችንን ከመገንባት አንጻር ጥሩ ጅምሮች ቢኖሩንም በአፋጣኝ መፈታት ያለባቸው እና ያልተሻገርናቸው በርካታ ማነቆዎች እንዳሉም መገንዘብ ተችሏል፡፡ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን የመፍታትና በተገልጋዩ በኩል ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ፈጣን ምላሽ የመስጠት አቅም በሚፈለገው ደረጃ አልደረሰም፡፡ ተገልጋዮችንም በእኛ ላይ ሙሉ እርካታና አመኔታ አልፈጠረም፡፡ አሁንም የዘርፉ አገልግሎት አሰጣጥ ዋና የመልካም አስተዳደር ችግር ምንጭ ሁኖ ቀጥሏል፡፡ ከአገልግሎት አሰጣጥ ጋር በተያያዘ በከተሞች የሚታየውን ሌብነት ለማረም ሰፊ ጥረት ቢደረግም አሁን ካለው ተጨባጭ እውነት (ወቅታዊ ሁኔታ) አንፃር ችግሩን ተሻግረናል ማለት አይቻልም፡፡

## 1.3.3. የተቋሙ አመራርና ባለሙያ ሁኔታ

ወቅታዊ ሁኔታው ለአመራሩም ሆነ ለባለሙያው የማይመች ቢሆንም በየደረጃው ያለው አመራርና ባለሙያ ችግሩን ተቋቁሞ ተግባሩን ለመፈፀም የሚያደርገው ጥረት አበረታች መሆኑ፤ ለአብነትም አመራሩ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታውን ተገንዝቦ ለመምራት፣ ተግባሩን ለማወቅ እና ለመገንዘብ እንዲሁም የህዝብ አመኔታ ለመገንባት የሚያደርገው ጥረት አበረታች መሆኑ፤ በተጨማሪም የተመደበውን አነስተኛ በጀት በህዝብ ተሳትፎ እና በቁጠባ ተጠቅሞ ለውጥ ለማምጣት የሚያደርገው ጥረት አበረታች መሆኑ፤ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመናበብና በመነጋገር ችግሮችን እየፈቱ እያረሙ በመሄድ በኩል ይስተዋል የነበረው የቅንጅታዊ አሰራር መሰረታዊ ችግር እየተቀረፈ መምጣቱ…ወዘተ በጥንካሬ የሚታዩ ናቸው፡፡

ይሁን እንጅ በመሆኑም ባለፉት ዓመታት የዘርፉን ልዩ ባህሪ ተገንዝቦ ስትራቴጅካዊ አመራር መስጠት የሚችል የከተማ አመራር ለመፍጠር እና በዘርፉ የተሰማራውን ፈፃሚ በአመለካከት፣ በእውቀትና በክህሎት ለማብቃት በዘርፉ በተለያየ ጊዜ በወጡ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጅዎች እና ሌሎች የህግ ማዕቀፎች ላይ በየደረጃው ሰፋፊ ስልጠናዎች በዙር የተሰጡ ቢሆንም የከተማ ልማት

ስትራቴጅና ፖሊሲን ተገንዝቦና ተረድቶ እንዲሁም በዘርፉ ልምድና እውቀት አዳብሮ በመምራት በኩል የአቅም ውስንነት ያለበት መሆኑ፤ በተቋምና በህዝብ መካከል ያለን ትስስር አጠናክሮ በመምራት በኩል ውስንነት መኖሩ፤ ተግባራትን ለፈፃሚ ቆጥሮ ሰጥቶ ቆጥሮ በመቀበል፣ በማረምና በማብቃት በኩል ውስንነት መኖሩ፤ ከሙስና ፀድቶ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን ተቆጣጥሮ በማረም እረገድ ጅምሮች ቢኖሩም አሁንም ሰፊ ጉድለት የሚስተዋልበት መሆኑ፤ የሚገነቡ የመሰረተ ልማት ኘሮጀክቶችን ከቅድመ ዝግጅት እስከ ፍፃሜው በወቅቱ ጀምሮ በወቅቱ በመጨረስ በኩል /የፕሮጀክት አመራርና አስተዳደር/ ችግር ያለበት መሆኑ…ወዘተ በአመራሩ በኩል በድክመት የሚታዩና በቀጣይ ትኩረት ሰጥተን ልናርማቸው የሚገቡ ጉድለቶች ናቸው፡፡

ሌላው ከአመራር ስምሪት ጋር ተያይዞ መታየት ያለበት ጉዳይ በከተማ ደረጃ የሚመደቡ አመራሮች እና ፈፃሚዎች ተረጋግተው እና ለችግሮች ዘላቂ መፍትሔ አስቀምጠው የሚፈፅሙበት ምቹ ሁኔታም በሚፈለገው ደረጃ ተፈጥሯል ማለት አይቻልም፡፡ በርካታ አመራሮች ያለሙያቸው ተመድበው ወደ ስራ ከመግባታቸው በተጨማሪ በፍጥነት በመቀያየራቸው ምክንያት ስራዎች መሰረት ይዘው እየተከናወኑ አይደለም፡፡ በሌላ መልኩ ይህ የአመራር መቀያየር ለሌቦችና ለደላሎች ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ከዚህም ትምህርት እየተወሰደ አይደለም፡፡ በየደረጃው ያለው ከተማ አመራር ለከተማ ም/ቤቶችና ለነዋሪው ተጠያቂ የሚሆንበትም ሥርዓትም የተጠናከረ አይደለም፡፡

ከባለሙያው አኳያ በአብዛኛው የሚሰራው ስራ እና የሚከፈለው ክፍያ የሚመጣጠን ባለመሆኑ በውስጡ ቅሬታ ቢኖረውም ተግባሩን አክብሮ የሚሰራ እና ለውጤት የሚታትር በርካታ ሰራተኛ ያለ መሆኑ፤ የተገልጋዩን ዘለፋና ወቀሳ ተቋቁሞ ችግር ለመፍታት ደፋ ቀና የሚል ሰራተኛ ያለ መሆኑ፤ በብልሹ አሰራር እና በሙስና የሚጨማለቁ ሰራተኞችን የሚያወግዝ፣ የሚያርም እና ራሱን ከብልሹ አሰራር ያፀዳ ቀላል የማይባል ሰራተኛ መኖሩ…ወዘተ በጥንካሬ የሚወሰድ ነው፡፡ ሌላው አዳዲስ የለውጥ ጽንሰ-ሃሳቦችን በዕምነት በመቀበልና የአሠራር መሣሪያዎች አድርጎ በመጠቀም፣ በዘርፉ ስራዎችና እንቅስቃሴዎች አዎንታዊና ይመለከተኛል የሚል አስተሳሰብ በመፍጠር፣ ለተቋም ከማይጠቅሙ ልማዳዊ አሠራሮች በመላቀቅ ተግባርና ኃላፊነትን በእውቀት ላይ ተመስርቶ በመፈፀም እንዲሁም ስራዎችን ከተጀመሪያ አስከመጨረሻ /end to end/ ድረስ ተናብቦ በመስራት በኩል መሻሻሎች ታይተዋል፡፡

ይሁን እንጅ በየደረጃው በተመደበበት ሙያ እና ስራ ብቁ ያልሆነ እና በእውቀቱና በአመለካከቱም ብቃት የሚጉድለው በቅርበት መደገፍ ያለበት ሰራተኛ ቀላል ግምት የሚሰጠው አለመሆኑ፤ አዳዲስ አሰራር እና ዘመናዊ ቴክኖሎጅ የማይጠቀምና ከተማን የሚመጥን ዝግጅት የሚጉድለው ሰራተኛ መኖሩ፤ የወቅቱን ሁኔታ የተገነዘበ አገር ፈተና ላይ መሆኗን የተረዳና ለመፍትሔው የሚጨነቅ የበኩሌን ላበርክት ብሎ የሚሰራ ሰራተኛ ያለውን ያህል በሶሻል ሚዲያ ተጠምዶ የተሰጠውን ተልዕኮ የማይወጣ ጥቅሙን ብቻ የሚያሳድድ ሰራተኛ መኖሩ፤ ሁሉም ነገር ያለ መንግስት በጀት አይሰራም ብሎ የሚያምን (የህዝብን አቅም መጠቀም ላይ በአመለካከት የማይቀበል) እና የህዝብ ተሳትፎን በማረጋገጥና በቅርብ ያሉ ከተሞችን ደግፎ ለማብቃት ዝግጁ ያልሆነ ሰራተኛ መኖሩ…ወዘተ ከባለሙያው አኳያ የሚታዩ ድክመቶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በየደረጃው ያለው አመራር በዘርፉ የተጀመረውን ለውጥ ከማስቀጠል አንጻር ሰፊ የአመለካከት፣ የክህሎት እና የአቅም ክፍተቶች ያሉበት ሲሆን ይህ ክፍተት የዕቅድና የአፈጻጸም ሪፖርት ዝግጅት፣ የአፈጻጸም ክትትል፣ ድጋፍ እና ግምገማ እንዲሁም በዚህ ላይ ተመስርተው የሚሰጡ ግብረ-መልሶች በሚጠበቀው ደረጃ፣ ጥራትና ጊዜ እንዳይከናወኑ ምክንያት ሆኗል፡፡ ዕቅድን በብቃት ለመፈፀም የሚያስችሉ የፖሊሲ ሃሳቦችን ከማመንጨት ጀምሮ ልዩ ልዩ አዋጆችንና ደንቦችን በመቅረፅ እና አውቆ በመተግበር /በማስተግበር በኩል በርካታው አመራር ክፍተት ይታይበታል፡፡ ፈፃሚውም የህዝብ አገልጋይነት ስሜት ተላብሶ በኃላፊነት የያዛቸውን ተግባራት ሳያንጠባጥብ በጊዜ ያለማከናወን፣ በሥራ አፈጻጸም ሂደትም ከሌላው ለመማርና ሌላውንም ለማስተካከልና ለመደገፍ የሚያደርገው ጥረት አናሳ መሆን እንዲሁም በሥራ የሚፈጠሩ ችግሮችን ወደ ራስ ከመውሰድ ይልቅ ውጫዊ የማድረግ ችግሮች የሚታዩበት ነው፡፡

ሌላው ብቃትና ክህሎት ያለውና ዕቅዶቻችንን ማስፈፀም የሚችል የሰው ኃይል በማሟላት፣ ለስራው የሚያስፈልጉ መሣሪያዎችን /ግብዓቶችን በወቅቱና በዓይነት አሟልቶ በማቅረብ እና የሥራ ተነሳሽነትን የሚጨምሩ ምቹ የሥራ አካባቢዎችን በመፍጠር ረገድ የተከናወኑት ሥራዎች (በነበረው የበጀት እጥረት ምክንያት) ክፍተት የነበረባቸው በመሆኑ መሻሻል የሚገባቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም ባለሙያውን በቅርብ በመከታተልና በመደገፍ በተሰማራበት መስክ ውጤታማ እንዲሆን ከቁሳዊ ጥቅም ይልቅ ሞራላዊ ጥቅሙን አጕልቶ እንዲያይ ማድረግና ያለበትን የሙያ እና የልምድ ክፍተት መሙላት ያስፈልጋል፡፡ ተደግፎ ለመለወጥ ዝግጁ ያልሆነውን ሀይል ደግሞ ህግና አሰራርን የተከተለ የእርምት እርምጃ በመውሰድ የሴክተሩን ባለሙያ ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር በትኩረት መስራት ይጠይቃል፡፡

በአጠቃላይ በከተማ አጀንዳዎች ዙሪያ ውጤት ላይ ያተኮሩ እቅዶችን አቅዶ የሚፈፅም፣ ዘመናዊ አሰራሮችንና ቴክኖሎጅዎችን የሚጠቀም እንዲሁም ስትራቴጅካዊ አመራር መስጠት የሚችልና በዘርፉ በቂ ዕውቀት እና ክህሎት ያለው አመራርና ፈጻሚ ባልተፈጠረበት ሁኔታ ቀልጣፋና ቀጣይነት ያለው ልማት ማረጋገጥ፣ የዜጎችን ዕርካታ ማሳደግ አዳጋች እና በቀጣይ ብዙ መስራት የሚጠይቅ በመሆኑ በቀጣይ ዕቅዳችን የከተማ ፕላን እና የከተማ አመራር ማሰልጠኛ ተቋማትን በማደራጀትና ሰፊ ስልጠና በቀጣይነት በማመቻቸት በልዩ ትኩረት አጠናክሮ የማስቀጠል ጉዳይ ለስትራቴጅው መፈጸም ወሳኝ መሆኑ እንደ አንድ መሰረታዊ መነሻ መውሰድ ይገባል፡፡

## 1.4. የተገልጋይና የባለድርሻ አካላት ሁኔታ

### 1.4.1. የከተማ ነዋሪው ህዝብ ሁኔታ

ማዕከላዊ ስታስቲክስ ባለስልጣን በ214 የክልሉ ከተሞች ብቻ ባደረገው ጥናት በክልሉ ከተሞች የሚኖረው ህዝብ ከጠቅላላ የክልሉ ህዝብ ብዛት 21 በመቶ እንደሚሸፍን ያሳያል፡፡ እንደ ፕላንና ልማት ቢሮ 2016 ዓ.ም መረጃ በከተማ የሚኖረው 5,197,996 (22.07 በመቶ) (ወንድ 2,450,151 ሴት 2,747,845) ነው፡፡ ይሁን እንጅ የተቋሙ አስተዳደራዊ መረጃ እንደሚያሳየው አሁን ባሉን 729 ከተሞች የሚኖረው ህዝብ ብዛት 7,606,326 ሲሆን ከጠቅላላ የክልሉ ህዝብ ብዛት 32.3 በመቶ ይሸፍናል፡፡

ይህ የከተማ ነዋሪ ህዝብ የተቋሙ ቀጥተኛ ተገልጋይ እና የልማቱም ዋነኛ ባለድርሻ አካል ሲሆን ሰላም፣ ልማት እና ብልጽግና የሚሸት እና ለእነዚህ አላማዎች የሚተጋ ከመሆኑም በላይ በተግባር ከገጠር ወደ ከተማ በየዓመቱ የሚተም እና ለራሱ ገበያ እየፈጠረ ያለ ህዝብ ባለቤቶች መሆናችን፤ በከተሞች በርካታ የመልካም አስተዳደር ችግሮች እየተፈጠሩ ያሉ ቢሆንም በሂደት ይፈታልኛል የሚል ተስፋ ይዞ በትዕግስት አቤቱታውን እያቀረበ ያለ ህዝብ መሆኑና የመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዲፈቱለት ፊት ለፊት በመታገል በብልሹ አሰራር ውስጥ ያሉትን አመራር እና ለባለሙያ ማጋለጥ መጀመሩ፣ የክልላችን ህዝብ የሚኖርባቸውን ከተሞች እንዲለወጡና እንዲለሙ፣ በጉልበቱ፣ በገንዘቡና በቁሳቁስ የሚያደርገው ተሳትፎ እያደገ የመጣ መሆኑ፤ እንዲሁም የሚኖርበትን ከተማና አካባቢ በማልማት በተለይም ከመንገድ ከፈታ እስከ አስፖልት መንገድ ግንባታ፣ አካባቢውን በማፅዳት፣ ለጽዳት የሚከፈል ክፍያን በማሰባሰብ፣ ችግኝና ፍራፍሬ በመትከል... ወዘተ ተጨባጭ ተግባር ውስጥ የገባ ህዝብ መሆኑ፤ በዚህም በ2017 በጀት ዓመት 9 ወር ውስጥ በጥሬ ገንዘብ 670,242,766 ብር፣ በጉልበት 712,924,963 ብር፣ በቁሳቁስ 463,520,413 ብር በድምሩ 1,846,688,142 ብር የሚያወጣ የህዝብ ተሳትፎ መደረጉና ወንድ 1,722,360 ሴት 1,523,286 በድምሩ 3,244,646 የህብረተሰብ ክፍል (ከዚህም ውስጥ ወንድ 665,880 ሴት 591,580 በድምሩ 1,257,460 ወጣቶች) በቀጥታ በጉልበቱ የተሳተፈ መሆኑና መሠል ጥንካሬዎች ያሉት ቢሆንም ወደ ፊት በትኩረት መታረም እና መስተካከል ያለባቸው ድክመቶችም ይስተዋሉበታል፡፡

ለአብነትም የሚኖርበትን ከተማ የእድገት፣ የልማትና የብለጽግና መንስኤ እና ባለቤት ራሱ መሆኑን ተገንዝቦ ለማልማት ያለው እንቅስቃሴ ውስንነት ያለበት መሆኑ (የልማቱ ባለቤት ከመሆን ይልቅ ለመንግስት ብቻ መግፋት)፤ ከህጋዊ ተጠቃሚነት ይልቅ መሬት ወረራና ህገ ወጥ ግንባታ ላይ መሳተፍ፤ ጽዱና ውብ ከተማ የሚመኝ ህብረተሰብ ያለውን ያህል ለከተማ ጽዳትና ውበት የማይጨነቅ፣ መንገድ በማበላሸትና የጎርፍ ማስተላለፊያ ቱቦዎችን በመዝጋት ሳያውቀው ለጎርፍና ለተለያዩ አደጋዎች የተጋለጠ መሆኑ ወዘተ በድክመት የሚወሰዱ ናቸው፡፡ በአጠዋላይ የከተማ ነዋሪውም መሰረተ-ልማትና ማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች እንዲሟሉለት መሞገት መጀመሩ መልካም አጋጣሚ ቢሆንም ሁሉንም ነገር መንግስት ሊሰራለት እንደሚገባ አድርጎ የመመልከት እና በህገ-ወጥ ግንባታና መሬት ወረራ ላይ በመሳተፍ ያላግባብ የመጠቀም ዝንባሌ በስፋት ይስተዋላል፡፡ በመሆኑም ህዝባችን በቅርበት መደገፍና ማነሳሳት፣ ማደራጀትና ያሉበትን ክፍተቶች ማረም እንዲሁም ህግና ስርዓት እንዲይዝ ማድረግ ከቻልን ከተሞችን ለመለወጥና ለማሳደግ አማራጭ የሌለው ትልቅ አቅም አድርጎ መጠቀም ይገባል፡፡

### 1.4.2. የከተማው ወጣት ሁኔታ

እንደ ፕላንና ልማት ቢሮ 2016 ዓ.ም መረጃ ከክልሉ ሕዝብ 56.22 በመቶ (13,240,152) የሚሆነው በሥራ ሊሰማራ የሚችል (15 - 64 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ) ሲሆን ከዚህም ውስጥ 26.12 በመቶ (3,458,366) የሚሆነው በከተማ የሚገኝ ነው፡፡ እንዲሁም ከአምራች ሀይሉ ውስጥ 53.6 በመቶ (7,096,000) የሚሆነው በወጣትነት (15 - 29 ዓመት) የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን 29.95 በመቶ (2,125,364) የሚሆነው በከተማ የሚገኝ ነው፡፡

እንደ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ እ.ኤ.አ. 2020 በአማራ ክልል በአጠቃላይ 891,911 (321,833 ወንድ እና 570,078 ሴት) ሥራ አጥ ዜጎች የነበሩ ሲሆን 523,042 (187,881 ወንድ እና 335,161 ሴት) ወጣቶች ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ 471,786 (155,946 ወንድ እና 315,840 ሴት) ሥራ አጦች በከተሞች የሚገኙ ሲሆን 302,144 ወጣቶች (94,014 ወንድ እና 208,160 ሴት) ናቸው፡፡

በከተሞች የለውጥ ሀይል የሚሆን የሰለጠነ ግን ስራ ያጣ እና በስራ ላይ ያለ ወጣት ይታያል፡፡ ይህ አምራች ሀይል የሆነው ወጣት በቅርበት ቢደገፍ እራሱን ለውጦ በከተሞች ዕድገት ላይ የሚያመጣው ተጽዕኖ በጥንካሬ የሚወሰድ ነው፡፡ ለአብነትም ወጣቱ የቆሸሹ አካባቢወችን በማጽዳት በማልማት እና ገቢ ማስገኛ በማድረግ የከተማ ውበት የመጠበቅ ሚናው እየተጠናከረ የመጣ መሆኑ፤ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት ተግባር በተናጠልና በጋራ በመሰማራት ያረጁና የወደቁ ቤቶችን በመጠገን እና አረጋዊያንን በመደገፍ ጉልህ ሚና ያለው መሆኑ፤ የከተማውን ድምቀት የሚያሳድጉ አገልግሎቶችን በመስጠት /የፖርኪንግ፣ ላቪያጅ፣ የቤትና የቢሮ እቃዎች ምርት እና በግንባታ/ ላይ በመሰማራት የሚያበረታታ ተጨባጭ ለውጦች እየታዩ ያሉ መሆኑ፤ በአካባቢያቸው ተደራጅተው የአካባቢውን ደህንነት የሚጠብቁ ቅንና ተነሳሽነት ያላቸው ወጣቶች እየተበራከቱ የመጡ መሆናቸው… ወዘተ ከወጣቶች አኳያ በጥንካሬ የሚታዩ ናቸው፡፡

ይሁን እንጅ ሳይለፉ እና ሳይደክሙ በህገ-ወጥ ተግባራት በመሳተፍ በአቋራጭ ለመክበር የሚፈልጉ ወጣቶች ቁጥር እያደገ መምጣቱ፤ አልባሌ ቦታዎች ላይ የሚውሉና በሱስ የተጠመዱ ቀላል ማይባል ቁጥር ያላቸው ወጣቶች መኖራቸው…ወዘተ ወጣቶች ላይ የሚስተዋሉ ችግሮች ናቸው፡፡ በመሆኑም ወጣቱ የኢንቨስትመንት አቅም እንጅ ጠንቅ በማይሆንበት ደረጃ በቅርበት በመደገፍና ድክመቱን በማረም የከተሞች የለውጥ ሀይል አድርጐ በየመንደሩ በማሰማራት ልዩ ልዩ የመሠረተ ልማት ስራዎችን ማከናወን እንዲችል በትኩረት መስራት ይገባል፡፡

## 1.4.3. የግል ባለሀብቱ ሁኔታ

ነጻ ገበያ ስርዓት በሚገነባ ሀገር የግል ባለሀብቱ የኢኮኖሚው ዋና ሞተር ነው፡፡ የከተሞች የገቢ መሰረትም ከግል ባለሀብቱ ማደግ ጋር የሚቆራኝ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ የከተሞች ለውጥ እና ዕድገት ዋነኛው ባለቤት የሆነው ባለሀብት ከታዳጊ እስከ ሪጅኦፖሊታን ከተሞች ሀብቱን በማፍሰስ እያደረገ ያለው እንቅስቃሴ የሚበረታታ ከመሆኑም በላይ ሆቴል፣ ሆስፒታልና ት/ቤት በመገንባትና የአምራች ኢንዱስትሪዎችን ለመትከል ፕሮጀክት ቀርፆ በመቅረብ ያለው ዝንባሌ የሚያበረታታ መሆኑ፤ የሚጠበቅበትን ግብር እና የአገልግሎት ክፍያ በመክፈል የከተሞችን ገቢ በማሳደግም የማይተካ ሚና ያለው ሀይል መሆኑ፤ የሚፈለገውን ያህል ባይሆንም በቤት ልማት ስትራቴጅው በመሳተፍና ቤት ለሌላቸው አካላት ቤት ገንብቶ በማስረከብ የቤት ችግሩን የመጋራት ልምዱ እያደገ መምጣቱ፤ የወሰዱትን የፕሮጀክት ቦታም በፍጥነት ገንብቶ ለማልማት ጥረት የሚያደርጉ በርካታ ባለሀብቶች መኖራቸው፤ እንዲሁም ከተሞች የተረጋጋ ገበያና የኢኮኖሚ ማዕከል በመሆን የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ የማይተካ ሚና እየተጫወቱ መሆኑ በጥንካሬ የሚወሰድ ነው፡፡

ይሁን እንጅ ባለሀብቱ ፕሮጀክት ቀርፆ መሬት በመያዝና እሴት ሳይጨምር በመሸጥ በአቋራጭ ለመክበር መሞከሩ፣ አብዛኛው ባለሀብት ያልተገባ ጥቅም ለማግኘት ለአመራሩም ሆነ ለባለሙያው መደለያ በመስጠት የብልሹ አሰራር ተባባሪ መሆኑ፤ በየከተሞች የተወሰዱ ፕሮጀክቶች ከጅመር ህንፃ፣ ከመጋዝን ኪራይ እና ከአጥሮ ማስቀመጥ ያለፈ ተግባር የማይፈጽሙ ባለሀብቶች ቁጥር ቀላል አለመሆኑ፤ የገጠር ከተማ ትስስርን መሠረት ያደረገ ኢንቨስትመንት አለመከተል ለምሳሌ የአርሶ አደሩን ምርት ፕሮሰስ የሚያደርግ ፋብሪካ ላይ ያለማተኮርና አርሶ አደሩም ለፋብሪካ ብሎ እንዲያመርት አለማድረግ፣ በአካባቢው የሚገኝ አርሶ አደርን አውቶግሮውር አድርጉ አለመጠቀም፤ ከገጠር ከተማ እየፈለሰ ያለውን የሰለጠነ ወጣት አቅምና ሰፊ ጉልበት አለመጠቀም፣ እንዲሁም ህብረተሰቡን በሚጠቅም የአካባቢና ማህበራዊ ልማት ያለመሳተፍ ሁኔታ መኖሩ…ወዘተ ከግል ባለሀብቱ አኳያ በቀጣይ መታረም ያለባቸው ድክመቶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በግል ባለሀብቱ በኩልም የህዝብና የመንግስት የሆነውን ውስን ሀብት/መሬትን በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ያላግባብ ይዞ በአቋራጭ ለመበልፀግ የሚደረገው እንቅስቃሴ አልተገታም፡፡ በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪውም ጥቂት የማይባሉ ስራ ተቋራጮች አገራዊ ፋይዳውን ተረድተው ዘላቂ ጥቅማቸዉን ከማስጠበቅ ይልቅ ጊዜያዊ ጥቅም የመፈለግ ዝንባሌያቸው ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የከተማ እና መሠረተ ልማት ዋነኛ አቅም የሆነውን ባለሀብት ጥንካሬውን በማጉላትና ድክመቱን በማረም በከተማ መሰረተ

ልማትና አገልግሎት አቅርቦት፣ በፋይናንስ አቅራቢነት፣ በቤት ልማትና ግንባታ ስራዎች በግልና ከከተሞች ጋር በሽርክና ማሳተፍ ውጤታማና አዋጭ በመሆኑ የስትራቴጅው አካል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

### 1.4.4. በከተማ ፅዳት፣ ውበትና አረንጓዴ ልማት የተሰማሩ ማህበራት

በከተሞች በደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ እንዲሁም በአረንጓዴ ልማት ስራ ላይ የተሰማሩ በርካታ ቁጥር ያላቸው ማህበራ አሉ፡፡ ለአብነትም በ90 ከተሞች ደረቅ ቆሻሻን በመሰብሰብና በማስወገድ ስራ ብቻ ተሰማሩ 4,818 አባላት ያሏቸው 231 ማህበራት አሉ፡፡ እነዚህ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ሰጪ ማህበራት ቆሻሻን ሳይጸየፉ የፅዳት ስራውን በተገቢው መንገድ በማከናወን ቆሻሻን ከመሰብሰብና ከማስወገድ ባሻገር በመልሶ መጠቀም ተጨማሪ ገቢ የሚያገኙበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ የጽዳትና አረንጓዴ ልማት ስራው የሚያስፈልጉ ተሽከርካሪዎች (ገልባጭ፣ ካሬታ፣ ዶዘር ወዘተ)፣ መሳሪያዎች (አካፋ፣ አጁማ፣ መቀስ፣ መኮትኮቻ)፣ የደህንነት መጠበቂያ እቃዎች እና አልባሳት እንዲሁም የስራ ማስኬጃ በጀት በከተሞች እንዲሟላ እተደረገ ያለው ጥረት አበረታች ነው፡፡

ይሁን እንጅ የአገልግሎት አሰጣጥ ከስታንዳርድ በታች መሆን፣ የሚጠቀሙባቸው ተሽከርካሪዎች ከደረጃ በታች መሆን፣ ከኮምፖስት ውጭ ላሉ የቆሻሻ መልሶ መጠቀም ምርቶች የገበያ ትስስር አለመኖር፣ የማህበር አባላት የጤና መድን አገልግሎት እዲያገኙ እየተደረገ አለመሆኑ፣ ዘላቂ የፋይናንስ ስርዓት አለመዘርጋትና አለማስቀጠል፣ የመንግስት ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ክትትል እና ድጋፍ የላላ መሆን እንዲሁም ማህበራትን ከአጋር አካላት (ረጅ ድርጅቶች እና ሲቪክ ማህበራት … ወዘተ) ጋር አቀናጅቶ ያለመምራት ችግሮች ይስተዋላሉ፡፡

### 1.4.5. ሌሎች ባለድርሻ አካላት

ሌሎች ባለድርሻ አካላት የተባሉት የተቋሙን ተግባራት የሚጋሩና ለጋራ ውጤት ተቀናጅተው መስራት ያለባቸው ሌሎች አቻ የመንግስት ተቋማት ሲሆኑ ለአብነትም ከመሬት ቢሮ ጋር በከተሞች ማስፋፊያ አካባቢ የመሬት አቅርቦትና ዝግጅት፣ በመሬት መረጃ ማዘመን (ካዳስተር) ስራዎች፣ በልማት ተነሽዎች የካሳ አከፋፈል፣ በገጠር አገልግሎት መስጫ ማዕከላት የከተማነት እውቅና አሰጣጥ ዙሪያ፤ ከአካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን ጋር በከተሞች ፅዳትና አረንጓዴ ልማት፣ ከፖሊስ፣ ከፍ/ቤት፣ ከፍትህና ከፀረ-ሙስና ጋር በተለያዩ መመሪያዎች /ሰነዶች ዝግጅት፣ በህግ ማማከር፣ በህገ-ወጥ መሬት ወረራና ግንባታን በመከላከል ረገድ፣ በተቋሙ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮችን ከማስተካከልና ሌብነትን ከመታገል አንፃር፤ ከገቢዎች ቢሮ ጋር በከተማ አገልግሎት ገቢ አሰባሰብ ዙሪያ፤ ከገንዘብ ቢሮ ጋር በበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች፤ ከፕላን እና ልማት ቢሮ ጋር በከተሞች አስተዳደር ወሰን፣ በከተማ እውቅና እና ደረጃ ሽግግር፤ ከኦዲት ቢሮ ጋር በፋይናንሽያልና ክዋኔ ኦዲት ዙሪያ፤ ከህ/ስ/ማህበራት ማደራጃ ጋር በመኖሪያ ቤት ህ/ስ/ማህበራት አደረጃጀትና አሰራር ዙሪያ፤ ከስራና ስልጠና ቢሮ ጋር በስራ እድል ፈጠራ ዙሪያ፤ ከኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ጋር የምደባ ቦታ የሚፈልጉ የልማት ፕሮጀክቶችን በመለየት፣ በመወሰንና ወደ ልማት በማስገባት ረገድ፣ ከወጣቶችና ስፖርት ቢሮ እንዲሁም ሴቶች ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ጋር በወጣቶች፣ በሴቶች፣ በህፃናት፣ በአካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነት ዙሪያ፤ ከሲቪል ሰርቪስና የሰው ኃብት ልማት ኮሚሽን ጋር በመዋቅራዊ አደረጃጀት ዙሪያ…ወዘተ በቅንጅት እየተሰራ ይገኛል፡፡

ይሁን እንጅ ከነዚህ ተቋማት እንዲሁም ከሌሎች መሰረተ ልማት አቅራቢና ተዛማጅ ተቋማት (መብራት፣ መንገድ፣ ውሃ፣ ቴሌ) ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር ደካማ ከመሆኑም በላይ በዕቅድ ዝግጅትም ሆነ በትግበራ ወቅት ተቀናጅቶ የመስራት ልምዱ ውስንነት ያለበት ነው፡፡ ለከተማ ልማት ወሳኝ ሚና ካላቸው ሌሎች የመንግስት ተቋማት እንዲሁም መንግስታዊ ካልሆኑና የግል ተቋማት ጋር ያለው ግንኙነትም ሆነ የመናበብና ተቀናጅቶ የመስራት ልምድም በሚፈለገው ደረጃ ላይ የደረሰ አይደለም፡፡ በተዋረድ በሚገኙ እርከኖችም ቢሆን ከተሞችን ለመምራትና ለመደገፍ የተዘረጉት መዋቅሮችና ተቋማት ተናበውና ተቀናጅተው በጥብቅ ትስስር፣ ተመጋጋቢነትና ተደጋጋፊነት ባለው መልኩ እየተመሩ አይደለም፡፡

## 1.5. የልማት አቅሞች ሁኔታ ዳሰሳ

ለዘርፉ ልማት ወሳኝ ከሆኑት ሰብዓዊና ቁሳዊ ሀብቶች (ፀጋዎች) መካከል የመጀመሪያው ራሱ ሰው ሲሆን መሬት፣ ውሃ፣ ሀይል፣ ቴክኖሎጅ እና ፋይናንስ ደግሞ ከሰው ሀይል ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ የሚታዩ ናቸው፡፡ ሥለሆነም እነዚህን ሀብቶች በማልማት በግብዓትነት መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

### 1.5.1. ሰብዓዊ ሀብት

የከተማ ልማት ስራ ውስብስብና ፈርጀ-ብዙ ከመሆኑም በላይ የተለየ የአመራር ጥበብን እና ምናልባትም ከ50 እና 100 ዓመታት በኋላ የሚደረስበትን ውጤት አሁን ላይ ሁኖ ለማቀድ የሚያስችል እይታን የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህ ልክ አርቆ ማየት ካልተቻለ ደግሞ በሰለጠኑ ሀገራት እደታየው አሁን እኛው የገነባነውን ግዙፍ ህንፃ (መሰረተ-ልማት) ቀጣዩ ትውልድ በላዩ ከመጨመር ይልቅ እያፈረሰ የሚቀጥልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ ከዚህም አኳያ የከተማ አመራር ጥበብ እና እይታ ለሁሉም የከተማ ልማት ስራዎች ውጤታማነት ወሳኝ ሚና ያለው ቢሆንም ከተማን በፕላን መምራት የሚችል ልምድ ያካበተ የአመራር አቅም እና በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ሀይል በሰፊው አልነበረም፡፡ ይህን ክፍተት ለመሙላትም ከኢፌዴሪ ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ከሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲ ጋር በመተባበር በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በ2ኛ ዲግሪ እና በ3ኛ ዲግሪ ከክልል እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ያሉ የዘርፉ አመራሮችንና ፈፃሚዎችን በከተማ ልማት ዘርፍ እውቀታቸውን እንዲያሻሽሉ እየተደረገ ያለ ሲሆን በሀገሪቱ ያሉ በርካታ ዩነቨርሲቲዎችም ለዘርፉ እድገት በሚያስፈልጉ የሙያ አይነቶች (በከተማ አስተዳደር፣ በፕላን፣ በመሬት እና በፋይናንስ ወዘተ) ባለሙያዎችን እያስመረቁ ይገኛሉ፡፡ በዘርፉ የተሰማራውን የሰው ኃይል የእውቀትና የክህሎት ክፍተት ለመሙላትም በተመረጡ ዘርፎች ላይ የባለሙያዎች ስልጠና እና ምዘና ስርዓት በመዘርጋት የማሰልጠን እና የማስመዘን ስራ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ሌላው የሀገራችን የትምህርት ፖሊሲ ለሳይንስና ለምህንድስና ዘርፍ ከሰጠው ልዩ ትኩረት ጋር በተያያዘ ብዙ ቁጥር ያላቸው የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች በየዓመቱ እየተመረቁ ወደ ኢንዱስትሪው መቀላቀላቸው እንደ አንድ መልካም አጋጣሚ የሚወሰድ ቢሆንም እነዚህ ምሩቃን ከኢንዱስትሪው ጋር በተግባር የተቆራኘ ክህሎት አዳብረው ለኢንዱስትሪው እድገት የበኩላቸውን ሚና በተሻለ ደረጃ እንዲወጡ ከማድረግ አኳያ የዩኒቨርሲቲ-ኢንዱስትሪ ትስስርን በማጠናከር ወደ ኢንዱስትሪው በቀጥታ ከመቀላቀላቸው በፊት ለተወሰኑ ጊዜያት ተጨማሪ ተግባር ተኮር ስልጠና የሚወስዱበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ ይሁን እንጅ በከተሞች የስነምግባር፣ የልምድ እና የሙያ ዝግጅት የሌላቸው አመራሮች በስፋት መመደባቸው አሁን ካለው የአመራር በፍጥነት መቀያየር ጋር ተዳምሮ ከተሞችን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችል አቅም እንደሌለ ያሳያል፡፡ የባለሙያዎች የችግር ፈቺነትና መፍትሄ አመንጭነት አሁንም ትልቅ ስራ የሚጠይቅ ነው፡፡

### 1.5.2. የመሬት ሀብት

መሬት በባህሪው አዲስ የማይፈጠር ውስን ሀብት በመሆኑ በልዩ ሁኔታ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ለከተማ ግንባታ ወሳኝ የሆነው ይህ ሀብት ክልላችን ካለው የቆዳ ስፋትና የየብስ ክፍል አንፃር ሲታይ እንደ ሲንጋፖር ራስን በጠበበ ሁኔታ የሚወጥር አይደለም፡፡ አብዛኛው የመሬት ክፍልም ለከተማ ግንባታ ብዙ አስቸጋሪ አይደለም፡፡ በህገ-መንግስትና በፖሊሲ ደረጃም መሬት የህዝብና የመንግስት በመሆኑ ለተፈለገው ልማት ለማዋል በአንፃራዊነት ሰፊ ዕድል አለው፡፡

ይሁን እንጅ ይህ ሀብት የተጠቀሱት አስቻይ ሁኔታዎች የሚታዩበት ቢሆንም ከባህር ዳር ውጭ ያሉ አብዛኞቹ የክልላችን ከተሞች (ጎንደር፣ ደሴ፣ ወልደያ፣ ደ/ታቦር፣ ደ/ብርሃን፣ ላሊበላ፣ ...ወዘተ) በተራራ አካባቢ የተቆረቆሩ ስለሆነ ለመስፋፋትና ለመሰረተ-ልማት ዝርጋታ አመች አይደሉም፡፡ ከፕላን ጉድለት በተነሳም በአንፃራዊነት ለእርሻና ለደን መሆን የሚገባውን መሬት ለከተማ ማስፋፊያነት በማካተት ለመሰረተ-ልማት ወጭ መጨመር ምክንያት ከመሆኑም በላይ የመሬት አጠቃቀም ውጤታማነትን ይቀንሳል፡፡

### 1.5.3. የውሃ ሀብት

ከውሃ ሀብት ልማት አንፃር ክልላችን የውሃ ማማ እንደመሆኑ መጠን ለከተሞችም የሚሆን በቂ የውሃ ሀብት እንዳለ የሚያጠራጥር አይደለም ነገር ግን አብዛኞቹ ከተሞቻችን ከውሃ ምንጭ ርቀው ተራራ ላይ የተቆረቆሩ በመሆናቸው እና ለከተሞች የሚቀርበውን ውሃ ከምንጩ በማጣራት ንፅህናውን ጠብቆ በየደጁ እንዲደርስ ለማድረግ ከፍተኛ መዋለንዋይ እና ቴክኖሎጅ የሚጠይቅ በመሆኑ ከተሞቻችን ለልማት ቀርቶ ለመጠጥ አገልግሎት እንኳን በቂ ውሃ እያቀረቡ አይደለም፡፡ በተለይም ሰፊ ህዝብ የሚኖርባቸው ነባሮቹ ከተሞች እንኳን የፍላጎታቸውን 50 በመቶ ማቅረብ አልቻሉም፡፡ በውሃ ሀብት ከሌሎቹ ከተሞች የተሻለ መልካም አጋጣሚ/አስቻይ ሁኔታ ያሏት (የአባይና የጣና ውሃ አካላት ዙሪያዋን የከበቧት) ባህር ዳር ከተማ እንኳን እስከ አሁን የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ችግርን መፍታት አልቻለችም፡፡ ስለዚህ ይህን መሰረታዊ ችግር መፍታት ካልቻልን ከተሞችን በአረንጓዴ ማልማት፣ ውብ እና ለነዋሪዎቻቸው ምቹ ማድረግ ቀርቶ የማህበረሰቡን ጤና ማስጠበቅ አይቻልም፡፡

### 1.5.4. ታዳሽ ሀይል

ከሀይል ልማትና አቅርቦት አንፃርም ኢትዮጵያ ከራሷ አልፎ ለውጭ ማቅረብ የሚችል ታዳሽ እምቅ አቅም እንዳላት ይታወቃል፡፡ ይህን አቅም ለፍላጎታችን ለማዋልም ከህዳሴ ግድብ በተጨማሪ ሌሎች በርካታ የሃይል ማመንጫዎች የተገነቡ ሲሆን ከነበርንበት 2000 ሜጋ ዋት በታች አቅርቦት ወደ በ2016/17 ከ4000 ሜጋ ዋት በላይ ማደጉን የኢትዮጵያ ልማት ጥናት ተቋም መረጃ ያሳያል፡፡ የዚህ ሃይል ከፍተኛ ተጠቃሚዎችም ከተሞች ናቸው፡፡ ወደፊትም ከተሞች የኢንዱስትሪ ማዕከል እና የበርካታ ህዝብ መኖሪያ እንደመሆናቸው መጠን የሀይል ፍላጎታቸው ከፍተኛና አዳጊ ነው፡፡

በዘርፉ እስከ አሁን በተደረገው ጥረት እንደ ሀገር ጥሩ ለውጥ ቢኖርም የክልላችን ከተሞች አሁንም በሀይል ዕጥረቱ በከፍተኛ ደረጃ ተጎጅዎች ናቸው፡፡ በየደረጃው ውስብስብ ቢሮክራሲዎችን አልፈው በከተሞቻችን ከተገነቡት ኢንዱስትሪዎች መካከል አብዛኞቹ በሀይል አቅርቦች ችግር ምክንያት ወደ ስራ ያልገቡ/በሙሉ አቅማቸው የማይሰሩ ናቸው፡፡ እንደ ክልል ችግሩን ከማቃለል አንፃር በከተማ ደረጃ ጥቅም ላይ ሊውል የሚችል አማራጭ የሀይል ምንጭ (የፀሃይ ብርሃን) እየለማ አይደለም፡፡

### 1.5.5. ቴክኖሎጅ

ከቴክኖሎጅ ልማትና አጠቃቀም አንፃር የከተማ ልማት ስራ ከፍተኛ የቴክኖሎጅ ግብዓት የሚጠይቅ ውስብስብ ይዘት ያለው ነው፡፡ አሁን ባለንበት አለምም ይህን ስራ ለመደገፍ የሚችል በርካታ የቴክኖሎጅ ውጤት መኖሩ ትልቅ ተስፋ ነው፡፡ ይሁን እንጅ ቴክኖሎጅውን ለመኮረጅና ለማላመድ ከፍተኛ ሀብትና የመጠቀም ብቃትን የሚጠይቅ በመሆኑ ከተሞች ወቅቱ የሚፈልገውን ቴክኖሎጅ በበቂ መጠን ማቅረብ ያለመቻላቸውን ያህል አጠቃቀም ላይም ሰፊ ክፍተት አለባቸው፡፡

### 1.5.6. ፋይናንስ

ሌላው ሀብት ፋይናንስ/ገቢ ሲሆን ከላይ ላየናቸው ሌሎች ግብዓቶች አስቻይ ሁኔታ ፈጣሪና ለከተሞች የመሰረተ-ልማት ማደግ ወሳኝ ግብዓት ነው፡፡ ከተሞች የግብርና እና የኢንዱስትሪ ምርቶች እንዲሁም የአገልግሎት ግብይት ማዕከላት በመሆናቸው የፋይናንስ ዝውውር ማዕከልም ናቸው፡፡ በክልሉ ለሚከናውነው ሁለንተናዊ ልማት የሚያስፈልገውን ፋይናንስ/ገቢ ከፍተኛውን ድርሻ የሚያመነጩት ከተሞች ናቸው፡፡ ከዚህም ለከተሞች ልማት ፋይናንስ ወሳኝ እንደሆነ ሁሉ የከተሞች ማደግም የገቢ መሰረቶችን በማስፋትና በማሳደግ ለፋይናንስ ልማቱ የማይተካ ሚና እንዳለው መረዳት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጅ አሁንም የከተሞች የልማት ፋይናንስ አቅርቦት ከፍላጎታቸው በእጅጉ የራቀ ነው፡፡ አብዛኛው ከተሞች የድጎማ ጥገኞች ናቸው፡፡ ይህም የሆነበት ዋናው ምክንያት ከተሞች የገቢ መሰረታቸውንና ሃብታቸውን ለይተው አለማወቃቸው እና የፋይናንስ ልማትን ከከተማ ልማት ጋር በተገቢው መንገድ አስታሳስሮ በማቀድና ተመጋግበው እንዲያድጉ በማድረግ በኩል ክፍተት በመኖሩ ነው፡፡ ስለሆነም ከተሞችን ለማሳደግ የገቢ መሰረቶችን ከማስፋት በተጨማሪ የሚመነጨውን ገቢ አሟጦ መሰብሰብ ያስፈልጋል፡፡

## 2. የዕቅዱ መነሻዎች

### 2.1. የተቋሙ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈፃፀም እንደ መነሻ

### 2.1.1. ተቋማዊ የማስፈፀም አቅም ግንባታ ስራዎች አፈፃፀም

**የእቅድ ዝግጅት፡-** በዝግጅት ምዕራፍ ከሚከናወኑ ዋና ተግባራት ውስጥ አንዱና ዋናው ዕቅድን በጥራት ማቀድ ነው፡፡ በመሆኑም ከተቋሙ የ10 ዓመት መሪ እቅድ የተቀዳ፤ የተቋሙን ራዕይ እና ተልዕኮ መሰረት ያደረገ፤ የተለጠጠ (ሰፊ) ግን ሊደረስበት የሚችል፤ ከፌደራልና ከክልል፣ እንዲሁም ከድጋፍ ሰጭ ድርጅቶች ጋር የተናበበ፤ ጥራት ያለው፣ በጊዜ የተገደበና የተተነተነ፣ በውጤት ላይ ያተኮረ፣ የህዝብ ተሳትፎን ዋነኛ አቅም ያደረገ እንዲሁም ቅንጅታዊ አሰራርን መሰረት ያደረገ የ2017 በጀት አመት የልማትና መልካም አስተዳደር ዕቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

ከሐምሌ 1/2016 ዓ/ም ጀምሮ ጥራት ያለው የክረምት ተግባራት እቅድ እና ቼክሊስት በማዘጋጀት በእቅዱ እና በቼክሊስቱ ላይ ከፈፃሚ አካላት ጋር የጋራ መግባባት ተፈጥሮ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ ሌላው የፕሮጀክት ባህሪ ያላቸውን UIIDP እና የከተማ ምግብ ዋስትና በራሳቸው ባህሪ የፕሮጀክት እቅድ ተዘጋጅቶ ወደ ስራ ተገብቷል፡፡ በተጨማሪም የተቋሙን 40 ዋና ዋና ግቦችን ያካተተ የመግባቢያ ሰነድ በማዘጋጀት ከፌደራል ከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር ጋር የፊርማ ስነ ስርዓት ተካሂዷል፡፡

**የእቅድ ኦረንቴሽ:-** ጥራት ያለው ዕቅድ ማቀድ አንዱ ተግባር ሲሆን በዕቅዱ ላይ ከፈጻሚ አካላት ጋር በቂ መግባባት መፈጠር ደግሞ ሌላኛው ትኩረት የሚሰጠው ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በየደረጃው ያለውን እምቅ አቅም ግምት ውሰጥ ያስገባ እቅድ በማቀድ በመነሻ ሁኔታውና በሚከናወኑ ተግባራት ላይ ከ15,262 ፈፃሚና አስፈፃሚ፣ ከ12,932 ከባለድርሻ አካላት እንዲሁም ከ399,692 ከተማ ነዋሪ ጋር በቂ መግባባት ለመፍጠር ታቅዶ በክልል፣ በዞኖች እና በከተሞች በተካሄዱ የ2016 በጀት ዓመት ዕቅድ አፈጻጸም ግምገማና የ2017 በጀት ዓመት እቅድ ኦረንቴሽን መድረኮች ወንድ 6,808 ሴት 3,212 በድምሩ 10,020 (65.65%) አመራሮችና ፈፃሚዎች፣ ወንድ 9,243 ሴት 5,397 በድምሩ 14,640 (ከ100% በላይ) የህዝብ ክንፍ /አጋር አካላት እና ወንድ 334,028 ሴት 217,805 በድምሩ 551,833 (ከ100% በላይ) የከተማ ነዋሪ ህዝብ ተሳትፏል፡፡

**የህዝብ ክንፍና አጋር አካላት መድረክ:-** በክልል ደረጃ ወንድ 190 ሴት 30 በድምሩ 220 የዘርፉ ባለድርሻ አካላት (የተቋራጮች እና አማካሪዎች ማህበራት፣ የግብዓት አቅራቢ ድርጅቶች፣ የኮንስትራክሽን ባለሙያዎች ማህበራት፣ የልማት ድርጅቶች፣ የዲዛይንና ቁጥጥር ተቋማት ወዘተ አመራሮችና ተወካዮች) የተሳተፉበትና በክልሉ ከፍተኛ አመራሮች የተመራ የኮንስትራክሽን ፎረም/መድረክ የተካሄደ ሲሆን በዚህ ፎረም የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው የደረሰበትን የእድገት ደረጃ፣ እያጋጠሙት ያሉ ተግዳሮቶችንና ማነቆዎችን እንዲሁም የመፍትሄ አቅጣጫዎችን እና ከባለድርሻ አካላት የሚጠበቁ ጉዳዮችን በተመለከተ ፍሬያማ ውይይት ተደርጓል፡፡

**የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ:-** በየደረጃው በየሩብ ዓመቱ የሥራተኛ የምክክር መድረክ (የቁልፍና አበይት ተግባራት አፈጻጸም ግምገማ መድረክ) በማዘጋጀት 15,262 (9,920 ወንድና 5,342 ሴት) አመራሮች እና ፈፃሚዎች እንዲሳተፉ ለማድረግ ታቅዶ በየደረጃው በተፈጠሩ የ2017 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም ግምገማ መድረኮች መሳተፍ ከነበረባቸው ወንድ 7,497 ሴት 3,706 ድምር 11,203 አመራሮች እና ፈፃሚዎች ውስጥ በ1ኛው ሩብ ዓመት እቅድ አፈፃፀም ግምገማ ወንድ 6,772 ሴት 3,329 ድምር 10,101 (90.16%) አመራሮች እና ፈፃሚዎች የተሳተፉ ሲሆን በ2ኛው ሩብ ዓመት እቅድ አፈፃፀም ግምገማ ደግሞ ወንድ 6,745 ሴት 3,514 ድምር 10,259 (91.57%) አመራሮች እና ፈፃሚዎች ተሳትፈዋል፡፡

**የአቅም ግንባታ ስልጠና:-** የከተማ ልማትና መልካም አስተዳደር ስራዎቻችን በላቀ ደረጃ ለማስፈፀም በተቋሙ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ማንዋሎች ላይ በየደረጃው ለሚገኙ 18,835 (35% ሴቶች) አመራሮች፣ ባለሙያዎችና አጋር አካላት በተለያዩ የስልጠና ሰነዶች ላይ ስልጠና ለመስጠት ታቅዶ ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጋር በመተባበር እንዲሁም በክልልና በከተሞች በተሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ወንድ 30,468 ሴት 38,197 ድምር 68,665 (ከ100% በላይ) አመራሮችና ፈፃሚዎች ተሳትፈዋል፡፡

### 2.1.2. የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ማሻሻያ ስራዎች

በተቋሙ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለይቶ በመፍታት እንዲሁም በዘርፉ የሚሰጠውን አገልግሎት ቀልጣፋና ውጤታማ በማድረግ የተገልጋዮች እርካታ በአማካይ 70% እንዲደርስ ለማድረግ ግብ ተይዞ በየደረጃው ባለው መዋቅራችን በህብረተሰቡ የሚነሱት የልማት ፍላጎት እና የመልካም አስተዳደር ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተበራከቱ በመምጣታቸው በተቋሙ የሚታዩ የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮች ወይም የሌብነት ተግባራት በስፋት የሚታዩባቸውን ዘርፎችና ችግሮች በመለየት ከቢሮው ጀምሮ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ ያሉ ሁሉም ተቋማት ከስራ ባህሪያቸው አንፃር ራሱን የቻለ የመልካም አስተዳደር ችግር መፍቻ እቅድ አቅደው ወደ ተግባር እንዲገቡ ተደርጓል፡፡

**በእቅድ የተለዩ ዋና ዋና የመልካም አስተዳደር ችግሮች:-** ከአገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት አንፃር የውሳኔ ማዘግየትና ማጉላላት (በስታንዳርድ መሰረት አገልግሎት አለመስጠት) እና መሰረታዊ የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች አቅርቦትና ተደሽነት ችግር፤ ከፕላን ዝግጅትና አፈጻጸም አንፃር በፕላን ዝግጅት ወቅት የፕላን ጥራት ችግር መኖር፣ ወቅቱን የጠበቀ የፕላን ዝግጅትና ክለሳ አለማድረግ፣ የፕላን ጥሰት እና ዞኒንግ ለውጥ መኖር፤ ከከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር አንጻር ሌብነትና አድሎዊ አሰራር መኖር፣ የሰነድ አልባ እና ከፊል ሰነድ አልባ ይዞታዎችን ሰነድ ሰጥቶ ያለማጠናቀቅ፣ ህገ-ወጥ የመሬት ወረራና ግንባታ መበራከት፣ የለማ የከተማ ቦታ አቅርቦት ችግር እና የከተማ መሬት መረጃ አያያዝ ችግር፤ ከቤቶች ልማትና አስተዳደር ስራዎች አኳያ የመኖሪያ ቤት አቅርቦትና ተደራሽነት ችግር እና የመንግስት ቤት መረጃ አያያዝና አስተዳደር ችግር፤ ከመሰረተ-ልማት አቅርቦት አንጻር የከተማ መሰረተ-ልማት አቅርቦት ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት እና የጥራት ችግር መኖር፤ ከከተማ ፅዳትና ውበት ስራዎች አንጻር የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ችግር እና

የከተማ አረንጓዴ ቦታ አስተዳደር ችግር፤ ከሰው ኃይል አስተዳደር አንጻር የሰራተኛን ጥቅማጥቅም አለማስከበር (ኬሪየርና የደረጃ ዝቅተኛ መሆን) ናቸው፡፡

**የተፈቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች፡-** እነዚህን በተቋሙ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮች ለመፍታት የሚያስችል ጥናት ባለፈው በጀት ዓመት የተጠና ሲሆን እንደ ችግሮች ክብደትና ቅለት በቅደም ተከተል ለመፍታት እቅድ ተይዞ በዞኖችና ከተሞች በእቅድ ከተለዩት 534 የመልካም አስተዳደር ችግሮች ውስጥ 408 (76.40%) የተፈቱ ናቸው፡፡

በከተሞች የሚስተዋሉ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ትኩረት ሰጥቶ ከመፍታት አኳያ በግማሽ ዓመቱ በሁሉም ዞኖችና ከተሞች ዝርዝር የአፈጻጸም ግምገማ እና ጥናት የተካሄደ ሲሆን የመልካም አስተዳደር ችግሮች በስፋት የሚስተዋልባቸው ዘርፎችን በተመለከተ መሬትና መሬት ነክ አስተዳደር ተግባራት፤ የህንጻ ሹም ተግባራት /ፕላን ስምምነት፣ ግንባታ ፈቃድ፣ ስመንብረት ዝውውር/፣ የኮንስትራክሽን ግዥወችና የፋይናንስ ነክ ተግባራት፣ የመንግስት ቤቶች አስተዳደር ወዘተ...ናቸው፡፡




**ቻርት 1፡- በዞኖችና ከተሞች በእቅድ ከተለዩና የተፈቱ የመልካም አስተዳደር ችግሮች**

**በዘርፉ የሚታየውን ሌብነት/ሙስና መከላከል፡-** በበጀት ዓመቱ በየደረጃው በሀብት ምዝገባ፣ በስነ-ምግባር እና በሙስና ወንጀሎች ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር ወንድ 38 ሴት 28 በድምሩ ለ66 ሀብት አስመዝጋቢዎች 2 የመጀመሪያ እና 64 የእድሳት ምዝገባ ተደርጓል፡፡

ሌላው አለም አቀፍ የፀረ-ሙስና ቀንን አስመልክቶ የተቋሙ ወንድ 118 ሴት 86 ድምር 204 አመራሮችና ባለሙያዎች የተሳተፉበት ውይይት ተደርጓል፡፡ እንዲሁም ወቅታዊ ሁኔታውን መሰረት በማድረግ በልዩ ልዩ የህገውጥነት ተግባር ውስጥ ገብተው በተገኙ 238 (102 አመራሮች እና 136 ባለሙያዎች) ላይ ህጋዊና አስተዳደራዊ ርምጃ መውሰድ ተችሏል፡፡

**የክልላዊ የፀጥታ ችግር ምክንያት በመዋቀወራችን የደረሰ ጉዳት፡-** እንደሚታወቀው ከሁለትና ሶስት ዓመታት ወዲህ የገጠመን ክልላዊ የፀጥታ ችግር በተቋማችን እስከታችኛው መዋቅር ድረስ በሚገኙ 122 አመራሮችና ባለሙያዎች ላይ ማለትም 17 የህይወት መሰዋትነት፣ 56 የአካል ጉዳት እና 49 የንብረት ጉዳት አስከትሏል፡፡

**አገልግሎት አሰጣጥ፡-** በበጀት ዓመቱ በዞን መምሪያዎች በኩል ከመሬት ይዞታ አስተዳደር ጋር ተያይዞ 99,881 ጉዳዮች ቀርበው ለ47,550 ጉዳዮች የቃል ምላሽ እና ለ32,199 ጉዳዮች የፅሁፍ ምላሽ የተሰጠ ሲሆን ለ20,352 ጉዳዮች ለፍትህና ለፀረ ሙስና ተቋማት በፅሁፍ ሙያዊ ማብራሪያ የተሰጠባቸው ናቸው፡፡ ከዞኑ አቅም በላይ ሁነው ወደ ቢሮው የመጡ ከመሬት ይዞታ አስተዳደር ጋር ተያይዞ 414 እና ከግንባታ ፕሮጀክቶች አስተዳደር ጋር የተያያዙ 2,967 በድምሩ 3,381 ጉዳዮች በፅሁፍ የቀረቡ ሲሆን ለ3,372 ጉዳዮች (ከመሬት አስተዳደር ጋር የተያያዙ 405 ጉዳዮች እና ከግንባታ ፕሮጀክቶች አስተዳደር ጋር የተያያዙ 2,967 ጉዳዮች) በፅሁፍ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ ከነዚህም ውስጥ 3,052 ጉዳዮች (ከመሬትጋር የተያያዙ 85 ጉዳዮች እና ከግንባታ አስተዳደር ጋር የተያያዙ 2,967 ጉዳዮች) ለፍትህና ለፀረ ሙስና ተቋማት በፅሁፍ ሙያዊ ማብራሪያ የተሰጠባቸው ናቸው፡፡ በመሬት ዘርፍ እስካሁን 9 ጉዳዮች ምላሽ ያልተሰጣቸው ሲሆኑ በቢሮው ደረጃ የጋራ ውሳኔ የሚሹ፣ በመስክ መጣራት ያለባቸው እና ተዓማኒነት የጎደላቸው የግለሰብ ቅሬታዎችም ይገኙበታል፡፡

**ለምደባ እና ለማስፋፊያ ቦታ ጥያቄዎች የተሰጠ ምላሽ፡-** በቢሮው ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ከተለያዩ ዞኖችና ከተሞች የቀረቡ የምደባ ጥያቄዎችን በተመለከተ ሆቴል 84፣ ጤና 23፣ ትምህርት 67፣ ሞል 70፣ ሎጅ 43፣ ሪልስቴት 118 እና ሌሎች 6 በድምሩ 411 ፕሮጀክቶች የቀረቡ ሲሆን ከነዚህም መካከል 102 ፕሮጀክቶች ውሳኔ ተሰጥቶባቸው ወደ ስራ እንዲገቡ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም በቢሮው በኩል ውሳኔ እንዲሰጥባቸው ከቀረቡት 68 የአገልግሎት ዘርፍ የማስፋፊያ ጥያቄዎች መካከል 57 ይዞታዎች የቦታ መጠናቸው 52,131.409 ካ/ሜ ውሳኔ የተሰጣቸው ሲሆን ከቀረቡ 8 የአምልኮ ቦታ ጥያቄዎች ውስጥ 7 የአምልኮ ቦታ ጥያቄዎች የቦታ መጠናቸው 30,800 ካ/ሜ ውሳኔ እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

**የኮንቲባና ስራ አስኪያጅ አስተዳደር ፍትህ መድረክ፡-** በ28 ከተሞች የከንቲባና ስራ አስኪያጅ አስተዳደር ፍትህ መድረክ በማቋቋም ለበርካታ ጊዜ ሲንገላቱ የቆዩ ተገልጋዮችን ችግር ለመፍታት በተደረገው ጥረት አበረታች ውጤት እየተመዘገበ ይገኛል፡፡ የከንቲባና ስራ አስኪያጅ አስተዳደር ፍትህ መድረክ ያቋቋሙ ከተሞች ሰ/ሸዋ (ሸዋሮቢት፣ መ/ሜዳ፣ ሞላሌ፣ አረርቲ፣ ቡልጋ፣ አስከተማ፣ ደብረሲና፣ እነዋሪና አጣየ)፣ ደ/ጎንደር (ወረታ፣ አ/ዘመንና እብናት)፣ ደ/ወሎ (ሀርቡ)፣ ም/ጎጃም (ደ/ወርቅ፣ ግ/ወይንና ደጀን)፣ ኦሮሞ (ከሚሴና ባቲ)፣ ዋግኸምራ (ሰቆጣ)፣ ሰ/ጎጃም (መራዊ)፣ ባ/ዳር፣ ጎንደር፣ ደሴ፣ ደ/ብርሃን፣ ደ/ማርቆስ፣ ኮምቦልቻ፣ ደ/ታቦር እና ወልደያ ናቸው፡፡

## 2.1.3. የህግ እና የአሰራር ማሻሻያ ስራዎች

ከአሰራር ጋር ተያይዞ የሚታየው ዋናው ጉዳይ ተቋሙ የሚመራባቸው የህግ ማዕቀፎች አግባብነትና ችግር ፈችነት ነው፡፡ ከዚህም አኳያ ብዙ ሊያሰሩ የሚችሉ የህግ ማዕቀፎች ያሉ ቢሆንም ተቋሙ የሚመራባቸው አብዛኛው አሰራሮችና መመሪያዎች የህግ ክፍተት ያለባቸው፣ አግባብነትና ችግር ፈችነት የጎደላቸው፣ ቢሮክራሲ ማራዘም የተጠናወታቸው እና ከወቅቱ ጋር የማይሄዱ በመሆናቸው እያደገ የመጣውን የህዝብ የልማትና መልካም አስተዳደር ጥያቄ የማይመልሱ ናቸው፡፡

በመሆኑም በተቋሙ ተዘጋጅተው በወረዱ የህግ እና የአሰራር ማዕቀፎች ላይ የክፍተት ትንተና እና የፋይዳ ግምገማ ጥናቶችን በማድረግ እንዲሁም የማሻሻያ ሃሳቦችን በማቅረብ 7 ነባር 7 አዲስ ደንብና መመሪያ፣ 1 ስትራቴጂ እና 1 የአሰራር ማኗል በድምሩ 16 የህግ እና የአሰራር ማዕቀፎችን ለማዘጋጀት ታቅዶ 16ቱም የተዘጋጁ ሲሆን ከነዚህም መካከል 5ቱ (የከተሞች አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና ታሪፍ ማሻሻያ ደንብ፤ የቤት ልማት ስትራቴጂ፤ የመኖሪያ ቤት ኪራይ ቁጥጥርና አስተዳደር መመሪያ፤ የከተማ ቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ስለማዘጋጀት፣ ስለማምከን እና ትክ አሰጣጥ መመሪያ፤ የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር የአሰራር ማንዋል) በበጀት ዓመቱ በመስተዳድር ምክርቤት ፀድቀው አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ ቀሪዎቹ 8 በማነጅመንት እና በህግ ክፍል በመታየት ላይ

የሚገኙ ሲሆን 3 በስራ ክፍሎች በመዘጋጀት ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ሰነዶች በማጠናቀቅ አስፀድቆ ወደ ተግባር ለመግባት እየተሰራ ይገኛል፡፡

**በአዲስ የተዘጋጁ የህግና የአሰራር ማዕቀፎችን በተመለከተ፡-** የመኖሪያ ቤት ኪራይ ቁጥጥርና አስተዳደር መመሪያ፤ የከተማ ቦታ ይዞታ ማረጋገጫ ሰነድ/ካርታ ስለማዘጋጀት፣ ስለማምከን እና ትክ አሰጣጥ መመሪያ፤ የሪል ስቴት መመሪያ፤ የማካካሻ ቤት መመሪያ፤ የመንግስት ሠራተኞች የመኖሪያ ቤት ልማት መመሪያ፤ አረንጓዴ ቦታዎችን ለማስተዳደር፣ በጊዛዊነት ለማስተላለፍና የስራ ዕድል ለመፍጠር የሚያስችል የአሰራር ማንዋል፤ የከተማ መሬት ልማትና አስተዳደር የአሰራር ማንዋል ናቸው፡፡

**ማሻሻያ የተደረገባቸው የህግና የአሰራር ማዕቀፎችን በተመለከተ፡-** የደቀቁ ግንባታዎች የሚገኙበትን የከተማ ቦታ መልሶ ማልማት መመሪያ፤ የስመንብረት ዝዉዉር መመሪያ፤ የጥቃቅንና አነስተኛ የኮ/ ኩባ/ የምዝገባና የብቃት ማረጋገጫ መመሪያ፤ የመንግስት ቤት አስተዳደር መመሪያ፤ የመኖሪያ ቤት ህ/ስ/ማ/ የቤት ልማት መመሪያ፣ የከተማ ቦታ የነባር ይዞታ ኪራይና የሊዝ መነሻ ዋጋ፣ የከተሞች አገልግሎት ገቢ አሰባሰብና ታሪፍ ማሻሻያ ደንብ ናቸው፡፡

### 2.1.4. ተቋማዊ አሰራርን ማዘመን (E- Service)

በተቋሙ የሚታየውን ብልሹ አሰራርና ሌብነት ለመታገል እንዲሁም ፈጣንና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት የተገልጋይ እርካታን ለማሳደግ ተቋማዊ አሰራሮችን ማሻሻልና ማዘመን አስፈላጊ ነው፡፡ በመሆኑም ቤት መረጃ አደረጃጀትና አስተዳደር ሶፍትዌር በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኩል ለምቶ አገልግሎት ላይ የዋለ ሲሆን እስከ አሁን በዞኖችና ከተሞች 39,559 የመንግስት ቤቶችን ወደ ዘመናዊ የቤት መረጃ ስርዓት (system software) ማስገባት ተችሏል፡፡

**የሶፍት ዌር ልማት፡-** እንደ ክልል የቢሮዉን አገልግሎት አሰጣጥ ለማዘመን የተመረጡ 7 ሲስተሞች (Land Mgt System፣ Construction licensee Mgt system፣ HRM Mgt System፣ Inventory Mgt System፣ Internal Letter Mgt System፣ Service delivery System እና Integrated Infrastructure System) እየለሙ ይገኛሉ፡፡

ከነዚህም ውስጥ 3ቱ ሲስተሞች (Inventory, Internal letter & Service delivery) ተጠናቀው ለሰራተኛዉ ስልጠና እየተሠጠ ይገኛል፡፡ እንዲሁም በባ/ዳር ዩኒቨርሲቲ የለማው Construction licensee Mgt system 100% ተጠናቆ ወደ ሙከራ ትግበራ ተሸጋግሯል፡፡

ሌላው በከተማ ደረጃ ደ/ብርሃን፣ ደሴ፣ ወልድያ፣ ባ/ዳር፣ እንጅባራና አዘና መሪ ማዘጋጃቤት የመሬት መረጃ ሶፍት ዌር በማስለማት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ በከተሞች የsmart city እሳቤን ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ባህርዳርና ደሴ የስማርት ካሜራ አገልግሎት ያስጀመሩ ሲሆን ጎንደርና ኮምቦልቻ ከተሞች በዝግጅት ላይ ናቸው፡፡

### 2.1.5. የተለያዩ የልማትና መልካም አስተዳደር ኢኒሸቲቮች አፈፃፀም

**የኢትዮ ኮደርስ ስልጠና ኢኒሸቲቭ፡-** ይህ ኢኒሸቲቭ በቢሯችን ትኩረት ተሰጥቶት እየተተገበረ ያለ ሲሆን በዚህ ዙሪያ ግንዛቤ ካገኙ ወንድ 145 ሴት 100 ድምር 245 ፈፃሚዎች መካከል ወንድ 83 ሴት 65 ድምር 148 ስልጠና አጠናቀው የምስክር ወረቀት አግኝተዋል፡፡ ሌሎች ደግሞ በስልጠና ላይ ናቸው፡፡

**የአንድ ከተማ አንድ ፕሮጀክት ኢኒሸቲቭ፡-** ይህ ኢኒሸቲቭ በክልሉ በሚገኙ ሁሉም ከተሞች የሚተገበር እና ቢሮው ክትትል እያደረገበት ያለ ሲሆን በ8ቱ ሪጆዮፖሊታን ከተሞች የሚገኙ 31 ክፍለ-ከተሞች፣ 57 ከተማ አስተዳደሮች፣ 93 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች፣ 46 ንዑስ መዘጋጃ ቤት ከተሞች እና 81 ታዳጊ ከተሞች በድምሩ 308 ከተሞችና ክፍለ-ከተሞች ፕሮጀክታቸውን የለዩ ሲሆን ፕሮጀክቶቹ የተለዩት የአካባቢው ማህበረሰብ ፍላጎት መሰረት አድርጎ ነው፡፡

ከተለዩት 308 ፕሮጀክት ውስጥ አዊ፣ ማዕ/ጎንደር፣ ደ/ወሎ፣ ሰ/ሸዋ፣ ደ/ብርሃን፣ ኮምቦልቻ፣ ጎንደር፣ ሰ/ጎጃም ወ.ዘ.ተ. 61 ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ሲሆን 104 ፕሮጀክቶች ከ50% በላይ አፈፃፀም ያላቸው ናቸው፡፡ 29 ፕሮጀክቶች ከ50% በታች አፈፃፀም

ያላቸው ሲሆን ቀሪ ፕሮጀክቶች በጨረታ ሂደት ላይ የሚገኙ ናቸው፡፡ በትግበራ ሂደት በሚገኙት 194 ፕሮጀክቶች ለ34,786 (ወንድ 16,491 እና ሴት 18,295) ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡

**የኮሪደር ልማት ኢኒሸቲቭ፡-** ይህ ኢኒሸቲቭ ከ2016 በጀት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ በክልላችን በሚገኙ 7 ሪጂዮ ፖሊታን ከተሞች እየተተገበረ የሚገኝ ሲሆን እስከዚህ ወር 6.5173 ኪ.ሜ አስፓልት መንገድ፣ 16.9 ኪ.ሜ የእግረኛ መንገድ፣ 15.84 ኪ.ሜ የሳይክል መንገድ፣ 6.73 ኪ.ሜ የጎርፍ ማስወገጃ መስመር፣ 33.64 ኪ.ሜ የመንገድ መብራት መስመር ዝርጋታ፣ 5 የጋራ መፀዳጃ ቤት፣ 5 አደባባይ እና 14 ካፍቴሪያዎች ተገንብተዋል፡፡ በዚህም ከህብረተሰቡ የተሰበሰበ 2,505,500,000 ብር እና በመንግስት የተበጀተ ብር 1,898,968,260.34 አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

በተያያዘም ለ36,000 ዜጎች የስራ እድል ተፈጥሯል፡፡ በተጨማሪ ም ዱርቤቴ ከተማ በመንግስትና በህብረተሰብ ተሳትፎ 29,731,647.48 ብር ወጪ በማድረግ 2.51 ኪ.ሜ የእግረኛ መንገድ እና 1.7 ኪ.ሜ መብራት ዝርጋታ ተከናውኗል፡፡ አዴት ከተማ በመንግስትና በህብረተሰብ ተሳትፎ 22,727,250.00 ብር ወጪ በማድረግ 1.5 ኪ.ሜ የአስፓት አካፋይ ከርብ ስቶን እና 1.42 ሄ/ር አረንጓዴ ልማት ተሰርቷል፡፡ ሐይቅ፣ ጊንባ፣ መርሳ፣ ቆቦ፣ አማኑኤል፣ ሞጣ፣ ሸዋ ሮቢት እና አለም ከተማ የኮሪደር ልማት ስራ ለመስራት የጀመሩና በዝግጅት ላይ ያሉ ከተሞች ናቸው፡፡

### 2.1.6. የአበይት ተግባራት እቅድ አፈፃፀም

#### 2.1.6.1. የከተሞች መልካም አስተዳደር አቅም ግንባታ ስራዎች

**የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድ ትግበራ፡-** በከተሞች መልካም አስተዳደርን ለማስፈን በመጀመሪያ ሁሉም የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶች ደረጃ ወጥቶላቸው ግልፅነት፣ ተጠያቂነትና የተገልጋዩን ዕርካታ በሚያረጋግጥ ሁኔታ ተፈፃሚ መሆን አለባቸው፡፡ ከዚህም አኳያ በከተሞች የሚሰጡ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎቶችን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲቻል 7 የተለያዩ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርዶች ተዘጋጅተው ወርደው ባለፉት ዓመታት 77ቱ ከተማ አስተዳደሮች ወደ ትግበራ የገቡ ሲሆን በበጀት አመቱ 14 መሪ ማዘጋጃ ቤት ከተሞች ወደ ሙከራ ትግበራ እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ በ8 (57.14%) ከተሞች (ደ/ጎንደር አርብ ገበያ፣ ሰ/ሸዋ ሰላድንጋይ፣ ዋግህምራ ጽጽቃ፣ አዊ ዞን አዘና እና ሰ/ወሎ ሮቢት፣ ሰ/ጎጃም ሊበን፣ ደ/ወሎ ተንታ አጅባር እና ኦሮሞ ቦራ መሪ ማዘጋጃቤት) ወደ ሙከራ ትግበራ ገብተዋል፡፡

**የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ የአፈፃፀም ምዘና፡-** የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ምዘና ለማካሄድ የሚያስችሉ ቁልፍ የምዘና መለኪያዎችን (Key Performance Indicators) በማዘጋጀት በ70 ከተሞች ምዘና ለማካሄድ ታቅዶ በዞኖች አማካኝነት በ24 ከተሞች በ4 የአገልግሎት አይነቶች ምዘና ተደርጎ የ24ቱ ከተሞች አማካይ ውጤት በመሬት ልማትና ማኔጅመንት 62.73%፣ በግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ 70.27%፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ 44.06% እና የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ 52.03% ሲሆን የ4ቱም አማካይ ውጤት 58.92% ሁኗል፡፡ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርድ በሚተገበርባቸው 89 ከተሞች የዜጎች ቻርተር እንዲዘጋጅ ለማድረግ ታቅዶ በ81 (91.01%) ከተሞች ተግባራዊ ማድረግ ተችሏል፡፡

**በማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ የተገልጋይ እርካታ ደረጃ፡-** የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርድ በሚተገበርባቸው 77 ከተማ አስተዳደሮች የተገልጋዩ ዕርካታ 70 በመቶ መድረሱ በጥናት ለማረጋገጥ ታቅዶ በዞን ደረጃ በ18 ከተሞች እና በ3 አገልግሎቶች ጥናት ተደርጎ በመሬት ልማትና ማኔጅመንት 61.12%፣ በግንባታ ፈቃድ አሰጣጥ 71.07% እና በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ 59.2% የተገልጋይ እርካታ የተመዘገበ ሲሆን ጥቅል አማካይ ውጤት 61.8% ነው፡፡ በቢሮ ደረጃ ባህርዳር፣ ደሴ እና ኮምቦልቻ በ2 አገልግሎቶች ላይ የተገልጋይ እርካታ ጥናት ተደርጎ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ አገልግሎት የተገልጋይ እርካታ 60.27% እና የህዝብ መጸዳጃና ገላ መታጠቢያ አገልግሎት የተገልጋይ እርካታ 59.64% ሁኗል፡፡ በአጠቃላይ የሁሉም አገልግሎቶች አማካይ 62.26% ነው፡፡

**የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥን ማዘመን፡-** በ14 ከተሞች /በዞን 1 ከተማ/ የመሬትና የኮንስትራክሽን ዘርፍ የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ በቴክኖሎጂ በመታገዝ እንዲዘምን /አውቶሜት/ዲጂታላይዝ ለማድረግ ታቅዶ በ12 ወሩ ደ/ብርሃን፣ ደሴ፣ ወልድያ፣ ባ/ዳር እና አዘና መሪ ማዘጋጃቤት ሶፍት ዌር በማስለማት አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ ሲሆን ኮምቦልቻ፣ እንጅባራ፣ ቻግኒ፣ ጎንደርና ሌሎች የተወሰኑ ከተሞች ተሞክሮ በመውሰድ ለመተግበር የዝግጅት ስራ ላይ ይገኛሉ፡፡

**የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች አቅርቦት፡-** የቄራ ግንባታ ባለባቸው 45 ከተማ አስተዳደሮች ደረጃውን የጠበቀ የቄራ አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ታቅዶ በ10 (20%) ከተሞች (ባ/ዳር 1,686፣ ደሴ 3,731፣ ደ/ማርቆስ 1,907፣ ኮምቦልቻ 2,760፣ ወልድያ 1040፣ በደ/ታቦር 909፣ ደ/ብርሃን 1,888፣ ሰ/ወሎ 580፣ ሰ/ሸዋ 60 እንዲሁም ኦሮሞ ብ/ዞን 3,764) በድምሩ 18,070 የቀንድ ከብት፣ የበግና ፍየል የቄራ እርድ አገልግሎት ተሰጥቷል፡፡

የእሳት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር አገልግሎት በሚገኝባቸው 8 ከተሞች አገልግሎቱ በአግባቡ እንዲሰጥ ድጋፍና ክትትል ለማድረግ ታቅዶ በ7 ከተሞች 171 (ባህር ዳር 89፣ ጎንደር 21፣ ደሴ 23፣ ኮምቦልቻ 15፣ ወልደያ 5፣ ደ/ብርሃን 16 እና ሰ/ወሎ 2) የእሳት አደጋዎች ተከስተው ሊደርስ ይችል የነበረውን አደጋ ለመቀነስ የተቻለ ሲሆን በተከሰቱ የእሳት አደጋዎች የደረሰው ጉዳት በገንዘብ ሲተመን 115,453,405.00 ብር ነው፡፡

በ77 ከተማ አስተዳደሮች ለባይተዋር ዜጎች ዘላቂ ማረፊያ አገልግሎት በአግባቡ እንዲሰጥ ለማድረግ ታቅዶ ባ/ዳር 124፣ ጎንደር 723፣ ደሴ 36፣ ደ/ማርቆስ 6፣ ኮምቦልቻ 78፣ ወልድያ 15፣ ደ/ታቦር 1፣ ደ/ብርሃን 15፣ ሰ/ወሎ 16፣ ሰ/ሸዋ 12 እና ዋግኽምራ 2 በድምሩ 1028 ቀባሪ ለሌላቸው ባይተዋር ዜጎች የቀብር አገልግሎት ተፈፅሟል፡፡ የገበያ ቦታ አቅርቦትን በተመለከተ ባህርዳር 4፣ ደሴ 2፣ ደ/ማርቆስ 2፣ ወልድያ 12፣ ደ/ታቦር 6፣ ደ/ብርሃን 2 እና ሰ/ወሎ 1 በድምሩ 29 የገበያ ቦታዎች ለምተው ለተጠቃሚ ተላልፈዋል፡፡

**የማዘጋጃቤታዊ ሰው ሃይል ስታንዳርዳይዜሽንና ምዘና፡-** በ16 ከተማ አስተዳደሮች በማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት መስኮች አገልግሎት ለመስጠት የተሰማሩ 1,000 (70% ሴቶች) አመራሮችንና ባለሙያዎችን በአሴት ማኔጅመንት፣ በቤቶች ማስተላለፍ፣ በቄራ፣ በእሳት አደጋ፣ በህብረተሰብ ተሳትፎ፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አሰባሰብ፣ በአረንጓዴ ልማት በማሰልጠን ብቃታቸው በምዘና ተረጋግጦ እውቅና እየተሰጠ ወደ ስራ እንዲሰማሩ ለማድረግ ታቅዶ በተለያየ የሙያ መስኮችና የሙያ ደረጃዎች ወንድ 109 ሴት 69 ድምር 178 ባለሙያዎች ተመዝነው ወንድ 74 ሴት 53 ድምር 127 የብቃት ምዘናውን ያለፉ ሲሆን ወንድ 35 ሴት 16 ድምር 51 ደግሞ ምዘናውን ያላለፉ ናቸው፡፡

**የህብረተሰብ ተሳትፎ፡-** በበጀት አመቱ በ683 ከተሞች በህብረተሰቡና በመንግስት በጋራ በሚከናወኑ የአካባቢ ልማት ስራዎችና ፕሮጀክቶች (የመንገድ ጠረጋና ግንባታ፣ የህዝብ መፀዳጃ ቤት ግንባታ፣ የተፋሰስና የዲች ግንባታ፣ የመብራትና የውሃ መስመር ዝርጋታ፣ የአካባቢ ማስዋብና አረንጓዴ ልማት እንዲሁም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራዎች ወዘተ) ላይ ህብረተሰቡ 15% በገንዘብ፣ 15% በቁሳቁስ፣ 20% በጉልበት በድምሩ 50% እንዲሳተፍ ለማድረግ ታቅዶ በጥሬ ገንዘብ 1,395,217,826.89 ብር፣ በጉልበት 1,110,728,120.8 ብር፣ በቁሳቁስ 714,000,316.71 ብር በድምሩ 3,219,946,264.40 ብር አስተዋጽኦ ተደርጓል፡፡ በመንግስት በኩልም 3,013,365,340.15 ብር ለአካባቢ ልማት ስራዎች ወጪ ተደርጓል፡፡ በጠቅላላው ለአካባቢ ልማት ስራዎች 6,233,311,604.55 ብር ወጪ የተደረገ ሲሆን የህዝብ ተሣትፎ አፈፃፀም 51.66% ነው፡፡

እንዲሁም በከተሞች በሚከናወኑ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ስራዎች ላይ የሴቶች እና የወጣቶች ተሳትፎ 50% እንዲደርስ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 2,654,095 ሴት 2,405,594 በድምሩ 5,059,689 የህብረተሰብ ክፍል (ከዚህም ውስጥ ወንድ 927,640 ሴት 1,029,039 በድምሩ 1,956,679 ወጣቶች) በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ የተሳተፉ ሲሆን የሴቶች ተሳትፎ ድርሻ በአማካይ 47.54% እና የወጣቶች ተሳትፎ ድርሻ በአማካይ 38.67% ነው፡፡ ይሁን እንጅ ሰ/ወሎ እና ምዕ/ጐንደር ዞኖች የመንግስት ወጪ ከህብረተሰብ ተሳትፎ መረጃው ጋር አብሮ አለመሰብሰቡ በጉድለት የሚታይ ነው፡፡

**የከተማ አገልግሎት ገቢ አሰባሰብ፡-** በ683 ከተሞች የገቢ ሀብታቸውን ውጤት በሚያመጣ መንገድ አሟጠው በመጠቀም የመሰረተ ልማት ወጭያቸውን 70% ከራሳቸው ማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ገቢ እንደሸፍኑ ለማድረግ ግብ ተይዞ በበጀት አመቱ በ606 መሪ፣ ንዑስና ታዳጊ ከተሞች 7,000,128,000.00 ብር ለመሰብሰብ ታቅዶ 1,223,082,047.28 ብር (17.47%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡ በገቢዎች ቢሮ በኩል ከ77 ከተማ አስተዳደሮች 15,500,000,000 ብር የአገልግሎት ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 5,957,730,351 ብር (38.44%) መሰብሰብ ተችሏል፡፡

በጠቅላላው በ683 ከተሞች 22,500,128,000 ብር የአገልግሎት ገቢ ለመሰብሰብ ታቅዶ 7,180,812,425 ብር የአገልግሎት ገቢ በመሰብሰብ የእቅዱን 31.91% መፈፀም ተችሏል፡፡ በክልሉ በሚገኙ ከተማ አስተዳደሮች፣ መሪ፣ ንዑስና ታዳጊ ከተሞች መሰብሰብ ካለባቸው 61 የገቢ አርእስቶች ውስጥ በአማካይ 45 የገቢ አርዕስቶችን ተደራሽ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ በአማካይ በ38 (84.44%) የገቢ አርዕስቶች የአገልግሎት ገቢ መሰብሰብ ተችሏል፡፡

ይሁን እንጅ የከተሞችን የገቢ አቅም ከማሳደግ አንጻር አሁን ባለው ወቅታዊ የፀጥታ ችግር ምክንያት በሁሉም የገቢ አርዕስቶች አሟጦ ባለመስብሰቡ ምክንያት የበጀት አመቱ የአገልግሎት ገቢ አሰባሰብ አፈፃፀማችን (31.91%) በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

**የፋይናንስ አጠቃቀም ኦዲት፡-** በበጀት አመቱ የከተሞችን ፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነት ለማሳደግና ብክነትን ለመከላከል 182 የማዘጋጃ ቤት ከተሞች ኦዲት ለማስደረግ ታቅዶ 82 (45.05%) ከተሞች ኦዲት አስደርገው 4,446,582.94 ብር ጉድለት የተገኘ ሲሆን ከተገኘው ጉድለት 1,455,654.67 (32.73%) ብር ተመላሽ ሆኗል፡፡ ከባለፋት ዓመታት ኦዲት የተገኘው 9,465,107.78 ብር የገንዘብ ጉድለት 100% ተመላሽ ለማድረግ ታቅዶ 3,592,433.12 (37.95%) ብር ተመላሽ ተደርጓል፡፡ በጠቅላላው በበጀት ዘመኑ እና ከባለፉት ዓመታት በኦዲት ከተገኘው 13,911,690.72 ብር የገንዘብ ጉድለት ውስጥ 5,048,087.97 (36.29%) ብር የተመለሰ ሲሆን ቀሪው ብር 8,863,602.75 (63.71%) ደግሞ ያልተመለሰ ነው፡፡ ይሁን እንጅ የከተሞችን ፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነት ለማሳደግና ብክነትን ለመከላከል እንዲቻል በወቅቱ ኦዲት አለማድረግ እና በኦዲት ወቅት በተገኙ ጉድለቶች ላይም ፈጥኖ የማስተካከያ እርምጃ አለመወሰድ በአብዛኛው ከተሞች የሚታይ ክፍተት ነው፡፡

### 2.1.6.2. የቤቶች ልማትና አስተዳደር ስራዎች

**የመኖሪያ ቤት ልማት፡-** በከተሞች እድገትና በተለያዩ ገፊ ምክያቶች እያደገ የመጣውን የመኖሪያ ቤት ፍላጎትና አቅርቦት አለመጣጣም ችግር /የመልካም አስተዳደር ችግር/ መፍታት ልዩ ትኩረት ማግኘት ያለበት ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም በበጀት አመቱ ወሩ ይህን ችግር ለማቃለል በተለያዩ የመኖሪያ ቤት ልማት አማራጮች 43,997 መኖሪያ ቤቶች ተገንብተው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ በተለያዩ የቤት ልማት ስትራቴጂዎች 44,269 (ከ100% በላይ) ቤቶች ተገንብተዋል፡፡

በበጀት አመቱ ከደረጃ በታች የሆኑ ቤቶች የማሻሻያ ልማት (ጥገና) ለማካሄድ የሚያስችል 10 ሚሊየን ብር በከተሞች እንዲበጀት በማድረግ 2,875 ቤቶች ደረጃቸው እንዲሻሻል ለማድረግ ታቅዶ 2,245 (78.08%) ቤቶች እድሳትና ጥገና የተደረገ ሲሆን ኮምቦልቻ ከተማ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በጎ አድራጊነት 12 ሚሊዮን ብር በጀት በመመደብና የደቀቁ የቀበሌ ቤቶችን መልሶ በማልማት ለ7 አባውራ የተሟላ ግንባታ ተከናውኖ ተመርቆ ርክክብ ተደርጓል፡፡ ሌላው 2,875 ቤቶች በመልሶ ማልማት እንዲገነቡ ለማድረግ ታቅዶ 597 (20.76%) ቤቶች እንዲገነቡ ማድረግ ተችሏል፡፡ በተለያዩ የቤት ልማት ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ለመሆን የተመዘገቡ ቤት ፈላጊዎች 10 ቢሊዮን ብር እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ 5.9 (59%) ቢሊዮን ብር ቆጥበዋል፡፡

የዝቅተኛ ነዋሪዎች ቤት ግንባታ ለማከናወን የሚያስችል 117.25 ሚሊዮን ብር ከዚህ ውስጥ 40% (46.9 ሚሊዮን ብር) በህ/ሰብ ተሳትፎ፣ 30% (35.18 ሚሊዮን ብር) ከተማው በሚመደብ በጀት እና 30% (35.18 ሚሊዮን ብር) መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ባለሀብቶችን በማሳተፍ ለማሰባሰብ ታቅዶ ከህብረተሰብ ተሳትፎ 104.182 ሚሊዮን ብር፣ ከተሞች ከራሳቸው በጀት 109.958 ሚሊዮን ብር እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንና ባለሀብቶችን በማሳተፍ 37.637 ሚሊዮን ብር በድምሩ 251.778 ሚሊዮን ብር (ከ100% በላይ) መሰብሰብ ተችሏል፡፡

በከተሞች በበጎ ፈቃድ አገልግሎት 500 አዲስ የአቅመ ደካማ የህብረተሰብ ክፍሎች ቤቶችን ለመገንባት እና 1,000 የአቅመ ደካማ ቤቶች ጥገና ለማድረግ ታቅዶ 690 (69%) የአቅመ ደካማ ቤቶች ጥገና/እድሳት የተደረገላቸው ሲሆን 229 (45.8%) የአቅመ ደካማ ቤቶችን በአዲስ መገንባት ተችሏል፡፡ በዚህ ተግባርም 22,852 (ወንድ 15,384 ሴት 7,468) በጎፈቃደኞች ተሳትፈዋል፡፡ እንዲሁም ከመንግስት፣ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከህ/ሰብ ተሳትፎ የተሰበሰበ 54,237,638.00 ብር አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡

**የመንግስት ቤት አስተዳደር:-** የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ያልወጣላቸውን 14,000 የመንግስት ቤቶች በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ታቅዶ 13,253 (94.66%) ቤቶች ካርታ ተሰርቶላቸዋል፡፡ በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ 18,000 ቤቶችን የኪራይ ዋጋ ለማሻሻል እንዲቻል የቤት ፍረጃ ለማድረግ ታቅዶ የ25,027 (ከ100% በላይ) ቤቶች ፍረጃ ማከናወን ተችሏል፡፡ ያለአግባብ የመንግስት ቤት የያዙ 300 ተጠቃሚዎች ላይ ርምጃ በመውሰድ በህጉ መሰረት ለሌሎች አዲስ ተከራዮች እንዲተላለፍ ለማድረግ ታቅዶ 319 (ከ100% በላይ) ያለአግባብ የተያዙ ቤቶችን በማስለቀቅ ለተጠቃሚዎች ማስተላለፍ ተችሏል፡፡

በመንግስት ቤቶች ላይ ህገወጥ ተግባር የሚፈጽሙ 400 ተከራዮችን በመለየት የማስተካከያ ርምጃ ለመውሰድ ታቀዶ 457 ህገወጥ ተግባር የተፈፀመባቸውን ቤቶች በመለየት 372 (93%) ቤቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ 36,000 ቤቶች የዉል እድሳት ለማድረግ ታቅዶ 43,266 (ከ100% በላይ) ቤቶች የውል እድሳት ማድረግ ተችሏል፡፡

በተጨማሪም የ16,000 መኖሪያ ቤቶችን መረጃ ለሶፍትዌሩ ግብዓት በሚሆን መንገድ ለማደራጀት እና 30,000 ቤቶችን ወደ ዘመናዊ የመረጃ ቋት (ሶፍትዌር) እንዲገቡ ለማድረግ ታቅዶ የ29,645 (ከ100% በላይ) ቤቶችን መረጃ ማደራጀት እና 28,404 (94.68%) ቤቶችን ወደ ዘመናዊ የመረጃ ቋት (ሶፍትዌር) ማስገባት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ እስከ አሁን በክልሉ ከሚገኙ 60,560 የመንግስት ቤቶች ውስጥ 39,559 (65.32%) ቤቶች ወደ ዘመናዊ የመረጃ ቋት (ሶፍትዌር) ገብተዋል፡፡

### 2.1.6.3. የከተማ መሰረተ- ልማት ስራዎች

#### የከተሞች ተቋማዊና መሠረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራም (UIIDP) አፈፃፀም

የ1ኛው ምዕራፍ የከተሞች ተቋማዊና መሠረተ ልማት ማፋፊያ ፕሮግራም (UIIDP - I) ተጠናቆ 2ኛውን ምዕራፍ ለመጀመር የፕሮግራሙ ሰነድ ዝግጅት ተጠናቆ የፕሮግራም በጀት ባለመለቀቁ የመንግስትን በጀት መነሻ በማድረግ የ2017 በጀት ዓመት ዕቅድ ታቅዶ ወደ ተግባር ተገብቷል፡፡

በዚህ መሠረት የUIIDPI ነባርና የUIIDPII እጩ ከተሞች ከክልሉ መንግስት የተመደበላቸውን በጀት እና የራሳቸውን ገቢ መነሻ በማድረግ ህብረተሰቡን ያሳተፈ የ2017-19 ተንከባላይ የ3 ዓመት መዋለንዋይ እቅድ እንዲያቅዱ ለማድረግ ታቅዶ ከነባር 32 የUIIDP ከተሞች ውስጥ 30 (93.75%) ከተሞች ዕቅዳቸውን በክልል ቢሮ ያስጸደቁ ሲሆን 2 (6.25%) ከተሞች (ደ/ማርቆስ እና ደባርቅ) ዕቅዳቸውን አዘጋጅተው በከተማ በም/ቤት ካጸደቁ በኋላ ረቂቅ (ድራፍት ሶፍት ኮፒ) ልከው ምላሽ ያገኙ ናቸው፡፡

**የ18 እጩ ከተሞች ዕቅድ ዝግጅት:-** 8 (44.44%) ከተሞች (መካነ እየሱስ፣ ሉማሜ፣ መካነሰላም፣ አጣየ፣ መሀልሜዳ፣ አለምከተማ፣ እብናት እና ወረኢሉ) ረቂቅ እቅድ አዘጋጅተው ለክልል ልከው አስተያየት የተሰጣቸው ሲሆን 3 (16.66%) ከተሞች (ዱርቤቴ፣ ቆላድባ እና መርጦ ለማሪያም) እቅድ በማዘጋጀት ሂደት ላይ ያሉ ናቸው፡፡ 4 (22.22%) ከተሞች (ግምጃ ቤት፣ ዳባት፣ ደንበጫ እና ፍላቂት) የእቅድ ዝግጅት ቡድን ያቋቋሙ ናቸው፡፡ 3 (16.66%) ከተሞች ደግሞ (ቲሊሊ፣ አምባ ጊዮርጊስ እና መተማ ዮሃንስ) ምንም እንቅስቃሴ የሌላቸው ናቸው፡፡

**ከ2016 በጀት ዓመት ወደ 2017 በጀት ዓመት የተንከባለሉ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም:-** በ15 ከተሞች በፕሮጀክት ባህሪያቸውና በአፈጻጸም አቅም ማነስ ምክንያት የተንከባለሉ 42 ፕሮጀክቶች የነበሩ ሲሆን የደ/ማርቆስ 2 ፕሮጀክቶች ውል በመቋረጡ ምክንያት

40 ፕሮጀክቶች የሚገኙ ሲሆን 24 (60%) ኘሮጀክቶች የተጠናቀቁ፤ 2 (5%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ80% በላይ የሆኑ፤ 6 (15%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50 - 80% የሆኑ፤ 8 (20%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50% በታች ነው፡፡

**በ2017 በጀት ዓመት ለሚከናወኑ አዲስ ፕሮጀክቶች የዲዛይን እና ስራ ዝርዝር ዝግጅት፡-** 32 (100%) ከተሞች የዲዛይንና የስራ ዝርዝር አዘጋጅተው ያጠናቀቁ ሲሆን 29 (90.62%) ከተሞች አዲስ ፕሮጀክቶች የሚሰሩበትን ቦታ ከ3ኛ ወገን ነፃ ያደረጉ ናቸው፡፡ እንዲሁም 3 (9.37%) ከተሞች (ፍ/ሰላም፣ ቡሬ እና ባ/ዳር) የተወሰኑ ፕሮጀክቶች የሚሰሩበትን ቦታ ከ3ኛ ወገን ነፃ ያደረጉ ናቸው፡፡

**የአካባቢና ማህበራዊ ደህንነት ተፅዕኖ ግምገማ፡-** በ32 ከተሞች የአካባቢና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናትና ልየታ ከሚያስፈልጋቸው 411 ፕሮጀክቶች ውስጥ 381 (92.7%) ፕሮጀክቶች ልየታ የተሰራላቸው ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 330 (86.61%) ፕሮጀክቶች የይሁንታ የምስክር ወረቀት አግኝተዋል፡፡ ሌላው 13 ፕሮጀክቶች መልሶ ማስፈር የሚያስፈልጋቸው ሲሆን 6 (46.15%) ፕሮጀክቶች መልሶ ማስፈር የተሰራላቸው ናቸው፡፡

**በ2017 በጀት ዓመት የታቀዱ አዲስ ፕሮጀክቶች አፈፃጸም፡-** በ32 ከተሞች በ2017 በጀት ዓመት ከታቀዱ 387 አዲስ ፕሮጀክቶች ውስጥ 135 (34.88%) ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ሲሆን 14 (3.61%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ80% በላይ ነው፡፡ 20 (5.16%) ፕሮጀክቶች ደግሞ አፈጻጸማቸው ከ50 - 80% ነው፡፡ እንዲሁም 19 (4.9%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50% በታች የሆኑ ወይም ወደ ስራ የገቡ ሲሆን 202 (52.19%) ፕሮጀክቶች ወደ ስራ ያልገቡ ናቸው፡፡

**በ2017 በጀት ዓመት የታቀዱ የጥገና ፕሮጀክቶች አፈፃጸም፡-** ከ287 የጥገና ፕሮጀክቶች ውስጥ 76 (26.48%) ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ሲሆን 17 (5.92%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ80% በላይ ነው፡፡ 10 (3.48%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50 - 80% ሲሆን 10 (3.48%) ፕሮጀክቶች አፈጻጸማቸው ከ50% በታች የሆነ እንዲሁም 175(60.97%) ፕሮጀክቶች ወደ ስራ ያልገቡ ናቸው፡፡

## በ (UIIDP) ፕሮግራም ባልታቀፉ ከተሞች የመሰረተ ልማት ፕሮጀክት አፈፃፀም

ከ2016 ወደ 2017 በጀት ዓመት ከዞሩ 102 ፕሮጀክቶች ውስጥ 100 ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ ሲሆን ያልተጠናቀቁ 2 ፕሮጀክቶች የሚገኙባቸው ዞኖች ሰ/ሸዋ 2 ጠጠር መንገድ በበጀት ምክንያት የቆሙ ናቸው፡፡ በ2017 በጀት ዓመት ከታቀዱ 664 ፕሮጀክቶች ውስጥ የአካባቢያዊ እና ማህበራዊ ተፅዕኖ ግምገማ የማያስፈልጋቸው 610 ፕሮጀክቶች ተለይተው የጥናት ሰነድ የተዘጋጀላቸው ሲሆን ከነዚህም መካከል 550 ፕሮጀክቶች የግንባታ ይሁንታ ፈቃድ ያገኙ ናቸው፡፡ ከነዚህ 664 ፕሮጀክቶች መካከል 571 (85.99%) ፕሮጀክቶች ተጠናቀዋል፡፡ 34 (5.12%) ፕሮጀክቶች አፈፃፀማቸው ከ50 - 80% የሆኑ፣ 41 (6.17%) ፕሮጀክቶች አፈፃፀማቸው ከ50% በታች የሆኑ እንዲሁም 18 (2.71%) ፕሮጀክቶች በጨረታ ሂደት ላይ ያሉ ናቸው፡፡

በበጀት አመቱ 80 ኪ.ሜ የጌጠኛ ድንጋይ (Cobblestone) ለመገንባት ታቅዶ 33.23 (41.54%) ኪ.ሜ፤ 350 ኪሜ ጠጠር መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 285.58 (81.59%) ኪ.ሜ፣ 411 ኪሜ ፐርጊያ መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 411.81 ((ከ100% በላይ)) ኪ.ሜ፤ 17 ኪ.ሜ አስፓልት መንገድ ለመገንባት ታቅዶ 11.37 (66.88%) ኪ.ሜ፤ 183 ኪ.ሜ የጎርፍ ማስወገጃና መከላከያ ለመገንባት ታቅዶ 101.88 (55.67%) ኪ.ሜ፣ 25 ከፍተኛና መለስተኛ ድልድይ ለመገንባት ታቅዶ 34 (ከ100% በላይ) ድልድይ የተገነባ ሲሆን 300 ስላብ ከልቨርት ለመገንባት ታቅዶ 325 (ከ100% በላይ) መገንባት ተችሏል፡፡

በበጀት አመቱ 423 ኪ.ሜ የከተማ ውስጥ የመንገድ ሙብራት መስመር ለመዘርጋት ታቅዶ 598.47 (ከ100% በላይ) ኪ.ሜ፤ 473 ኪ.ሜ የከተማ ውስጥ የውሃ መስመር ለመዘርጋት ታቅዶ 636.61 (ከ100% በላይ) ኪ.ሜ፤ 151 የውሃ ቦኖ ለመገንባት ታቅዶ 205 (ከ100% በላይ) ተገንብቷል፡፡ 1,500 ሼድ ለመገንባት ታቅዶ 1,343 (89.53%)፤ 135 የህዝብ መጸዳጃ ለመገንባት ታቅዶ 156 (ከ100% በላይ) ፤ 5 የወጣት ማዕከል ለመገንባት ታቅዶ 5 (100%)፤ 10 የገበያ ማዕከል ለመገንባት ታቅዶ 7 (70%) የተገነባ ሲሆን 36 ጊዜያዊ ቄራ ለመገንባት ዕቅድ 7 (19.44%) መገንባት ተችሏል፡፡ በጎንደር ከተማ 1 ዘመናዊ ቄራ ለመገንባት ታቅዶ

የግንባታው አፈፃፀም 85% ደርሷል፡፡ በደ/ብርሃን ከተማ 1 ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ለመገንባት ታቅዶ የግንባታው አፈፃፀም 99% ደርሷል፡፡

ሌላው በበጀት አመቱ 23 ኪ.ሜ ጌጠኛ መንገድ ለመጠገን ታቅዶ 26.62 (ከ100% በላይ) ኪ.ሜ፤ 428 ኪ.ሜ ጠጠር መንገድ ለመጠገን ታቅዶ 376.77 (88.03%) ኪ.ሜ ጥገና የተደረገ ሲሆን 6 ኪ.ሜ አስፓልት መንገድ ለመጠገን ታቅዶ 14.24 (ከ100% በላይ) ኪ.ሜ ጥገና ተደርጓል፡፡

**ሰንጠረዥ 2:- በፕሮግራሙ በታቀፉና ባልታቀፉ ከተሞች የተሰሩ መሰረተ ልማቶች አፈፃፀም**

| ተ.ቁ | የመሠረተ ልማት አይነቶች | መለኪያ | ዕቅድ | ክንውን | አፈፃፀም |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የተገነባ ጌጠኛ ድንጋይ መንገድ | በኪ/ሜ | 80 | 33.23 | 41.54 |
| 2 | የተገነባ ጠጠር መንገድ | በኪ/ሜ | 350 | 285.58 | 81.59 |
| 3 | የተገነባ ጥርጊያ መንገድ | በኪ/ሜ | 411 | 411.81 | 100.20 |
| 4 | የተገነባ የአስፓልት መንገድ | በኪ/ሜ | 17 | 11.37 | 66.88 |
| 5 | የጎርፍ ማስወገጃና መከላከያ ግንብ | በኪ/ሜ | 183 | 101.88 | 55.67 |
| 6 | የተገነባ ከፍተኛና መለስተኛ ድልድይ | በቁጥር | 25 | 34 | 136 |
| 7 | የተገነባ ስላብ ከልቨርት | በቁጥር | 300 | 325 | 108.33 |
| 8 | የተዘረጋ የመንገድ መብራት መስመር | በኪ/ሜ | 423 | 598.47 | 141.48 |
| 9 | የተዘረጋ የውሃ መስመር | በኪ/ሜ | 473 | 636.61 | 134.59 |
| 10 | የተገነባ የውሃ ቦኖ | በቁጥር | 151 | 205 | 135.76 |
| 11 | የተገነባ ደረጃውን የጠበቀ ሽድ | በቁጥር | 1500 | 1343 | 89.53 |
| 12 | የተገነባ የህዝብ መፀዳጃ ሽንት ቤት | በቁጥር | 135 | 156 | 115.56 |
| 13 | የተገነባ የወጣት ማዕከል | በቁጥር | 5 | 5 | 100 |
| 14 | የተገነባ የገባያ ማዕከል | በቁጥር | 10 | 7 | 70 |
| 15 | የተገነባ ደረጃውን ጊዜያዊ ቄራ | በቁጥር | 36 | 7 | 19.44 |
| 16 | የተጠገነ የጌጠኛ ድንጋይ መንገድ | በኪ..ሜ | 23 | 26.62 | 115.74 |
| 17 | የተጠገነ የጠጠር መንገድ | በኪ..ሜ | 428 | 376.77 | 88.03 |
| 18 | የተጠገነ የአስፋልት መንገድ | በኪ..ሜ | 6 | 14.24 | 237.33 |

## 2.1.6.4. የከተሞች ጽዳት፣ አረንጓዴ ልማትና ውበት ሥራዎች

**የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፡-** ከደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስርዓት ማሻሻያ ሥራዎች አንዱ የከተማውን ህዝብ ግንዛቤ በመፍጠር የጽዳት ቀን ወስኖ ሰፈሩንና አካባቢውን እንዲያጸዳ ማድረግ ነው፡፡ ከዚህም አኳያ በበጀት አመቱ በ500 ከተሞች የብዙሃን መገናኛ እና ህዝባዊ መድረኮችን በማመቻቸት እንዲሁም አጫጭር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን በመስጠት የሰፈር አደረጃጀቶችን እና የልማት ኮሚቴዎችን በማጠናከር 1,014,400 የከተማ ነዋሪዎችን በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ፣ አሰባሰብና አወጋገድ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠር በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ በቀጥታ ለማሳተፍ ታቅዶ በ401 ከተሞች ለወንድ 805,212 እና ለሴት 827,052 በድምሩ 1,632,264 (ከ100% በላይ) የህብረተሰብ ክፍሎችን ግንዛቤ በመፍጠር በፅዳት ስራው ላይ በቀጥታ እንዲሳተፉ ተደርጓል፡፡ በ683 ከተሞች 2,000 ኪ.ሜ መንገዶችን እና 2,000 ኪ.ሜ የውሃ ማፋሰሻ ቦዮችን በተከታታይነት የማጽዳት ስራ ለማከናወን ታቅዶ በ501 (73.35%) ከተሞች 2,685 ኪሜ (ከ100% በላይ) መንገዶችን እና 3,169 ኪሜ (ከ100% በላይ) ማፋሰሻ ቦዮችን የማጽዳት ስራ ተከናውኗል፡፡

በ683 ከተሞች የሚገኙ 800,000 የግለሰቦች መኖሪያ ቤቶች እና 32,500 ተቋማት ከ20 - 50 ሜትር ርቀት ግቢያቸውንና አካባቢያቸውን እንዲያፀዱ ለማድረግ ታቅዶ በ476 (69.69%) ከተሞችና ክ/ከተሞች የሚገኙ 543,056 (68%) ነዋሪዎች እና 56,877 (ከ100% በላይ) ተቋማት ተግባራዊ አድርገዋል፡፡

በ100 ከተሞች 600 አዲስ እና 1,993 ነባር የመንገድ ላይ ደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ቅርጫቶች ተቀምጠው ተገቢውን አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ ታቅዶ በ93 ከተሞች 623 (ከ100% በላይ) አዲስ የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ቅርጫቶች የተቀመጡ ሲሆን 1,981 ነባር የደረቅ ቆሻሻ ማስቀመጫ ቅርጫቶች ተገቢውን አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡

በ138 ከተሞች በደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ የተደራጁ 302 ነባር ማህበራትን በማጠናከር እና በ68 ከተሞች 132 አዲስ ማህበራትን በማደራጀት በከተሞች ከሚመነጨው ቆሻሻ 1,014,400 ሜትር ኪዩብ ቆሻሻ በተገቢው ቦታ ለማስወገድ ታቅዶ በ118 ከተሞች የሚገኙ 273 ነባር ማህበራትን በማጠናከር እና በ57 ከተሞች 78 አዲስ ማህበራትን በማደራጀት 1,680,150 (ከ100% በላይ) ሜትር ኪዩብ ቆሻሻ በተገቢው ቦታ እንዲወገድ ተደርጓል፡፡ በክልሉ በሚገኙ 104 ከተሞችና ክ/ከተሞች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት በመስራት የግንባታ ፍርስራሽ ቆሻሻ በአግባቡ ለማስወገድ ታቅዶ በ130 (ከ100% በላይ) ከተሞች ለማከናወን ተችሏል፡፡

በ30 አዲስ እና በ89 ነባር ከተሞች የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል ቀጣይነት ያለው እና የተመቻቸ የፋይናንስ ስርዓት ተግባራዊ ለማድረግ ታቅዶ በ29 (96.66%) ከተሞች በአዲስ የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ የፋይናንስ ስርዓት ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን 80 (89.88%) ነባር ከተሞች እንዲጠናከሩ ማድረግ ተችሏል፡፡ በ84 ከተሞች የሞዴል መንደር መመልመያ መስፈርትን መሰረት በማድረግ 168 ሞዴል መንደሮች ለመፍጠር ታቅዶ በ90 ከተሞች 144 (ከ100% በላይ) ሞዴል መንደሮችን መፍጠር ተችሏል፡፡

በ16 ከተሞች እንደ የከተሞች የእድገት ደረጃ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ በመስፈርቱ ከ3ኛ ወገን ነጻ እንዲሆን ለማድረግ ታቅዶ በ43 (ከ100% በላይ) ከተሞች ተከናውኗል፡፡ እንዲሁም በ200 ከተሞች ቋሚ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ የሌላቸውን በመለየት ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ ነጻ የሆነ ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እንዲዘጋጅ ለማድረግ ታቅዶ በ234 (ከ100% በላይ) ከተሞች ተዘጋጅቷል፡፡

**የአረንጓዴ ልማትና ውበት ሥራዎችን በተመለከተ፡-** ከሐምሌ 1/2016 ዓ/ም ጀምሮ የአረንጓዴ አሻራ ችግኝ ተከላ እቅድ በማዘጋጀት በ683 ከተሞች 880,000 የህብረተሰብ ክፍል በማሳተፍ በፓርኮች፣ በመንገድ አካፋዮችና በወንዞች ዳርቻ 25 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል 1,510 ሄ/ር አዲስ አረንጓዴ ቦታዎችን ለማልማት ታቅዶ በ320 (46.85%) ከተሞች ወንድ 654,532 ሴት 529,466 ድምሩ 1,183,998 (ከ100% በላይ) የህብረተሰብ ክፍሎችን በችግኝ ተከላ እና እንክብካቤ ዙሪያ ግንዛቤ በመፍጠርና በቀጥታ በማሳተፍ 24,525,337 (98.10%) ችግኞችን መትከል ተችሏል፡፡ በዚህ ችግኝ ተከላ መርሃ ግብርም 2,161 ሄ/ር (ከ100% በላይ) አረንጓዴ ቦታ ማልማት ተችሏል፡፡

በ300 ከተሞች የሚኖሩ 10,000 የመንግስትና የግል እንዲሁም የእምነት ተቋማት ግቢና አካባቢያቸውን በ50 ሜትር ራዲየስ እና 200,000 ነዋሪዎች መኖሪያ ቤታቸውን በ20 ሜትር ራድየስ በአረንጓዴ እንዲያለሙ ለማድረግ ታቅዶ በ348 (ከ100% በላይ) ከተሞች የሚገኙ 18,497 (ከ100% በላይ) ተቋማት እና 210,586 (ከ100% በላይ) ነዋሪዎች ግቢያቸውንና አካባቢያቸውን እንዲያለሙ ተደርጓል፡፡

በ32 ከተማ አስተዳደሮች 32 አዲስ አገልግሎት የሚሰጡ የመዝናኛ ፓርኮች በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲለሙ እና በ73 ከተሞች የሚገኙ 198 ነባር የመዝናኛ ፓርኮች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ በ29 ከተሞች 35 (ከ100% በላይ) አዲስ የመዝናኛ ፓርኮች የለሙ ሲሆን በ122 ከተሞች ለሚገኙ 198 (100%) ነባር የመዝናኛ ፓርኮች እንክብካቤ ተደርጓል፡፡

በ41 ከተሞች (የራሳቸው ችግኝ ጣቢያ የሌላቸው ከተሞችን በመለየት) 41 አዲስ ችግኝ ጣቢያዎች እንዲለሙ እና በ110 ከተሞች የሚገኙ 147 ነባር ችግኝ ጣቢያዎች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ በ36 ከተሞች 50 (ከ100% በላይ) አዲስ ችግኝ ጣቢያ የተቋቋመ ሲሆን በ178 ከተሞች ለሚገኙ 201 ነባር ችግኝ ጣቢያዎች እንክብካቤ ተደርጓል፡፡

በ300 ከተሞች በኘላን የተመላከቱ 1,500 አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲሰራላቸው ለማድረግ ታቅዶ በ172 ከተሞች የሚገኙ 2,039 (ከ100% በላይ) አረንጓዴ ቦታዎች የተለዩ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ለ1,241 (60.86%) አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ተሰርቶላቸዋል፡፡ እንዲሁም ለ6,446 ሄ/ር ነባር አረንጓዴ ቦታዎች እንክብካቤ ለማድረግ ታቅዶ 5,122 ሄ/ር (79.46%) አረንጓዴ ቦታዎች እንክብካቤ ማድረግ ተችሏል፡፡

### 2.1.6.5. የከተማ ሴፍቲ ኔትና ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ስራዎች

በከተሞች በኑሮ ደረጃቸው ከድህነት ወለል በታች የሆኑና የመስራት አቅም ያላቸው የከተማ ነዋሪዎች በህብረተሰብ ልማት ስራዎች ማለትም በከተማ አረንጓዴ ልማት፣ በተፋሰስ ልማት፣ በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ በከተማ ማህበራዊ መሰረተ ልማት ግንባታና ጥገና ስራዎች፣ በከተማ ግብርና እና በሌሎችም የቤተሰብ ኑሮ ማሻሻያ ስራዎች በማሳተፍና የስራ እድል በመፍጠር ገቢ እንዲያገኙና ከሚያገኙት ገቢም ቆጥበው ዘላቂነት ያለው የራሳቸውን ስራ እንዲሰሩ ለማስቻል እንዲሁም የመስራት አቅም የሌላቸውን የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ በማድረግ ምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እየተሰራ ያለ ሲሆን በክልላችን በፕሮግራሙ በታቀፉ 18 ከተሞች በዚህ በጀት ዓመት ወደ ፕሮግራሙ የተቀላቀሉ አዲስ የመንግስት መቀናጀ በጀት ተጠቃሚዎችን ጨምሮ 193,419 ዜጎችን በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ በማሳተፍ እና 36,672 ዜጎችን በቀጥታ ድጋፍ በጠቅላላው 230,091 ዜጎችን የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ግብ ተይዞ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ከዚህም አኳያ በ18ቱ ከተሞች ወደ ፕሮግራሙ የተቀላቀሉ የመንግስት መቀናጀ በጀት የአካባቢ ልማት ተጠቃሚዎችን ጨምሮ የከተሞችን ገጽታ ሊቀይሩ በሚችሉ በ5ቱ የማኅበረሰብ አቀፍ ሥራዎች 61,805 ሰሪ ኃይሎችን በማሳተፍ እና 663,329,339 ብር የጉልበት ክፍያ በማስተላለፍ ለ193,647 ዜጎችን የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ ታቅዶ በ18ቱ ከተሞች ወንድ 16,553 ሴት 43,580 በድምሩ 60,133 ሰሪ ሀይሎችን በማሳተፍ ወንድ 80,758 ሴት 106,819 በድምሩ 187,577 (96.86%) የቤተሰብ አባላትን ተጠቃሚ ማድረግ የተቻለ ሲሆን ለተጠቃሚዎች ወርሃዊ ክፍያ ብር 907,534,632 ማስተላለፍ ተችሏል፡፡ እንዲሁም የሴቶችን ተሳትፎ በተጠቃሚ 55.16% ማድረስ ተችሏል፡፡

በከተማ ምግብ ዋስትና ስትራቴጂና ፕሮግራሞች ዙሪያ ለ350,035 የከተማ አመራሮች፣ በየደረጃው ላሉ ለኮሚቴ አባላት፣ ለፕሮግራሙ ተጠቃሚዎችና ለባለድርሻ አካላት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራ ለመስራት ታቅዶ በ18 ከተሞች ወንድ 453,193 ሴት 557,508 በድምሩ ለ1,010,701 (ከ100% በላይ) የከተማ፣ ክፍለ ከተማና ቀበሌ አመራሮች፣ ባለድርሻ አካላት እንዲሁም ለከተማው ነዋሪ የሕብረተሰብ ክፍል ግንዛቤ ማስጨበጥ ተችሏል፡፡

በበጀት ዓመቱ ከድህነት ወለል በታች የሚኖሩና በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ ተሳታፊ የሆኑ 29,286 የቤተሰብ ሃላፊዎች በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም እንዲታቀፉ በማድረግ በዘላቂነት ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉ እና ለ13,725 የአካባቢ ልማት ተጠቃሚ ቤተሰቦች የማሕበራዊ አገልግሎት ተጠቃሚነት ትስስር ለመፍጠር ታቅዶ 50,279 ተጠቃሚዎች የጤና መድን ሽፋን፣ 1,934 ተጠቃሚዎች የትምህርት ቤት ምገባ፣ 6,188 ተጠቃሚዎች የትምህርት ቤት ቁሳቁስ (ደብተር እስክቢቶ ዩኒፎርም)፣ 3,333 ተጠቃሚዎች የጎልማሶች ትምህርት፣ 4,663 ተጠቃሚዎች በቴክኒክና ሙያ ትምህርት ቤት/ኮሌጅ የሙያ ትምህርት፣ 199 ተጠቃሚዎች የቀበሌ ቤት እንዲያገኙ ድጋፍ የተደረገላቸው፣ 172 ተጠቃሚዎች የመኖሪያ ቤት ዕድሳት የተደረገላቸው ሲሆን 32 ተጠቃሚዎች ነጻ የትራንስፖርት አገልግሎት አግኝተዋል፡፡ የኑሮ ማሻሻያ ድጋፎችን ያጠናቀቁ የመጀመሪያው ዙር ወንድ 2,946 ሴት 7,810 ድምር 10,756 የልማታዊ ሴፍቲኔት ተጠቃሚዎች በበጀት ዓመቱ ተመርቀው ከፕሮግራሙ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡

በዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም የታቀፉ 29,286 (60% ሴቶች) የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ ተጠቃሚዎች ተከታታይነት ያለው የምክርና ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 8,224 ሴት 20,797 ድምር 29,021 (99.1%) ተጠቃሚዎች (71.66% ሴቶች) የምክርና ድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ 29,286 (60% ሴቶች) የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ ተጠቃሚዎች የህይወት ክህሎት እና የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ስልጠና እንዲያገኙ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 5,439 ሴት 13,000 በድምሩ 18,439 (62.9%) ተጠቃሚዎች (70.50% ሴቶች) በህይወት ክህሎት እና የገንዘብ አያያዝና አጠቃቀም ላይ ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡

በበጀት ዓመቱ በ18 ከተሞች (UPSNJP) 39,234 እና በመንግስት መቀናጀ ፈንድ (GMF) 32,523 በአጠቃላይ 71,757 የኑሮ ማሻሻያ ተጠቃሚዎች በየወሩ ከሚያገኙት ክፍያ (20 በመቶ) ብር 118,518,881 እንዲቆጠቡ ታቅዶ ብር 116,764,964 (99%) እንዲቆጥቡ ማድረግ ተችሏል፡፡ እንዲሁም 19,905 የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ ተጠቃሚዎች በከተማ ግብርና እና ከከተማ ግብርና ውጪ ባሉ ተጨማሪ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ 83,667,546 ብር ገቢ እንዲያገኙ እና ከሚያገኙት ገቢ

44,470,773 ብር እንዲቆጥቡ ለማድረግ ታቅዶ ወንድ 4,010 ሴት 9,512 ድምር 13,522 የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ ተጠቃሚዎች በከተማ ግብርና እና ከከተማ ግብርና ውጪ ባሉ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ በመሰማራት 72,412,730 ብር ገቢ ያገኙ ሲሆን ከተገኘው ገቢ ውስጥም 30,325,552 ብር ተቆጥቧል፡፡

### 2.1.6.6. የባለብዙ ዘርፍ ስራዎች አፈፃፀም

በተቋሙ የሚወጡ ዕቅዶች የስርዓተ-ጾታ፣ የህፃናት፣ የወጣቶች፣ የአካል ጉዳተኞች፣ የአቅመ- ደካሞችና አረጋዊያን እና የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከል ...ወዘተ ጉዳዮች በተቋሙ እስከ ታችኛው መዋቅር ድረስ በወጡ እቅዶችና ሪፖርቶች እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ከዚህም አኳያ በዘርፉ በሚከናወኑ የአቅም ግንባታ ስራዎች (ሥልጠና እና ትምህርት) 35%፣ በልማት ስራዎች 50% ሴቶች ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማድረግ ታቅዶ በሥልጠና እና በትምህርት 62.86% ሴቶችን እንዲሁም በአካባቢ ልማት ስራዎች 46.95% ተጠቃሚ ማድረግ ተችሏል፡፡ በአመራርነት (በተቋም/የስራ ክፍል መሪነት) እና በውሳኔ ሰጭነት ደረጃ የሴቶች ተሳትፎ 35% እንዲደርስ ለማድረግ ታቅዶ 31.6% ማድረስ ተችሏል፡፡ በዓመቱ በተቋሙ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፈንድ ተጠቃሚ ለሆኑ 2 ግለሰቦች ተከታታይነት ያለው ድጋፍ ለማድረግ ታቅዶ በተቋሙ የኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፈንድ ተጠቃሚ ለሆኑ 2 ግለሰቦች 24,000.00 ብር የገንዘብ ድጋፍ ተደርጓል፡፡

### 2.1.6.7. የስራ እድል ፈጠራ ስራዎች

በፕላን ዝግጅትና ክለሳ፣ በኮንስትራክሽን፣ በመሰረተ ልማት፣ በቤቶች ልማት፣ በደረቅ ቆሻሻና አረንጓዴ ልማት ስራዎች ላይ ለ277,155 (የወጣቶች ድርሻ 194,009) ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል ለመፍጠር ታቅዶ ለ 328,295 (ከ100% በላይ) ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድል የተፈጠረ ሲሆን የወጣቶች ድርሻ 211,886 (ከ100% በላይ) ነው፡፡

### 2.1.6.8. ማደማደሚያ

በየደረጃው ያለው አመራርና ባለሙያ በበጀት አመቱ የታቀዱ ተግባራትን ቆጥሮ ይዞ በባለቤትነት ለመፈፀም አስቸጋሪ የነበረ ቢሆንም በዚህ አስቸጋሪ ወቅት ውስጥ ሁነንም በከፍተኛ አመራሩ የታገዘና የተቀናጀ ጠንካራ የድጋፍና ክትትል ስርዓት በመዘርጋት መደበኛ ዕቅዳችን ለመፈፀም በተደረገው ጥረት የተቋሙ የ2017 በጀት ዓመት እቅድ አፈፃፀም በዋና ዋና የውጤት አመላካቶችና መመዘኛ መስፈርቶች ተመዝኖ 89.04% (ከፍተኛ) መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በመሆኑም ይህን አፈፃፀም መነሻ በማድረግ በቀጣይ በጀት ዓመት የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ እንዲቻል በተለይም አገልግሎት አሰጣጣችን ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በመፍታት ሰብአዊነት የተላበሰ አገልግሎት የመስጠት ጉዳይ፤ በተቋሙ የሚታዩ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ትኩረት ሰጥቶ የመፍታት ጉዳይ፤ የተቋማችን አሰራር የማዘመንና ዲጂታይዝ የማድረግ እንዲሁም ምቹ የስራ አካባቢ የመፍጠር ስራችን በትኩረት ይዘን የምናከናውነው ይሆናል፡፡

ሌላው የከተማ አገልግሎት ገቢን በታቀደው ልክ የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም አሟጦ መሰብሰብ፣ በሁሉም የልማት ስራዎቻችን የህብረተሰቡን ተሳትፎና በባለቤትነት ማጠናከር፣ የመሰረተ ልማት ፕሮጀክቶችን እንደ የአካባቢው የሰላም ሁኔታ ልዩ ትኩረት በመስጠት ማጠናቀቅና ማስመረቅ፣ በክልላችን ዋና ዋና ከተሞች የተጀመረውን የኮሪደር ልማት በቅርበት ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ማጠናቀቅ፣ የአንድ ከተማ አንድ ፕረጀክት ኢኒሸቲቭ ትኩረት ሰጥቶ በመከታተል ወደ ውጤት መቀየር እንዲሁም በከተሞች በሚከናወኑ የልማት ስራዎች ሰፊ የስራ እድል መፍጠር ወዘተ የማጠናቀቂያ ምዕራፉ በትኩረት የምንፈፅማቸው ጉዳዮች ናቸው፡፡

## 2.2. የክልሉ የ25 ዓመት ፍኖተ ካርታና የ5 ዓመት የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ እንደ መነሻ

በክልላችን አሁን እየተመዘገበ ያለውን የኢኮኖሚ ዕድገት ለማፋጠን የ25 ዓመት ፍኖተ ካርታና የ5 ዓመት የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የተዘጋጀ ሲሆን የህግ የበላይነትን በማስከበር የክልሉን ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ፤ ክልላዊ ወንችን፣ እሴቶችንና ባህሎችን በማዳበር በስነ-ምግባር የታነፀና ሀገር ወዳድ ትውልድ ለማፍራት፤ ሃብትና ፈጠራን ለማሳደግ የሚያስችል እውቀት በማዳበር ኢኮኖሚው የሚፈልገውን የሰው ኃይል ለማፋራትና ምርታማነትንና ቅልጥፍናን ለማሳደግ እንዲሁም ጥራት ያለው ኢኮኖሚ በመገንባት የዜጎችን የህይወት ጥራት ለማሻሻል የሚያስችሉ ስትራቴጂክ ጉዳዮችንም ተለይተዋል፡፡

እስከ 2022 ዓ/ም የክልሉን ሰላምና ደህንነት የማረጋገጥ፣ በግብርና ምርት እምርታ ከመፍጠር ባለፈ መካከለኛ ገቢ የማስመዝገብ፣ በ2027 ዓ/ም በመሰረታዊ የኢንዱስትሪ ምርቶች የራሱን ፍላጎት የሚሸፍንና የተሳካ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር በማድረግ በትክክለኛ የብልፅግና ፍኖት ላይ እንዲገኝ የማድረግ እንዲሁም በ2042 ዓ/ም ደግሞ በዓለም በቴክኖሎጂ ተወዳዳሪ የሆነ የዘመናዊ ኢኮኖሚ ባለቤት እንዲሆን የማድረግ ርዕይ ተቀምጧል፡፡

የቴክኖሎጂ ተስተካካይነትን መሠረት ያደረገ ዘመናዊ ኢኮኖሚ መገንባት፣ ዘላቂ እና ዘመናዊ ከትመት ማረጋገጥ፣ የገጠር ማሕበራዊ ሽግግር ማረጋገጥ እና ሣይንሳዊ ዕውቀትን ከመልካም አገራዊ እሴቶች ጋር አጣጥሞ የሚዘልቅ ርትዕ ማሕበረሰብ መገንባት የክልሉ የቀጣዮቹ 25 ዓመታት የትኩረት አቅጣጫዎች ሲሆኑ የረጅም ጊዜ የትኩረት መስኮችም ዘመናዊ ኢንዱስትሪ (አምራች ኢንዱስትሪ፣ ዘመናዊ ግብርና፣ ዘመናዊ እና ግሎባላይዝድ አገልግሎት)፣ ቴክኖሎጂ፣ ሰብዓዊ ልማት፣ መሠረተ ልማት እንዲሁም ፍትህ እና መልካም አስተዳደር ናቸው።

የረጅም ዘመን ክልላዊ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግርን በተመለከተ የግብርና ዘርፍ ተጨማሪ እሴት ከክልላዊ ምርት ያለው ድርሻ በ2015 ዓ.ም ከተመዘገበው 52.5 በመቶ በ2042 ዓ.ም ወደ 17.1 በመቶ እንዲቀንስ የታቀደ ሲሆን የኢኮኖሚውን ፍጥነት እንዲመራ የሚፈለገው የአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ ተጨማሪ ዕሴት በ2015 ዓ.ም ከተመዘገበው 8.6 በመቶ በ2042 ዓ.ም ወደ 27.4 በመቶ እንዲያድግ፣ በተመሳሳይም የአገልግሎት ዘርፍ በ2015 ዓ.ም ከተመዘገበው 31.8 በመቶ በ2042 ዓ.ም ወደ 49 በመቶ እንዲያድግ ታቅዷል።

የመካከለኛ ዘመን የኢኮኖሚ እድገትን በተመለከተ ከ2018 እስከ 2022 ባሉት አምስት ዓመታት የክልሉ ኢኮኖሚ በአማካይ በ10.6 በመቶ እንዲያድግ ታቅዷል። ይህ የ10.6 በመቶ ዕድገት ምጣኔም በክልሉ በአሁኑ ወቅት ይኖራል ተብሎ የሚገመተውን የ21 በመቶ የድህነት ምጣኔ (ከድህነት ወለል በታች የሚኖር ሕዝብ መጠን በመቶኛ) በ2022 ወደ 15 በመቶ ለመቀነስ የሚያስችል ሲሆን ከ10.6 በመቶ እድገት ውስጥ 1.8 በመቶ ከሠራተኛ ኃይል እድገት፣ 4.8 በመቶ ከካፒታል እድገት እና ቀሪው 4 በመቶ ደግሞ ከምርታማነት ዕድገት እንደሚገኝ ታሳቢ ተደርጓል። እንዲሁም ከ10.6 በመቶ እድገት ውስጥ 4.6 በመቶ (የክልል አቀፍ ጥቅል ምርት ዕድገቱ 43.4 በመቶ) ከግብርና እና ተዛማጅ ዘርፎች፣ 2.8 በመቶ (የክልል አቀፍ ጥቅል ምርት ዕድገቱ 26.4 በመቶ) ከኢንዱስትሪ እና 3.2 በመቶ (የክልል አቀፍ ጥቅል ምርት ዕድገቱ 30.2 በመቶ) ከአገልግሎት ዘርፍ ተጨማሪ እሴት እንደሚገኝ ታሳቢ ተደርጓል።

**የከተማ ልማት እቅድ፡-** በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የአሻጋሪ ዕድገት እና የዘላቂ ልማት ዕቅድ (2018 – 2042) የከትመት ምጣኔ እድገት በ2013 ዓ.ም ከነበረበት 19.6% በ2022 ዓ.ም ወደ 27.8%፣ በ2027 ዓ.ም ወደ 33.9%፣ በ2032 ዓ.ም ወደ 41.2%፣ በ2037 ዓ.ም ወደ 50.1% እና በመጨረሻም በ2042 ዓ.ም ወደ 61.0% እንደሚደርስ ታቅዷል፡፡ የከተሞች ሕዝብ ቁጥር ዕድገትም ከነበረው በበለጠ ፍጥነት እየጨመረ ሂዶ በ2037 ዓ.ም ከክልሉ ጠቅላላ ህዝብ ውስጥ ከ50 በመቶ በላይ በከተሞች ሊኖር እንደሚችል የታቀደ ሲሆን አሁን በክልሉ የሚገኙ ዋና ዋና ከተሞች ወደ ፊት ሊሸከሙት የሚችሉት የሕዝብ ብዛት ምን ያህል መሆን እንዳለበት እንዲሁም በዙሪያቸው የዚህን ትውልድ አሻራ በሚያሳይ ሁኔታ በዘመናዊ መንገድ በመልሶ ማልማት የሚለሙበት አግባብ በእቅድ መመለስ እንዳለበት ተመላክቷል፡፡ የእያንዳንዱ ከተማ የኢኮኖሚ መሠረትም እንደ ሀብት መሠረታቸው በኢኮኖሚ ቀጠና መታቀድ እንዳለበት እንዲሁም ከተሞች በመሠረተ ልማት ተሳስረውና ተመጋግበው ቢጋራ መልማት እንዳለባቸው ፍኖተ ካርታው ያትታል።

ከዚህም አኳያ ከተሞች መዋቅራዊ ለውጡን ተከትሎ የሚመጣውን ክልላዊ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ዕድገት እና ፍላጎት በመሸከምና በማስቀጠል ረገድ የሚጫወቱት ሚና ከፍተኛ እንደሚሆን ይገመታል፡፡ ሌላው በክልላችን አስተማማኝ ሰላምና ደህንነት ለማረጋገጥ፣ ፖለቲካውን ለማዘመን፣ በኢኮኖሚ እራስን ለመቻልና ተወዳዳሪ ለመሆን፣ ተለዋዋጭ የሆነውን የዜጎች ፍላጎት ለማሟላት እና አሉታዊ ተፅዕኖችን ለመቀነስ እንዲቻል በከተሞች የሚኖሩ የዜጎችን ማኅበራዊ ንቃት፣ ጠያቂነት እና ተፅዕኖ ፈጣሪነት በመገንዘብ በጥብቅ ዲሲፕሊን መምራት ያስፈልጋል፡፡ ስለሆነም በክልሉ የ25 ዓመት ፍኖተ ካርታና የ5 ዓመት የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የተካተቱ ከተማን የሚመለከቱ ስትራቴጅክ ጉዳዮችንና ርዕይ እውን ለማድረግ ከተሞች የሚኖራቸውን የጎላ ሚና ለመምራት የሚያስችል ተቋማዊ የመካከለኛ ዘመን እቅድ ማዘጋጀት አስፈላጊ በመሆኑ እንደመነሻ ተወስዷል፡፡

## 2.3. የተቋሙ የ5 ዓመት (2018-2022) የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ እንደ መነሻ

ከክልሉ የ25 ዓመት ፍኖተ ካርታና የ5 ዓመት የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የተቀዳ የከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ የቀጣይ 5 ዓመት (2018-2022) የልማትና መልካም አስተዳደር እቅድ የተዘጋጀ ሲሆን የሚከተሉት ዋና ዋና አላማዎችና ግቦችም ታቅደዋል፡፡

ከዚህም አኳያ የእቅዱ አጠቃላይ ዓላማ ክትመታችን የገጠር ዕድገትን የሚያፋጥን፣ መሬትንና ሌላ ሃብትን በቁጠባ የሚጠቀም፣ እንቅስቃሴን የሚያፋጥን፣ ለአካባቢ ተጽዕኖ የማይበገር እንዲሆን እና ዘላቂ ልማትን በሚያቀናጅ ተዋረድ ባለው የተሟላ ፕላን መምራት ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎችም አገልግሎት አሰጣጡን ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ የተገልጋይ ዕርካታን ማሳደግ፤ የከተሞችን የፋይናንስ ልማት እና አስተዳደር ስርዓት በማሻሻልና በማዘመን የመሰረተ ልማትና አገልግሎት ወጫቸውን በራሳቸው ገቢ እንዲሸፍኑ ማድረግ፤ በክልሉ የተቀናጀ ዘላቂ የከተማ ፕላን እና የተመጣጠነ የአከታተም ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፤ በከተሞች የመኖሪያ ቤት አቅርቦትን ተደራሽ ማድረግና የአስተዳዳር ስርዓቱን ማሻሻል፤ በከተሞች ደረጃውን የጠበቀና የተቀናጀ መሠረተ-ልማትና አገልግሎት ማስፋፋት፤ በከተሞች የፅዳትና የአረንጓዴ ልማት አገልግሎትን በማስፋፋት ለሚከሰቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ አካባቢያዊና ኢኮሎጂዊ ተጽዕኖዎች የማይበገሩ ለኑሮ ምቹ እና ተስማሚ ማድረግ፤ በከተሞች አምራችነት ላይ ያተኮረ የምግብ ዋስትና ሴፍቲኔት ስርዓትን በመዘርጋትና በማስፋፋት ድህነትን መቀነስ፤ ተቋማዊ አደረጃጀትን በማስተካከልና እና አሰራርን በማዘመን የማይለዋወጡ የከተማ ልማት ተቋማትን መገንባት፤ በከተማ ልማቱ የሴቶችን፣ የህጻናትን፣ የወጣቶችን፣ የአረጋዊያን እና የአካል ጉዳተኞችን ልዩ ፍላጎት በማካተት እኩል ተሳታፊነትና ባለቤትነት ማረጋገጥ፤ በከተሞች ዘርፉ የሚፈጥረውን የሥራ ዕድል ምርታማ፣ ምቹና አዳጊ እንዲሆን በማድረግ በከተሞች ስራ አጥነትን መቀነስ የሚሉት ናቸው፡፡

የዘርፉ የ5 ዓመት እቅድ ዋና ዋና ግቦችም አገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻል የተገልጋዮችን የዕርካታ መጠን በ2017 ካለበት 61% በ2022 ወደ 85% ማሳደግ፤ በክልሉ የተመጣጠነ አከታተም ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ የክትመት ምጣኔን በ2017 ካለበት 22.77% በ2022 ወደ 27.8% ማሳደግ፤ በ85 ከተማ አስተዳደሮች ስማርት ሲቲን (smart city) ተግባራዊ ማድረግ፤ በከተሞች በተለያዩ አማራጮች 919,598 መኖሪያ ቤቶች እንዲገነቡ በማድረግ የቤት አቅርቦትን 2017 ከነበረበት 915,628 በ2022 ወደ 1,835,226 ማድረስ፤ በከተሞች የጠጠር፣ የጌጠኛ ድንጋይና የአስፓልት መንገድ መሰረተ ልማት ሽፋንን በ2016 ካለበት 10,263.18 ኪ.ሜ በ2022 ወደ 15,476.18 ኪ.ሜ ማሳደግ፤ በከተሞች የንፁህ መጠጥ ውሀ መሰረተ ልማት ሽፋንን በ2016 ካለበት 7,577.54 ኪ.ሜ በ2022 ወደ 11,687.54 ኪ.ሜ ማሳደግ፤ በከተሞች የመንገድ መብራት መሰረተ ልማት ሽፋንን በ2016 ካለበት 5,709.25 ኪ.ሜ በ2022 ወደ 8,503.25 ኪ.ሜ ማሳደግ፤ በከተሞች ዘመናዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ መሰረተ ልማትን በ2016 ካለበት 3 በ2022 ወደ 9 ማሳደግ፤ በ8 ሪጅዮፖሊታን ከተሞች ደረጃውን የጠበቀ የእሳት አደጋ መከላከያ ጣቢያ መገንባት፤ በ85 ከተማ አስተዳደሮች የኮሪደር ልማትን ተግባራዊ ማድረግ፤ በከተሞች የሚመነጨውን ቆሻሻ በመልሶ መጠቀምና ኡደት እንዲያልፍ በማድረግ እና ቀሪውን በተገቢው ቦታ በማስወገድ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሽፋንን 60 በመቶ ማድረስ፤ በከተሞች በፕላን ከተመላከቱ አረንጓዴ ቦታዎች መካከል 60 በመቶ የሚሆኑት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲለሙና ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ፤ በ18 ከተሞች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ 238,377 ዜጎችን የምግብ ዋስትና ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የከተማ ድህነትን መቀነስ፤ በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ባልታቀፉ 67 ከተማ አስተዳደሮች ከድህነት ወለል በታች ያሉ 33,500 ዜጎችን በተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ስራዎች በማሳተፍ ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉ ማድረግ፤ በዘርፉ እቅዶችና የህግ ማዕቀፎች የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በማካተት 50 ከመቶ ሴቶች እና 70 ከመቶ ወጣቶች ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም በከተሞች በሚከናወኑ የልማት ስራዎች ለ1,453,600 ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር የከተማ ሥራ አጥነትን መቀነስ የሚሉት ናቸው፡፡

ስለሆነም በተቋሙ የ5 ዓመት (2018-2022) የመካከለኛ ዘመን ዕቅድ የተካተቱ ስትራቴጅክ ጉዳዮችን እና የእቅዱን ርዕይ እውን ለማድረግ ከታቀዱ ዋና ዋና ግቦች መካከል ለ2018 በጀት ዓመት የታቀዱትን ዋና ዋና ግቦችና ተግባራት እንዳለ በመውሰድ በዚህ እቅድ ማካተት አስፈላጊ በመሆኑ እንደመነሻ ተወስዷል፡፡

## 3. የተቋሙ ርዕይ፣ ተልኮ፣ ዕሴት እና ስልጣንና ተግባር

**ርዕይ 2022፡-** *"በ2022 የክልሉ ከተሞች ምርታማ፣ ዘመናዊ የአገልግሎት፣ የግብይት እና የብልፅግና ማዕከላት ሁነው ማየት"*

**ተልዕኮ፡-** *በከተሞች ደረጃውን የጠበቀ የመኖሪያ ቤት፣ መሰረተ ልማትና አገልግሎት በማቅረብ የክልሉ ከተሞች የልማት፣ የፖለቲካና የመልካም አስተዳደር፣ የዘመናዊነትና የብልጽግና ማዕከላት እንዲሆኑ ማድረግ፣*

**ዕሴት፡-** *እንደ ክልል በቀጣዮቹ የዕቅድ ዓመታት በትኩረት ተይዘው ሊሰራባቸው የሚገባ ወጥ የሆኑ እሴቶች እንዲኖሩ የተመረጡ እሴቶችና መገለጫቸው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡*

- ✓ ***ሙያዊ ብቃት፡-*** *ያለ ክንፍ መብረር ያለ ሙያ መከበር አይቻልምና በሙያ ብቃት እንከበር፤*
- ✓ ***አገልጋይነት፡-*** *መታዘዝ ከመስዋዕትነት ይበልጣልና ምርጫችን አገልጋይነት ነው፤*
- ✓ ***ባህልን መጠበቅ፡-*** *የሰው ወርቅ አያደምቅምና በራሳችን ባህል እንደምቃለን፤ እንጠበቃለን፤*
- ✓ ***ሕግን ማክበር፡-*** *አበው በህግ አምላክ ብለው እንደተገዙለት እኛም ለህግ እንገዛለን፤*
- ✓ ***ሕዝባዊ ወገንተኝነት፡-*** *ከባህር የወጣ ዓሳ ላለመሆን ሕዝባዊ ወገንተኝነትን አጥብቀናል፤*
- ✓ ***አርበኝነት፡-*** *ከመቃብር በላይ ስም ይቆማልና አርበኝነት መለያችን ነው፤*
- ✓ ***ሀብትን በአግባቡና በቁጠባ መጠቀም፡-*** *ብልህ የዓመቱን፣ ሞኝ የእለቱን ነውና እንደ ብልሆች ሀብትን በአግባቡ ቆጥበን እንጠቀማለን፤*
- ✓ ***ለልዕለ ሐሳብ ተገዥነት፡-*** *መልካም ሃሳብ ወንዝ ያሻግራልና ልዕለ ሐሳብ ይገዛናል፤*
- ✓ ***ግብ ተኮር፡-*** *መድረሻውን ያላወቀ የትም ይገኛልና ትኩረታችን ለግቦቻችን ይሁን ብለናል፤*
- ✓ ***ብዝሐነትን መቀበል፡-*** *ልዩነታችን ውበት ነውና ብዝሐነትን ተቀብለናል፤*
- ✓ ***ምርምርና ፈጠራ፡-*** *ቋጠሮ መፍታት ከውሉ እንዲሉ ምርምርና ፈጠራን ለችግራችን መፍቻ አድርገናል፤*
- ✓ ***ቅንጅታዊ አሠራር፡-*** *ድር ቢያብር አንበሳ ያሥር ነውና ቅንጅታዊ አሠራር እሴታችን ነው፤*
- ✓ ***ግልፅነትና ተጠያቂነት፡-*** *አለባብሰው ቢያርሱ በአረም ይመለሱ በመሆኑ ግልፅነትና ተጠያቂነት እሴታችን ነው፡፡*

**ስልጣንና ተግባር፡-** በአዋጅ ቁጥር 300/2017 ለቢሮ የተሰጠው ስልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዋና የቢሮው ስልጣንና ተግባር የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ✓ *በክልሉ የሚገኙ ከተሞችን በበላይነት መምራትና መቆጣጠር፣*
- ✓ *የተመጣጠነ የከተሞች እድገት፣ ሽግግር እና የሕዝብ አሰፋፈር እንዲኖር በማድረግ የክልሉን የከትመት ምጣኔ ማፋጠን፣*
- ✓ *ዘመናዊ የከተማ ልማት ሥርዓትን እውን ለማድረግ በሚመለከተው አካል የተዘጋጀውን ፕላን በክልሉ በሚገኙ ከተሞች ማስተግበር፣*
- ✓ *የከተሞችን አገልግሎት አሰጣጥ በማሻሻል መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ፣*
- ✓ *የቤት ልማትና አቅርቦትን ማሳደግ እና የመንግስት ቤት አስተዳደርን ማሻሻል፣*
- ✓ *ለከተሞች የልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ሥርዓት መዘርጋትና ማጠናከር፣*
- ✓ *የከተሞችን ፕላን በጠበቀ መልኩ የመሠረተ ልማት አውታሮችን ማስፋፋት እና ተያያዥ አገልግሎትን ማቅረብ፣*
- ✓ *የተቀናጀ የከተማ መሠረተ ልማት መዋቅራዊ እና ማስተር ፕላን ማዘጋጀት፣ አፈፃፀሙን መከታተልና መቆጣጠር፣*
- ✓ *የክልሉ ከተሞች ውብ፣ ፅዱ እና አረንጓዴ እንዲሁም ለኑሮ እና ለሥራ ተስማሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣*
- ✓ *በከተሞች የምግብ ዋስትና እና የሥራ እድል ፈጠራ ፕሮግራምን ማስፋፋት…ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡*

# 4. የእቅዱ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች፣ የትኩረት መስኮችና የትኩረት አቅጣጫዎች

## 4.1. ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች

- ✓ የመልካም አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥ ችግር፣
- ✓ በክልሉ የተመጣጠነ የአከታተም ሥርዓት አለመኖር፣
- ✓ ዘላቂ የመኖሪያ ቤት አቅርቦትና አስተዳደር ችግር፣
- ✓ የመሰረተ ልማት አቅርቦትና አስተዳደር ችግር፣
- ✓ የጽዱ፣ ለኑሮ ተስማሚና የአረንጓዴ ከተሞች ግንባታ ውስንነት፣
- ✓ የከተማ ምግብ ዋስትና አለመረጋገጥ፣
- ✓ በከተሞች በቴክኖሎጅ የተደገፈ ዘመናዊ የመረጃና አሰራር ሥርዓት አለመኖር ናቸው፡፡

## 4.2. የእቅዱ የትኩረት መስኮች

1. የከተሞች መልካም አስተዳደርና አከታተም
2. ተደራሽ የቤት ልማትና አስተዳደር
3. የተቀናጀ ምርታማና ዘላቂ የከተማ መሠረተ ልማት
4. የከተማ ጽዳትና አረንጓዴ ልማት
5. የከተማ ምግብ ዋስትና እና ሴፍቲኔት
6. ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት እና ተቋም ግንባታ ናቸው፡፡

## 4.3. የእቅዱ የትኩረት አቅጣጫዎች

- የማዘጋጃ ቤት አገልግሎቶችን በማዘመን መልካም አስተዳደርን ማስፈን፤
- ከተሞችን እንደሀብት መሠረታቸው የልማት ማዕከላት ማድረግ፤
- በዜጎች ተሳትፎ የሚገነቡ ዘላቂ የመኖሪያ ቤቶችን ማስፋፋት፤
- የከተማ መሠረተ ልማትን ተደራሽነት፣ ፍትሃዊነት እና ጥራት ማረጋገጥ፤
- ከተሞች ለኑሮ ምቹ፣ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገሩ፣ ውብ፣ ጽዱና አረንጓዴ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- በከተሞች የምግብ ዋስትናን ጨምሮ ማሕበራዊ ጥበቃን ማረጋገጥ፤
- ዘመናዊ የከተማ መረጃ አያያዝ ሥርዓት ማስፈን፤
- አካታች የከተማ ልማት ሥርዓት መዘርጋት ናቸው፡፡

# ክፍል ሁለት

# ዓላማዎች፣ ግቦች የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት እና ማስፈፀሚያ ስልቶች

የከተሞችን እድገት ለማፋጠን በዘርፉ የተቀረፁ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጅዎችን እንዲሁም ፕሮግራሞችን ተግባራዊ በማድረግ ከተሞች ውብ፣ ፅዱ፣ አረንጓዴ፣ ለኑሮ እና ለስራ ምቹና ተስማሚ የሚሆኑበትን፣ የከተማ መሰረተ-ልማት የሚስፋፋበትን፣ የመኖሪያ ቤት ፈላጊዎች የቤት ባለቤት የሚሆኑበትን፣ ዜጎች የስራ እድል ተጠቃሚ የሚሆኑበትን እንዲሁም የዘርፉ አገልግሎት አሰጣጥ የሚሻሻልበትን ነባራዊ ሁኔታ ታሳቢ ያደረገ የ2018 በጀት ዓመት መሪ የልማት እና የመልካም አስተዳደር እቅድ አላማዎች፣ ግቦችና የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት በዚህ ክፍል እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 2.1 የእቅዱ ዓላማ፣ ግቦችና የሚከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት

**ጥቅል ዓላማ፡- ከተሞችን ምቹና ዘላቂ የመኖሪያ እና የሥራ አውዶች ማድረግ፣**

**የትኩረት መስክ 1፡- የከተሞች መልካም አስተዳደርና አከታተም**

**ግብ 1. በከተሞች የአገልግሎት አሰጣጥን በማሻሻልና በማዘመን የተገልጋዮችን የዕርካታ መጠን በ2017 ከነበረበት 61% በ2018 ወደ 65% ማሳደግ፣**

ተግባር 1. በ94 ከተሞች ከተሞች ሁሉም የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎቶች ስታንዳርድ ተዘጋጅቶላቸው እንዲተገበሩ ይደረጋል፡፡

ተግባር 2. በ94 ከተሞች ከተሞች ስታንዳርድ ለወጣላቸው የከተማ አገልግሎቶች የዜጎች ቻርተር እንዲዘጋጅ፣ ለዜጎች ተደራሽ እንዲሆንና አገልግሎቱም በስታንዳርዱ መሰረት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. በጽዳትና ውበት አገልግሎት የተሠማሩ 2,00 ባለሙያዎች ብቃታቸው በምዘና ተረጋግጦ ወደ ሥራ እንዲሰማሩ ይደረጋል፡፡

ተግባር 4. በ94 ከተሞች ደረጃውን የጠበቀ የእሣት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር፣ የዘላቂ ማረፊያ እንዲሁም የገበያ ቦታና የንግድ ቤቶች አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

ተግባር 5. በጥናት ላይ ተመስርቶ የህግ ማዕቀፎች 2 በአዲስ እንዲዘጋጁ እና 3 እንዲሻሻሉ ይደረጋል፡፡

**ግብ 2. በክልሉ የተመጣጠነ አከታተም ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ የከትመት ምጣኔን በ2017 ካለበት 22.77% በ2018 ወደ 23.45% ማሳደግ፣**

ተግባር 1. በክልሉ ከሚገኙ 728 ነባር ከተሞች መካከል በአቅራቢያቸው ወዳለ ትልቅ ከተማ ሊዋሀዱ የሚችሉ 10 ከተሞችን በጥናት በመለየት እንዲዋሀዱ ይደረጋል፡፡

ተግባር 2. በጥናት ላይ ተመስርቶ የከተማነት መስፈትቱን የሚያሟሉ 10 የገጠር የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት የከተማነት እውቅና እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. ከተሞችን በፈርጅ የማደራጀት ስርዓቱን በማጠናከር 5 ከተሞች ወደ ከተማ አስተዳደር፣ 9 ከተሞች ወደ መሪ ማዘጋጃ እና 19 ከተሞች ወደ ንዑስ ማዘጋጃ የፈርጅ ለውጥ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ተግባር 4. የከተማ ልማትን ከገጠር ልማት ጋር የሚያቀናጅ 1 የአሰራር ስርዓት እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

ተግባር 5. በክልሉ ያለውን የከተማ የህዝብ አሰፋፈር እና የአከታተም ስርዓት በተመለከተ 1 ጥናት እንዲጠና ይደረጋል፡፡

**ግብ 3. በክልሉ ለሚገኙ 728 ከተሞች የልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ስርዓት እንዲዘረጋ ማድረግ**

ተግባር 1. በክልሉ ከተሞች የልማት ፋይናንስ ማጠናከሪያ ሰርዓት ላይ የአሰራር ማሻሻያ ለማድረግ ግብዓት የሚሆን 1 ጥናት እንዲጠና ይደረጋል፡፡

ተግባር 2. የህበረተሰብ ተሳትፎ የአሰራር መመሪያ በማዘጋጀት ለዞኖችና ከተሞች እንዲወርድ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. መንግስታዊ ከሆኑ እና መንግስተዊ ካልሆኑ ድርጅቶች እና ከሌሎች ድጋፍ ሰጭ አካላት ጋር የተጠናከረ የስራ ግንኙነት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ተግባር 4. በተመረጡ 5 የክልሉ ከተሞች ከሌሎች ሀገሮች ከተሞች ጋር እህትማማች እንዲፈጥሩ እና የልማት አቅማቸው እንዲጎለብት ይደረጋል፡፡

**ግብ 4. በ8 ከተማ አስተዳደሮች ስማርት ሲቲን (smart city) ተግባራዊ ማድረግ፣**

ተግባር 1. ስማርት ሲቲ በሚተገበርባቸው 8 ከተማ አስተዳደሮች ወደ ትግበራ ከመገባቱ በፊት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ትብብር እና ቅንጅት ይፈጠራል፡፡

ተግባር 2. በ8 ከተማ አስተዳደሮች የሚስተዋሉ ተግዳሮቶችን፣ የቀጣይ የእድገት መዳረሻዎችን፣ በከተማው የሚገኘን የመሰረተ ልማት ሁኔታ እና ፀጋ/ሀብት በጥልቀት በመዳሰስ እና ግልጽ ግብ በመንደፍ የስማርት ሲቲ እቅድ እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. በ8 ከተማ አስተዳደሮች ስማርት ቴክኖሎጂ ወሳኝ አወንታዊ ተጽዕኖ የሚያመጣባቸውን እንደ ትራንስፖርት፣ ከተማ ፕላን፣ ትምህርት፣ ጤና፣ ፀጥታ እና የህዝብ ደህንነት፣ አስተዳደር፣ የአካባቢ ዘላቂነት፣ ኢነርጅ እና መሰረተ ልማት ዘርፎችን ወዘተ በመለየት የትግበራ ቅደም ተከተል እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

ተግባር 4. በ8 ከተማ አስተዳደሮች ከባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ አጋርነት በመመስረት እንዲሁም ተጨማሪ ፈንድ በማፈላለግና ራሱን የቻለ በቂ በጀት በመመደብ በቅደም ተከተሉ መሰረት ፍላግሽፕ ፕሮጀክት ሁኖ እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

ተግባር 5. በ8 ከተማ አስተዳደሮች በትግበራ ሂደት ከሚያጋጥሙ ችግሮችንና መልካም ተሞክሮዎች ትምህርት በመውሰድና ቀጣይነት ያለው የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት የፕሮጀክቱ ዘላቂነት እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

## የትኩረት መስክ 2፡- ተደራሽ የቤት ልማትና አስተዳደር

### ግብ 5. በከተሞች በተለያዩ አማራጮች 92,675 መኖሪያ ቤቶች እንዲገነቡ ማድረግ፣

ተግባር 1. በከተሞች በሪል ስቴት 5,946 ቤቶች፣ በህብረት ሥራ ማህበራት 63,671 ቤቶች፣ በግለሰቦች 21,558 ቤቶች፣ ለዝቅተኛ ነዋሪዎች 1,500 ቤቶች በድምሩ 92,675 ቤቶች እንዲገነቡ ይደረጋል፡፡

ተግባር 2. በከተሞች ያሉትን የተጎሳቆሉ የመኖሪያ ቤቶች ስርጭት አሳታፊ የሆነ የመልሶ ማልማት ፕሮግራም ተግባራዊ በማድረግ እንዲቀንሱ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ኩባንያዎችን በማሣተፍ የተሻሻሉ፣ ወጪ ቆጣቢ እናፈጣን የግንባታ ዲዛይኖችና ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

ተግባር 4. አዳዲስ የግንባታ ፕሮጄክቶች ማኔጅመንት ቴክኖሎጂዎችን በመፍጠር ወይም በማላመድ እንዲሁም ለአካባቢ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም በማስፋፋት በቤቶች ግንባታ ስራ ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

### ግብ 6. በበጀት ዓመቱ 35 ጥራት ያላቸው የቤት አልሚዎችን ወደ መስኩ በማስገባት ቤት ማልማት አንድ አዋጭ ኢንዱስትሪ እንዲሆን ማድረግ፣

ተግባር 1. በሪል ስቴት ቤት ልማት ለመሳተፍ ፕሮጀክት ቀርፀው ውሳኔ ያገኙ 18 አልሚዎችን ወደ ቤት ማልማት እንዲገቡ ይደረጋል፡፡

ተግባር 2. ከዚህ በፊት በሪል ስቴት ቤት ልማት የተሰማሩ 17 አልሚዎችን የጀመሯቸውን ቤቶች እንዲያጠናቅቁ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. ግለሰቦች ከቤት ግንባታ ይልቅ በሚያዋጣቸው መስክ እንዲተጉ በማድረግ የሥራ ክፍፍልን እና ስልጠትን ወይም ቅልጥፍናን እና ምርታማነትን ማበረታታት፤

### ግብ 7. የቤት አስተዳዳር ስርዓትን በማዘመን 100,000 ቤቶች በዘመናዊ መረጃ ቋት እንዲደራጁ ማድረግ፣

ተግባር 1. በከተሞች 20,879 የመንግስት ቤቶች፣ 20,093 የኮንደምንየም ቤቶች እና 59,028 የግለሰብ ቤቶች 100 ፐርሰንት በዘመናዊ መረጃ ቋት እንዲደራጁ ይደረጋል፡፡

ተግባር 2. በከተሞች በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ 56,292 ቤቶችን በየዓመቱ የውል እድሳት በማድረግ፣ 3,000 ቤቶችን የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲያገኙ በማድረግ፣ 5,000 ቤቶችን የኪራይ ዋጋ እንዲሻሻል በማድረግ እና 1,200 ያለአግባብ የተያዙ ቤቶችን ስርዓት በማስያዝ የመንግስት የቤቶች አስተዳዳር በህግ አግባብ እንዲመራ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. በከተሞች በመንግስት ባለቤትነት የሚከራዩ 1,200 ቤቶችን ጥገና እና ዕድሳት በማድረግ ደረጃቸው እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡

## የትኩረት መስክ 3፡- የተቀናጀ ምርታማና ዘላቂ የከተማ መሠረተ ልማት

### ግብ 8. በከተሞች የመንገድ መሰረተ ልማት ግንባታ ሽፋንን በ2016 ካለበት 18,535 ኪ.ሜ በ2018 ወደ 20,389 ኪ.ሜ ማሳደግ፣

ተግባር 1. በእቅድ ዘመኑ 123 ኪ.ሜ የኮብል ስቶን መንገድ፣ 714 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ፣ 1,000 ኪ.ሜ ጥርጊያ መንገድ፣ 17 ኪ.ሜ የአስፓልት መንገድ ግንባታ ይከናወናል፡፡

ተግባር 2. በእቅድ ዘመኑ 199 ኪ.ሜ የጎርፍ መከላከያ ግንብ፣ በቁጥር 18 ከፍተኛና መለስተኛ ድልድይ፣ በቁጥር 143 የስላብ ከልቨርት ግንባታ ይከናወናል፡፡

**ግብ 9. በከተሞች የንፁህ መጠጥ ውሀ መሰረተ ልማት ዝርጋታ ሽፋንን በ2016 ካለበት 6,731 ኪ.ሜ በ2018 ወደ 7,404 ኪ.ሜ ማሳደግ፣**

ተግባር 1. በእቅድ ዘመኑ 673 ኪ.ሜ የመጠጥ ውሃ፣ 200 ኪ.ሜ ለአረንጓዴ ልማት የሚውል የውሃ መሰረተ ልማት ዝርጋታ እና በቁጥር 162 የውሃ ቦኖ እንዲገነባ ይደረጋል፡፡

**ግብ 10. በከተሞች የመንገድ መብራት መሰረተ ልማት ዝርጋታ ሽፋንን በ2016 ካለበት 4,577 ኪ.ሜ በ2018 ወደ 5,035 ኪ.ሜ ማሳደግ፣**

ተግባር 1. በእቅድ ዘመኑ 458 ኪ.ሜ የመንገድ መብራት አቅርቦት መሰረተ ልማት ዝርጋታ ይከናወናል፡፡

**ግብ 11. በከተሞች ደረጃውን የጠበቀ የገበያ ማዕከላት ግንባታ በቁጥር በ2016 ከነበረበት 132 በ2018 ወደ 147 ማሳደግ፣**

ተግባር 1. በተመረጡ በከተማ አስተዳደሮች 15 የገበያ ማዕከላት ግንባታ እንዲከናወንና አስፈላጊው መሰረተ ልማት እንዲሟላ ይደረጋል፡፡

**ግብ 12. በከተሞች ደረጃውን የጠበቀ የመስሪያና የመሸጫ ሸድ ግንባታ በቁጥር በ2016 ከነበረበት 20,324 በ2018 ወደ 22,356 ማድረስ፣**

ተግባር 1. በ85 ከተማ አስተዳደሮች 2,032 የመስሪያና የመሸጫ ሸድ ግንባታና አስፈላጊ መሰረተ ልማቶች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡

**ግብ 13. በ8 ከተሞች የኮሪደር ልማት ማስፋፋት እንዲሁም በተመረጡ ከተሞች 15 የወጣቶች ማዕከላትን እና 128 የጋራ መፀዳጃ ቤት መገንባት፣**

ተግባር 1. በ8 ከተማ አስተዳደሮች የተጀመሩ የኮሪደር ልማቶችን በስፋት ማስቀጠል፣

ተግባር 2. በተመረጡ ከተሞች 15 የወጣቶች ማዕከላትን መገንባት፣

ተግባር 3. በተመረጡ ከተሞች 128 የጋራ መፀዳጃ ቤት መሰረተ ልማት መገንባት፣

**ግብ 14. በእቅድ ዘመኑ 8 ኪ.ሜ የኮብል ስቶን መንገድ፣ 504 ኪ.ሜ የጠጠር መንገድ እና 2 ኪ.ሜ የአስፓልት መንገድ ጥገና ማድረግ፣**

**ግብ 15. በ85 ከተማ አስተዳደሮች የተገነቡ መሰረተ ልማቶችን መረጃ በዘመናዊ የመረጃ አያያዝ ስርዓት 100% እንዲደራጅ ማድረግ፣**

## የትኩረት መስክ 4፡- የከተማ ጽዳትና አረንጓዴ ልማት

**ግብ 16. በ728 ከተሞች በደረቅ ቆሻሻ ኢያያዝና አወጋገድ እና በአረንጓዴ ልማት ዙሪያ ለ1 ሚሊዮን የህ/ሰብ ክፍሎች ግንዛቤ በመፍጠር በጽዳትና አረንጓዴ ልማት ስራ ላይ እንዲሳተፍ ማድረግ፣**

ተግባር 1. በ728 ከተሞች በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ ስራ ላይ ነዋሪው በቀጥታ ተሳታፊ እንዲሆን የሚያስችል የህዝብ ንቅናቄ ሰነድ በማዘጋጀትና ለ1 ሚሊዮን (50% ሴቶች) የከተማ ነዋሪ የህብረተሰብ ክፍል ግንዛቤ በመፍጠር ወርሃዊ የጽዳት ቀን ወስኖ እንዲሳተፍ ይደረጋል፡፡

ተግባር 2. በ728 ከተሞች የሚሆኑ የሚኖሩ 400,000 (20 በመቶ) ግለሰቦችና እና 60,000 ተቋማት ከ20 - 50 ሜትር ርቀት ግቢያቸውንና አካባቢያቸውን እንዲያጸዱ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. በ728 ከተሞች ለ1 ሚሊዮን (50% ሴቶች) የህብረተሰብ ክፍል በአረንጓዴ አሻራ ትግኝ ተከላ ላይ በማሳተፍ 16 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል 2,000 ሄ/ር አዲስ አረንጓዴ ቦታዎች እንዲለሙ ይደረጋል፡፡

ተግባር 4. በ200 ከተሞች የሚኖሩ 20,000 የመንግስትና የግል እንዲሁም የእምነት ተቋማት ግቢና አካባቢያቸውን በ50 ሜትር ራዲየስ እና 200,000 የሚሆኑ ከተማ ነዋሪዎች መኖሪያ ቤታቸውን በ20 ሜትር ራድየስ በአረንጓዴ እንዲያለሙ ይደረጋል፡፡

**ግብ 17. በ100 ከተሞች የሚመነጨውን ቆሻሻ በመልሶ መጠቀምና ኡደት እንዲያልፍ በማድረግ እና ቀሪውን 1 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ ደረቅ ቆሻሻ በተገቢው ቦታ በማስወገድ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሽፋንን በ2017 ከነበረበት 40 በመቶ በ2018 ወደ 60 በመቶ ማድረስ፣**

ተግባር 1. በ30 ከተሞች ደረቅ ቆሻሻ የሚያስወግዱ 30 አዲስ ማህበራትን በማደራጀት ቆሻሻን በአግባቡ የማስወገድ ስራ ይሰራል፡፡

ተግባር 2. በ15 ከተሞች አዲስ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ገቢና የፋናንስ አቅርቦት ስርዓት ይዘረጋል፡፡

ተግባር 3. በ100 ከተሞች ከሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ውስጥ 1 ሚሊዮን ሜትር ኪዩብ የሚሆነው በተገቢው ቦታ እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

**ግብ 18. በ200 ከተሞች በፕላን ከተመላከቱ አረንጓዴ ቦታዎች መካከል 60 በመቶ የሚሆኑት ደረጃቸውን ጠብቀው እንዲለሙና ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ፣**

ተግባር 1. በ200 ከተሞች በፕላን የተመላከቱ አረንጓዴ ቦታዎችን በመለየት 1,000 አረንጓዴ ቦታዎች የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ እንዲያገኙ እና በስታንዳርድና ዲዛይን እንዲለሙ ይደረጋል፡፡

ተግባር 2. በ85 ከተሞች 85 አዲስ አገልግሎት የሚሰጡ የመዝናኛ ፓርኮች በስታንዳርድ ዲዛይን እንዲለሙ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. የራሳቸው ችግኝ ጣቢያ የሌላቸው ከተሞችን በመለየት 20 አዲስ ችግኝ ጣቢያዎች እንዲለሙ ይደረጋል፡፡

ተግባር 4. በ200 ከተሞች የለሙ 5,000 ሄ/ር ነባር አረንጓዴ ቦታዎች ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥ ተገቢው እንክብካቤ ይደረጋል፡፡

## የትኩረት መስክ 5፡- የከተማ ምግብ ዋስትና እና ሴፍቲኔት

**ግብ 19. በ18 ከተሞች በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ 195,832 ዜጎችን የምግብ ዋስትና ስርዓት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ የከተማ ድህነትን መቀነስ፣**

ተግባር 1. የከተሞች ሴፍቲኔትና የሥራ ፕሮጀክት ተጠቃሚ ከተሞች ለ540,507 ሕዝብ የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ ይሰራል::

ተግባር 2. በከተሞች የሚገኙ የመስራት አቅም የሌላቸዉና ለማህበራዊ ችግር ለተጋለጡ 36,672 ዜጎች (የአካል ጉዳተኞች፣ አረጋውያን፣ የአዕምሮ ህሙማን እና ህጻናት) የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. በ18 ከተሞች 159,160 የመስራት አቅም ያላቸውና ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ ዜጎች የከተሞችን ገጽታ ሊቀይሩ በሚችሉ የማህበረሰብ አቀፍ ስራዎች በማሳተፍ የምግብ ዋስትናቸው ይረጋገጣል፡፡

**ግብ 20. በአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ ተሳታፊ የሆኑ 51,125 የቤተሰብ ሃላፊዎች በዘላቂነት ኑሮቸውን በሚያሻሽሉ የሥራ አማራጮች እንዲሳተፉ ማድረግ፣**

ተግባር 1. የአካባቢ ልማት ተጠቃሚዎች ገቢ በሚያስገኝ ሥራ ላይ ተሰማርተው በዘላቂነት ኑሮአቸውን እንዲያሻሽሉና ተነሳሽነታቸው እንዲጨምር ከሚያገኙት ወርሃዊ ክፍያ 20% እንዲቆጥቡ ይደረጋል፡፡

ተግባር 2. የስራ ዕድል መፍጠሪያ አማራጮችን በዳሰሳ ጥናት በመለየት ተጨማሪ ገቢ በሚያስገኙ የሥራ ዕድል መፍጠሪያ ዘርፎች 51,125 የቤተሰብ ተጠሪዎች እንዲሰማሩ ይደረጋል፡፡

**ግብ 21. በ18 ከተሞች የሚገኙ 195,832 የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚዎች የማህበራዊ አገልግሎት ትስስር እንዲያገኙ ማድረግ፣**

ተግባር 1. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመቀናጀት ለ159,160 የአካባቢ ልማት እና ለ36,672 የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች የማኀበራዊ አገልግሎት ትስስር ይፈጠርላቸዋል፡፡

**ግብ 22. ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች የተጋለጡ እና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎችን ብዝሃነት/አካታችነትን እና አሳታፉነትን ማጎልበት፣**

ተግባር 1. በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ባልታቀፉ በ67 ከተማ አስተዳደሮች የተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ሥራዎች ተጠቃሚዎች መመልመያ መስፈርት በማዘጋጀት ከድህነት ወለል በታች ያሉ 33,500 ተጠቃሚዎችን የመለየትና ኑሯቸውን የማሻሻል ስራ ይሰራል፡፡

ተግባር 2. በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ባልታቀፉ 67 ከተማ አስተዳደሮች በጊዜያዊነት ለተጨማሪ ገቢ ማስገኛ የሚውል 134 ሄ/ር መሬት እንዲዘጋጅ በማድረግ 33,500 ተጠቃሚዎች በከተማ ግብርና እና ከከተማ ግብርና ውጭ ባሉ ገቢ ማስገኛ ስራዎች እንዲሰማሩ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ባልታቀፉ 67 ከተማ አስተዳደሮች በተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ሥራዎች የተሰማሩ ተጠቃሚዎችን የሚከታተልና የሚደግፍ ኮሚቴ ይደራጃል፡፡

**የትኩረት መስክ 6፡- ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት እና ተቋም ግንባታ**

**ግብ 23. በ8 ከተሞች ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሁሉን አቀፍ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የተገልጋዮችን ሰነዶች /ፋይል ወደ ዲጂታል መረጃ እንዲቀየሩ ማድረግ፣**

ተግባር 1. በ8 ከተሞች ወረቀት አልባ አሰራር ስርዓት (ኢ-ሰርቪስ) በመዘርጋት ሁሉም የከተማ አገልግሎቶች ከዘልማዳዊ አሠራር ወጥተው ወደ ዲጂታል አሠራር እንዲሸጋገሩ ይደረጋል፡፡ ለዚህም አስፈላጊ የሆኑ የአይሲቲ መሰረተ ልማቶች እና ሶፍትዌሮች እንዲሟሉ ይደረጋል፡፡

ተግባር 2. በ8 ከተሞች የደንበኛ ሰነዶች (የከተማ ነዋሪዎች የቤተሰብ ሁኔታና አድራሻ፣ የቤቶች ይዞታ እንዲሁም ሌሎች ወሳኝ የከተማ ነክ መረጃዎች) 100% ወደ ዲጂታል መረጃ እንዲቀየሩ ይደረጋል፡፡

ተግባር 3. በ8 ከተሞች ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሁሉን አቀፍ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት መረጃዎች በኔትዎርክ አማካኝነት በአስተዳደር ደረጃዎች እና በተቋማት መካከል እንዲተሳሰሩ ይደረጋል፡፡

**የባለብዙ-ዘርፍ ጉዳዮች እቅድ**

**ግብ 24. በዘርፉ እቅዶችና የህግ ማዕቀፎች የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮችን በማካተት 50 ከመቶ ሴቶች እና 70 ከመቶ ወጣቶች ከልማቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣**

ተግባር 1. በአካባቢ ልማት ስራዎች እንዲሁም በስራ እድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና የሴቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ድርሻ 50% የወጣቶች ተሳትፎና ተጠቃሚነት ድርሻ 70 ከመቶ ይደርሳል፡፡

ተግባር 2. በከተሞች የአመራር ግንባታና ስምሪት 50% ሴቶችና ወጣቶች እንዲሁም በትምህርትና ስልጠና 50% ሴቶች ድርሻ ይኖራቸዋል፡፡

ተግባር 3. በከተሞች የግንባታና መሠረተ ልማት ዲዛይኖች የአካል ጉዳተኞችንና የአረጋዊያንን ልዩ ፍላጎት ያሟሉ 100% እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

**የስራ እድል ፈጠራ እቅድ**

**ግብ 25. በከተሞች በሚከናወኑ የልማት ስራዎች ለ145,350 ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር የከተማ ሥራ አጥነትን መቀነስ፣**

ተግባር 1. በከተማ ልማት ዘርፍ (በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድና በአረንጓዴ ልማት፣ በቤት ልማት እና መሰረተ ልማት ግንባታ) ለ145,350 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የሥራ እድል ይፈጠራል፡፡

# ክፍል ሶስት

# የማስፈፀሚያ ስልቶች፣ ስጋቶች እና እሳቤዎች

## 3.1 ማስፈፀሚያ ስልቶች

1. **የከተሞች መልካም አስተዳደርና አከታተም፡-** በከተሞች የማዘጋጃ ቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥን ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ እንዲቻል በጥናት ላይ ተመስርቶ ተቋማዊ አደረጃጀት፣ የሰው ሀይል ስምሪት እና ተደራሽ የህግ ማዕቀፎች በአዲስ እንዲዘጋጁ እና እንዲሻሻሉ ማድረግ፤ የከተሞች ያልተማከለ ተቋማዊ አደረጃጀት እና አስተዳደርን ተግባራዊ ማድረግ፤ ከተሞች ሚናቸውን የሚመጥን እና የሚያጠናክር አደረጃጀትና የአገልግሎት ስታንዳርድ እንዲኖራቸው ማድረግ፤ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ፣ ተደራሽ፣ ግልጽ፣ ኃላፊነትና ተጠያቂነት ያለበት የአገልግሎት አሰጣጥ ሥርዓት መዘርጋት፤ በከተማ ልማት ስራዎች ላይ የህብረተሰቡ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና ውጤታማነት ባለው አኳኋን እንዲመራ የሚያስችል ሥርዓት በመዘርጋት የሕብረተሰቡን ተሳትፎ እና ባለቤትነት ማሳደግ፤ ለከተማ አመራሮችና ባለሙያዎች ተከታታይ የአቅም ግንባታ ስራዎችን ማከናወን ከከተሞች መልካም አስተዳደርና ፋይናንስ አኳያ የተመረጡ ማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

2. **ተደራሽ የቤት ልማትና አስተዳደር፡-** የነዋሪዎችን የቤት ፍላጎት በጥናት መለየት፤ የለመኖሪያ ቤቶች ተደራሽነትና በጥራት ተፈፃሚነት የተዘጋጁ የህግ ማዕቀፎችንና አሰራሮችን ችግር ፈች እንዲሆኑ ማድረግ፣ በተለያዩ አልሚዎች የሚቀርቡ ቤቶች ለእያናዳንዳቸው የሚመሩበት እና ለተጠቃሚ የሚተላለፉበት ህግ ማዘጋጀት፤ ለቤት ልማት የሚውል የቤት ልማት ፈንድ የሚመራበት እና ሌሎችም እንደ አስፈላጊነቱ የህግ ማእቀፍ ማዘጋጀት፣ አገልግሎት እየሰጡ ያሉና ከደረጃ በታች የሆኑ መኖሪያ ቤቶችን እድሳትና ጥገና ማድረግ እንዲሁም የተጎሳቆሉ የመኖሪያ ቤቶችን በመልሶ ማልማት መቀነስ፤ መኖሪያ ቤት በተመጣጣኝ ዋጋ በኪራይ የሚቀርበት አካሄድ መተግበር፣ ለዝቅተኛ ነዋሪዎች ቤት ልማት ፕሮግራም የሚውል ፈንድ ማፈላለግ፤ በከተሞች የተጠናከረ የቤት ልማት ፋይናንስ ትስስር እና ምንጭን በመፍጠር የቤት ልማት ስራዎች በተፋጠነ መንገድ እንዲከናወኑ ማድርግ፤ በከተሞች ውብ፣ የተቀናጁ እና ዘላቂ የመኖሪያ መንደሮች እንዲፈጠሩ ለማድረግ ከሚመለከታቸው ኢጋር አካላት በቅንጅት መስራት፤ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር ኩባንያዎችን በማሣተፍ የተሻሻሉ፣ ወጪ ቆጣቢ እና ፈጣን የግንባታ ዲዛይኖችና ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ፤ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የቤቶች አስተዳደርና መረጃ አያያዝ ስርዓት በመዘርጋት የቤቶችን መረጃ 100% በዘመናዊ መረጃ ቋት ማደራጀት፤ መንግስት የሚያስተዳድራቸው ቤቶችን ወቅቱን የጠበቀ የአከራይ ተከራይ ውል የማከናወን እና የቤት ኪራይ ዋጋ ለማሻሻል የሚያስችል የቤቶች ፍረጃ ስራ መስራት ከቤት ልማትና አስተዳደር አኳያ የተመረጡ ማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

3. **የተቀናጀ ምርታማና ዘላቂ የከተማ መሠረተ ልማት፡-** ለመሰረተ-ልማት ግንባታ የአካባቢንና ማህበረሰብ ደህንነት የሚያረጋግጥ ሰነድ እንዲዘጋጅ ማድረግ፤ በጂኦግራፊያዊ መረጃ (GIS) የታገዘ የመሠረተ-ልማት የሀብት ምዝገባና አመራር፣ ግንባታና ኮንትራት ማኔጅመንት ስርዓት እንዲሁም የካፒታል ኢንቨስትመንት ፕላን ማኔጅመንት ሥርዓት መዘርጋት፤ የመሠረተ-ልማት አውታር ባለቤትና ገንቢ ባለድርሻዎች በፕላን ላይ ተመስርተውና ተቀናጅተው እንዲሰሩ ማድረግ፤ እንዲሁም ክልል አቀፍ የውይይት መድረክ በማዘጀት በፕሮጀክት አፈጻፀምና አስተዳደር ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን በዝርዝር በመለየት ከባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት መፍትሔ እንዲያገኙ ማድረግ፤ የግል ሴክተሩ በሽርክና በመሠረተ ልማት ፋይናንስ አቅራቢነት፣

በግንባታ፣ ጥገና እና አስተዳደር እንዲሳተፍ የሚያበረታታ ስርዓት መዘርጋት ከመሠረተ ልማት አኳያ የተመረጡ ማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

4. **የከተማ ጽዳትና አረንጓዴ ልማት፡-** ሚዲያዎችን እና ሌሎች አማራጮችን በመጠቀም የህብረተሰቡን ግንዛቤና ተሳትፎ ማሳደግ፤ ቆሻሻን ከምንጩ የመቀነስ፣ መልሶ የመጠቀም እና የመልሶ ኡደት መርሆዎችን ተግባራዊ ማድረግ፤ ከተሞች ባላቸው ሚና መሠረት የቆሻሻ ማሰባሰቢያ፣ መለያ፣ ማጓጓዣ እና ማስወገጃ ጣቢያዎች እንዲኖራቸው ማድረግ፤ በከተሞች በጥናት ላይ የተመሰረተ የደረቅ ቆሻሻ ፋይናንስ ስርዓት መዘርጋት፤ በከተሞች አረንጓዴ መሰረተ-ልማት ስታንዳርድ መሰረት በእያንዳንዱ ከተማ ቢያንስ አንድ በመንግስት የሚለማ ችግኝ ጣቢያ እንዲኖር ማድረግ፤ በመዝናኛ ፓርኮችና መናፈሻዎች ላይ የእጽዋት እና የፋሲሊቲ (Green, Gray and Blue Components) ጥምርታ በስታንዳርዳቸው መሰረት እንዲሆኑ ማድረግ፤ የግል ሴክተሩ በሽርክና በአረንጓዴ መሠረተ ልማትና ቆሻሻ አስተዳደር በፋይናንስ አቅራቢነት፣ በግንባታ፣ በጥገና እና አስተዳደር እንዲሳተፉ የሚያበረታታ ስርዓት መዘርጋት ከጽዳትና አረንጓዴ ልማት አኳያ የተመረጡ ማስፈፀሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

5. **የከተማ ምግብ ዋስትና እና ሴፍቲኔት፡-** በምግብ ዋስትና እና ሴፍቲኔት ፕሮጀክት ባልታቀፉ ከተሞች የምግብ ዋስትና ትግበራውን የሚያስተባብር ተቋማዊ አደረጃጀትና የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፤ ከድህነት ወለል በታች ያሉ ዜጎች በተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ስራዎች የሚሰማሩባቸው አማራጮች በጥናት መለየት፤ በዘርፉ ስራዎች አጋርነትና ቅንጅታዊ አሰራር የሚጎለብትበትን እና በከተሞች የምግብ ዋስትና ፈንድ በማቋቋም የምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተደራሽ ማድረግ፤ በአካባቢ ልማት የተሰማሩ ተጠቃሚዎች በኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራም እንዲታቀፉ በማድረግ የራሳቸውን ስራ እንዲጀምሩ ማድረግ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ የዕቅደ ማስፈጸሚያ ስልቶች ናቸው፡፡

6. **በከተሞች ዘመናዊ የመረጃ ሥርዓት እና ተቋም መገንባት፡-** ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም አገልግሎት አሰጣጥን የማዘመን (ኢ-ገቨርናንስ) እና በሶፍትዌር የታገዘ ሁሉን አቀፍ የመረጃ ሥርዓት የመገንባት ስራ ይሠራል፡፡ ከዚህም አኳያ የከተማ ነዋሪ ህዝብ ቁጥርና የወሳኝ ኩነቶች መረጃ ስርዓት እና ዘመናዊ የቤት መረጃ አያያዝና አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋት የደንበኛ ሰነዶች 100% ወደ ዲጂታል መረጃ እንዲቀየሩ ይደረጋል፡፡ ሁሉም ከተሞች እርስ በእርሳቸውና ከክልል ጋር በመረጃ ኔትወርክ እንዲገናኙ ይደረጋል፡፡

7. **ቅንጅታዊ አሠራርን መከተል፡-** የከተማ ልማት ሥራዎች በባሕሪያቸው የበርካታ ዘርፎችችን ተሳትፎ እና ቅንጅት የሚጠይቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም ዕቅዱን ተግባረዊ ለማድረግ በሕጎች እና በግቦች እንዲሁም በአተገባበር ረገድ በዘርፎች መካከል የቅንጅታዊ አሠራር ሥርዓትን ማስፈን ያስፈልጋል፡፡ በተለይም መሬትን ከሚያስተዳድሩ ተቋማት፣ ከጸጥታና ደህንነት፣ ከፍትህ ተቋማት፣ ከገቢዎች፣ ከኦዲት፣ ከሥራ ዕድል ፈጠራ፣ ከወሳኝ ኩነቶች ወዘተ ተቋማት ጋር የሕጎች፣ የግቦች እና የአተገባበር መናበብ መፍጠርና በጋራ አብሮ መስራት ይህንንም በእቅድ መመለስ ያፈልጋል፡፡

## 3.2 ስጋቶችና ታሳቢዎች

### 3.2.1 ስጋቶች

- ✓ ክልላዊ ፖለቲካዊ ሁኔታው ያለመረጋጋት፤ በየደረጃው ያለው አመራር በዘመቻ ስራ መጠመድ እና መደበኛ ስራው ለባለሙያ በመተው ተገቢ አመራር የማጣት ስጋት ሊኖር ይችላል፡፡
- ✓ በወቅታዊ ሁኔታው ምክንያት የፈለግነውን የማስፈጸሚያ በጀት ያለማግኘት፣ በኑሮ ውድነቱ ምክንያት በጥሬ ገንዘብ የህብረተሰብ ተሳትፎ የጠበቅነውን ያህል ያለመሆን ስጋት ሊሆነብን ይችላል፡፡
- ✓ በ2017 በጀት ዓመት የአለም ባንክ በጀት አለመኖሩ እና መደበኛ በጀት የሚመለከተው አካል በወቅቱ ያለመልቀቅና ፕሮጀክቶች በፈለግነው ጊዜና ወቅት ጀምረን ያለመጨረስ እድሉ ሰፊ ሊሆን ይችላል፡፡

### 3.2.2 ታሳቢዎች

በእቅዱ የተቀመጡ ዓላማዎችንና ግቦችን ለማሳካት ተገቢነት ያላቸው ተግባራት እና ማስፈጸሚያ ስልቶች የተነደፉ ሲሆን ለዚህ እቅድ ዓላማና ግብ መሳካት አጋዥ የሚሆኑ ሌሎች መልካም አጋጣሚዎችም በታሳቢነት ተወስደዋል፡፡ ለአብነትም፡-

- ✓ ከተሜነት የቀጣዩ የዕድገት ማዕከል እንደሚሆን፣

- ✓ ብቃት ያለውና ሥራ ፈጣሪ የሰው ሃይል አቅርቦት እየሰፋ እንደሚሄድ፣
- ✓ ችግር ፈቺ ቴክኖሎጅ በስፋት፤ በጥራት እና በተመጣጣኝ ወጭ እንደሚቀርብ፤
- ✓ የገጠር-ከተማ ፍልሰት ጤናማ እንዲሆን በገጠርና በመካከለኛና አነስተኛ ከተሞች የሚሰራው ስራ በልዩ ትኩረት ተጠናክሮ እንደሚሠራ፣
- ✓ የከትመት ፍጥነታችን 5.4 በመቶ እንደሚሆን በዚህ ምጣኔም የይዞታ ቁጥርም እንዲሁም ከገጠር ማዕከላት ወደ ከተማነት የሚደረገው ሽግግር ከፍተኛ እንደሚሆን፣
- ✓ የመሬት አቅርቦት ወጭ ከማስመለስና ልማትን በቀጣይነት በፍትሃዊነት ከመምራት አንፃር የቻይናን ተሞክሮ ዝቅተኛ ወለል (ከ47 እስከ 79 በመቶ) በገበያ ዋጋ ማቅረብ ሲንነሳ የኛ ከተሞች የመሬት አቅርቦት በገበያ ዋጋ የሚተላለፍ ከ40 በመቶ ማነስ እንደለሌበት፤
- ✓ መካከለኛ ገቢ ከገቡ ሀገራት ከተሞች ምጣኔ ስንነሳ ከተሞቻችን ያላቸዉን ደረጃዉን ያልጠበቀ አከባቢ ከ 73 በመቶ ወደ 30 በመቶ ማዉረድ እንዳለባቸዉ፤ ከከተማ ፕላን መረጃ ስንነሳ ደግሞ መልሶ ከሚለማዉ ዉስጥ 10 በመቶ ብቻ ሙሉ በሙሉ አፍርሶ መገንባት እንደሚሆን፣
- ✓ የልማት አጋሮችና የህብረተሰቡ ተሳትፎ እያደገ እንደሚሄድ፣
- ✓ ቅንጅታዊ አሰራር እንደሚዳብርና የመረጃ ልውውጡም ወደ ዲጂታል ደረጃ እንደሚያድግ፣

# ክፍል አራት

# የአፈፃፀም ክትትልና ግምገማ ስርዓት

በየደረጃው ያሉ ተቋማትና የአመራር አካላት የዚህን ዕቅድ አፈጻጸም በየሩብ ዓመቱ እየተሸነሸነ በሚወርደው እቅድ መነሻነት ውጤትን የሚያመለክቱ የክትትልና ግምገማ ሥርዓት በመዘርጋት መከታተልና መደገፍ ይኖርባቸዋል፡፡ ለዚህም በዋናነት የሚከተሉት የክትትል መሣሪያዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## 4.1 የእቅድ አፈፃፀም ክትትል ስርዓት

### 4.1.1 መደበኛ የአፈፃፀም ሪፖርት ልውውጥ ማከናወን

በየደረጃው ካለው የዘርፉ መዋቅር (ከዞን መምሪያዎች፣ ከወረዳ ጽ/ቤቶችና ከከተሞች) እንዲሁም ከሌሎች በቅንጅት ከሚሰሩ ተቋማት ጋር የሚደረገው መደበኛ የአፈፃፀም ሪፖርት ልውውጥ በዕቅድ ዘመኑ ላይ የተቀመጡ ዋና ዋና ግቦችን መሠረት ያደረገ ሆኖ ውጤት ላይ ያተኮረ፣ የተቀመውን ግብ ከአፈጻጸሙ ጋር በማነጻጸር ምን ያህል እንደተሳካ፣ ካልተሳካም ለምን እንዳልተሳካ የሚገልጽ መሆን ይኖርበታል፡፡ ሌላው መደበኛ ሪፖርቱ በእቅድ አፈፃፀም ወቅት የታዩ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን፣ የነበሩ መልካም ተሞክሮዎችንና ቀጣይነታቸውን ለማረጋገጥና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ወደ ሌሎች ለማስተላለፍ መከናወን ያለባቸውን ስራዎች እንዲሁም በቀጣይ ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮችን ያመላከተ እንዲሆን ይይደረጋል፡፡ ከላይ በተገለጸው መሠረት የሚዘጋጀው መደበኛ የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በየደረጃው እየተገመገመ ለቀጣይ ግብዓት እንዲሆን በመደበኛነት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርስ ይደረጋል፡፡

### 4.1.2 የመስክ ክትትልና ድጋፍ ማከናወን

በዕቅድ ዘመኑ የተቀመጡትን ሥራዎች አፈጻጸም በቀጣይነት ለመከታተል የምንጠቀምበት ሌላው መንገድ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ነው፡፡ በመሆኑም በእቅድ የተያዙ ፕሮግራሞችን አፈጻጸም በተመለከተ በየደረጃው ባለ የዘርፉ መዋቅር አማካኝነት በመስክ በአካል ተገኝቶ መደበኛ የመስክ ክትትልና ድጋፍ ይደረጋል፡፡ በመስክ ክትትል ወቅት በየፕሮግራሞቹ ሥር የሚካሄዱ ፕሮጀክቶችን በመጎብኘት እና ስለአፈጻጸማቸው አግባብነት ካላቸው የዞንና የከተማ አስተዳደር አካላት ጋር አጠቃላይ ውይይት በማካሄድ እንዲሁም በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት፣ የጋራ መፍትሄ በማስቀመጥ ወደ ዕቅድ ተቀይረው በማካካሻነት የሚከናወኑ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

### 4.1.3 የእቅድ አፈፃፀም ግምገማ እና ግብረ-መልስ ስርዓት

#### 4.1.3.1 የአፈፃፀም ምዘናና ግብረ-መልስ ማከናወን

በዕቅድ የያዝናቸው ሥራዎች አፈጻጸም ከምንመዘንባቸው ዘዴዎች መካከል አንዱ ከተዋረድ ተቋማት ጋር በሚደረገው የግብ ክፍፍልና የዕቅድ ማናበብ መሰረት በዓመት 1 ጊዜ የሴክተር ተቋማትን እቅድ መሠረት አድርጎ በተዘጋጀ መመዘኛ መስፈርት መሰረት በዞኖችና በከተሞች በመገኘት የዕቅድ አፈፃፀም ምዘና ማከናወን ነው፡፡ የምዘናው ውጤት ሪፖርት ተዘጋጅቶና ውይይት ተደርጎበት ከጸደቀ በኋላ የዘርፉ አፈጻጸም በሚገመገምበት መደበኛ የአፈፃፀም ግምገማ መድረክ (የሴክተር ጉባኤ) ላይ ቀርቦ ውይይት ተደርጎበት ግብረ-መልስ ይሰጣል፡፡

#### 4.1.3.2 መደበኛ የአፈፃፀም ግምገማ መድረክ (የሴክተር ጉባኤ) ማካሄድ

በክልሉ ቢሮ፣ በተጠሪ ተቋማት፣ በከተሞች እና አጋር አካላት መካከል የሚካሄድ መደበኛ የአፈፃፀም ግምገማ መድረክ (የሴክተር ጉባኤ) አንዱ የዕቅድ አፈጻጸም የምንገመግምበት ዘዴ ሲሆን በቢሮው አመቻችነት የሚካሄድ የጋራ የምክክርና የአፈፃፀም ግምገማ መድረክ ነው፡፡ የጋራ መድረኩ በቢሮው ሥር የሚገኙ የከተማና መሰረተ ልማት ዘርፍ ተቋማት (ዞኖች እና ከተሞች) በዕቅድ አፈጻጸም ወቅት ያጋጠሟቸውን ችግሮች በተመለከተ መፍትሔ በጋራ ለማፈላለግ፣ የሚጠበቁ ድጋፎችን በተገቢው መንገድ መስጠታቸውን ለማረጋገጥ፣ ጉድለት በታየበት አካባቢ ለማጠናከር፣ ግብረ-መልስ ለመስጠት እና የተሻሉ ተሞክሮዎችን ለይቶ በማውጣት ለመማማር የሚቻልበት ነው፡፡

### 4.2 ማጠቃለያ

በዚህ እቅድ የተቀመጡ ዋና ዋና ግቦችን ለማሳካት በቀጣይ የልማት ምዕራፎች ከሚኖረው ሥራ ስፋትና ትኩረት አንጻርም አደረጃጀቱን የማጠናከር እና በቀጣይነትም አቅም የማሳደግ ሥራ እንደሚሠራ ይጠበቃል፡፡

የከተማን ፈጣን እድገት ሊመራ የሚችል የከተማ አመራር መፍጠር፣ የከተሞችን መ/አስተዳደር እና አቅም ግንባታ ሥራዎችን ማጠናከር፣ የከተሞች አረንጓዴ ልማት፣ ጸዳትና ውበት ሥራዎችን ማጠናከር፣ የከተማ ቤት ልማትና አስተዳደር ሥራዎችን ማጠናከር፣ የተቀናጀ የከተማ መሰረተ - ልማትና አቅርቦት ሥራዎችን ማሳደግ እንዲሁም የከተማ ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀምን ማሻሻል ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረትም የተቋም አቅም ግንባታ ሥራን አጠናክሮ በመስራት ለተልዕኮ ዝግጁ የሚያደርግ ቅድመ ሁኔታ አሟልቶ ወደ አፈጻጸም እንደሚገባ ታሳቢ ተደርጓል፡፡

## 4.3 የ2018 በጀት ዓመት ዕቅድ ድርጊት መርሃ ግብር

| የዕቅድ ኮድ | የተግባር ስም | የመለኪያ አሃድ | ክብደት | ዓመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **1** | **የተቋሙን የመፈፀምና የማስፈፀም አቅም ማጎልበት** | | **15** | | | | | |
| 1.1 | ፖሊሲና ስትራቴጅ | | 1.3 | | | | | |
| 1.1.1 | ስትራቴጅ ማዘጋጀት | በቁጥር | 0.2 | 1 | 1 | | | |
| 1.1.2 | አዋጅ ማዘጋጀት | በቁጥር | 0.2 | 1 | 1 | | | |
| 1.1.3 | ደንብ ማዘጋጀት | በቁጥር | 0.3 | 1 | | 1 | | |
| 1.1.4 | መመሪያ ማዘጋጀት | በቁጥር | 0.3 | 3 | | 1 | | 2 |
| 1.1.5 | ማንዋል ማዘጋጀት | በቁጥር | 0.3 | 1 | | | 1 | |
| 1.2 | የተቋማዊ አደረጃጀትና ሚና | | 1.5 | | | | | |
| 1.2.1 | ተቋሙ ከተጠሪ ተቋማት ጋር የሚኖረውን ግንኙነት ማጠናከር | በቁጥር | | | | | | |
| 1.2.2 | በተዋረድ ከፌደራል እስከ ቀበሌ ድርስ ያለውን ግንኙነት ማጠናከር | በቁጥር | 0.5 | 2 | | 1 | | 1 |
| 1.2.3 | ከክልል ተቋማት ጋር የጎንዮሽ ቅንጅታዊ አሰራርን ማጠናከር | በቁጥር | 0.5 | 2 | | 2 | | |
| 1.2.4 | ለግምገማና ኦዲት ስራ ከተደራጁ ተቋማት (የክላስተር አስተባባሪዎች፣ የፕላንና ልማት ቢሮ፣ የገንዘብ ቢሮ እና ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት) ጋር ያለውን ቅንጅታዊ አሰራር ማጠናከር | በቁጥር | 0.5 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.3 | ልዩ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች | | 0.8 | | | | | |
| 1.3.1 | በጦርነት የተጎዱ ቦታዎችን በጥናት በመመስረት መረጃወችን መሰብሰብና ለሚመለከተዉ አካል በወቅቱ ማድረስ ፣ | በቁጥር | 0.3 | 1 | | | | 1 |
| 1.3.2 | የከተማ ኮሪደር ልማትን የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት በወጥነት እንዲከናወን ማድረግ፣ | በ% | 0.5 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.4 | ክትትልና ግምገማ | | 2 | | | | | |
| 1.4.1 | ከአሻጋሪ ዕድገትና ዘላቂ የልማት ዕቅድ የተቀዳና የተዘጋጀ የዕቅድ ሰነድ ማዘጋጀት | በቁጥር | 0.2 | 1 | 1 | | | |
| 1.4.2 | ጥራቱን የጠበቀ የዕቅድ ሰነድ ማዘጋጀት | በ% | 0.2 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.4.3 | ወቅቱን የጠበቀ የሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት | በቁጥር | 0.3 | 5 | 1 | 1 | 1 | 2 |
| 1.4.4 | ጥራቱን የጠበቀ የሪፖርት ሰነድ ማዘጋጀት | በ% | 0.3 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.4.5 | ውጤታማ የመስክና የዴስክ ክትትልና ግምገማ ማካሄድ | በቁጥር | 0.2 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |

| የዕቅድ ኮድ | የተግባር ስም | የመለኪያ አሃድ | ክብደት | ዓመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.4.6 | ወቅቱን የጠበቀ የመስክና የዴስክ የክትትልና ግምገማ ግብረ-መልስ አዘጋጅቶ መላክ | በቁጥር | 0.3 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.4.7 | ከተጠሪ ተቋማት፣ ከዞኖች፣ ከከተማ አስተዳደር እና ከአጋር አካላት ጋር የዘርፉን እቅድ አፈጻጸም በጋራ መገምገም | በቁጥር | 0.3 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.4.8 | የክትትልና ድጋፍ ተግባሩን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ እንዲሆን ማድረግ | በ% | 0.2 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.5 | የአሻጋሪ እድገትና የዘላቂ ልማት እቅድ ተግባቦት | | 1 | | | | | |
| 1.5.1 | በመደበኛ ሚዲያ በመጠቀም እቅዱን ማስተዋወቅ | በቁጥር | 0.3 | 1 | 1 | | | |
| 1.5.2 | የገፅ ለገፅ መድረክ በመፍጠር እቅዱን ማስተዋወቅ | በቁጥር | 0.3 | 1 | 1 | | | |
| 1.5.3 | በዲጅታል ሚዲያ በመጠቀም እቅዱን ማስተዋወቅ | በቁጥር | 0.4 | 1 | 1 | | | |
| 1.6 | የተቋማዊ ሪፎርም ስራን ማሳለጥ | | 4.4 | | | | | |
| 1.6.1 | የፕሮግራም በጀት ትግበራን ውጤታማ ማድረግ | በቁጥር | | | | | | |
| 1.6.2 | የፋይናንስ አጠቃቀም ውጤታማነትን ለማሳደግ ሂሳቦችን በኮዳቸው በሌጀር እና IBEX በመመዝገብ የተደረገ ክትትል እና ሪፖርት | በቁጥር | 0.5 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 1.6.3 | በበጀት ዓመቱ የተመደበ ደመወዝና ስራ ማስኬጃ በጀት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል የተደረገ ክትትል፣ ወቅታዊ ምዝገባ እና የተዘጋጀ ሪፖርት | በቁጥር | 0.3 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 1.6.4 | በየወሩ የባንክ ሂሳብ ማስታረቅ እና ሪፖርት ማድረግ | በቁጥር | 0.2 | 12 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 1.6.5 | የፋይናንስ እና የህጋዊነት የገቢ፣ የወጪ፣ የዝውውር፣ የተሰብሳቢ፣ የተከፋይ የሂሳብ ምርመራ ማካሄድ | በቁጥር | 0.3 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.6.6 | ለሚቀርቡ የዲስፐሊን ክሶች ህጋዊ ማጣራት በማድረግ የተሰጠ እርምት | በ% | 0.3 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.6.7 | በደረጃ ዕድገት፣ በዝውውር፣ በቅጥር ወይም በምደባ የሰራተኞች ስምሪት በመፈጸም በሰው ሃይል የተሸፈኑ ክፍት የስራ መደቦች | በ% | 0.3 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.6.8 | ተለይቶና ተደራጅቶ የተያዘ በቢሮ ደረጃ በበጀት አመት ውስጥ የሚወገዱና የተወገዱ ንብረቶች | በቁጥር | 0.3 | 1 | | | | 1 |
| 1.6.9 | ነቀፌታ ያለበትን የኦዲት ግኝት መቀነስና የተገኘውን ግኝት ማስመለስ | በ% | 0.4 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |

| የዕቅድ ኮድ | የተግባር ስም | የመለኪያ አሃድ | ክብደት | ዓመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1.6.10 | በውጭ ኦዲት የተገኘ ግኝትን ማስመለስ የተደረገ አስተዳደራዊ ማስተካከያ | በ% | 0.4 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.6.11 | የተቋሙን አገልግሎት አሰጣጥ በዳሰሳ ጥናት በመለየት የደንበኞችን እርካታ ማሻሻል | በቁጥር | 0.3 | 1 | | | | 1 |
| 1.6.12 | በተቋሙ ሶፍትዌሮችን ከኢኖቬሽንና ቴክኖሎጅ ቢሮ ጋር በመተባበር ማልማትና በተዋረድ ለሚገኙ ተቋማት አውቶሜት ማድረግ | በቁጥር | 0.3 | 4 | | 1 | 1 | 2 |
| 1.6.13 | ለተቋም አቅም ግንባታ በሀገር ውስጥ አጋርነት የተገኘ ድጋፍ | በብር | 0.6 | 2,000,000 | | | 1,000,000 | 1,000,000 |
| 1.6.14 | ለተቋም አቅም ግንባታ በውጭ ሀገር አጋርነት የተገኘ ድጋፍ | በብር | | | | | | |
| 1.6.15 | ለቢሮ ሰራተኞችና ተገልጋዮች ምቹ የስራ አካባቢ መፍጠር እና ኤርጎኖሚክስን ተግባራዊ ማድረግ | በ% | 0.2 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 1.7 | በተቋሙ የታቀዱ ተግባራትን በህዝብ ግንኙነት ንቅናቄ በማጅብ ተፈፃሚነታቸውን ማሳደግ | | 4 | | | | | |
| 1.7.1 | ተዘጋጅተው ለህብረተሰቡ ተደረሽ የተደረጉ ዜናዎች | በቁጥር | 0.4 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.7.2 | ማህበራዊ ሚዲያ (ፌስቡክ፤ ቴሌግራም፤ ዋትስአፕ እና በሌሎችም) ለህብረተሰቡ የሚተላለፉ ዜናዎች | በቁጥር | 0.5 | 40 | 10 | 10 | 10 | 10 |
| 1.7.3 | የቢሮው የማህበራዊ ሚዲያ ተከታይ ቁጥር ማሳደግ | በቁጥር | 0.3 | 17,000 | | | | 17,000 |
| 1.7.4 | መድረኮች በውጤታማነት እንዲካሄዱ ከሚመለከተው አካል ጋር በቅርበት መስራት | በቁጥር | 0.6 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.7.5 | የተዘጋጀ ዶክመንታሪ ፊልም | በቁጥር | 0.6 | 1 | | | | 1 |
| 1.7.6 | የመረጃ ተደራሽነትን ለማሳደግ በተቋሙ የተለያዩ ስብሰባዎችና ወርክሾፕ በመገኘት የተያዙ እና የተደራጀ መረጃዎች | በቁጥር | 0.6 | 4 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 1.7.7 | በቢሮው በልዩ ልዩ ወቅታዊ ኩነቶች ላይ ያተኮሩ መጠይቆችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት በተቋሙ ተገልጋዮች የሚኖረዉን አስተያየት በመሰብሰብና በመተንተን ትቅም ላይ የዋለ መረጃ | በቁጥር | 0.5 | 1 | | | | 1 |
| 1.7.8 | የተቋሙ የተቀመሩ ተሞክሮዎችን ማስፋት | በቁጥር | 0.5 | 1 | | | | 1 |
| **2** | **በክልሉ የተመጣጠነ አከታተም ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ፣** | | **3** | | | | | |
| 2.1 | በክልሉ የተመጣጠነ አከታተም ሥርዓት እንዲኖር በማድረግ የከትመት ምጣኔን በ2017 ካለበት 22.77 በመቶ በ2018 ወደ 23.45 በመቶ ማሳደግ፤ | | 3 | | | | | |

| የዕቅድ ኮድ | የተግባር ስም | የመለኪያ አሃድ | ክብደት | ዓመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2.1.1 | በክልሉ ከሚገኙ 729 ነባር ከተሞች መካከል በአቅራቢያቸው ወዳለ ትልቅ ከተማ ሊዋሀዱ የሚችሉ ከተሞችን በጥናት በመለየት እንዲዋሀዱ ማድረግ፣ | በቁጥር | 1 | 10 | | | | 10 |
| 2.1.2 | በጥናት ላይ ተመስርቶ የከተማነት መስፈትቱን የሚያሟሉ የገጠር የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት የከተማነት እውቅና እንዲያገኙ ማስቻል፣ | በቁጥር | 1 | 10 | | | | 10 |
| 2.1.3 | ከተሞችን በፈርጅ የማደራጀት ስርዓቱን በማጠናከር 5 ከተሞች ወደ ከተማ አስተዳደር፣ 9 ከተሞች ወደ መሪ ማዘጋጃ እና 19 ከተሞች ወደ ንዑስ ማዘጋጃ የፈርጅ ለውጥ እንዲያገኙ ማድረግ፣ | በቁጥር | 1 | 33 | | | | 33 |
| **3** | **የከተማ መልካም አስተዳደርና አገልግሎት አሰጣጥን ማሻሻል** | | **13.5** | | | | | |
| 3.1 | በ729 ከተሞች ዘመናዊ ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሁሉን አቀፍ የመረጃ ሥርዓት በመዘርጋት የተገልጋዮችን ሰነዶች/ፋይል ወደ ዲጂታል መረጃ እንዲቀየሩ ማድረግ፤ | | 1 | | | | | |
| 3.1.1 | በ8 ከተሞች ወረቀት አልባ አሰራር ስርዓት (ኢ-ሰርቪስ) በመዘርጋት ሁሉም የከተማ አገልግሎቶች ወደ ዲጂታል አሠራር እንዲሸጋገሩ ማድረግ፣ | በ% | 1 | 100 | 100 | 100 | 100 | 100 |
| 3.2 | የከተሞች መልካም አስተዳደርና ፋይናንስ | | 6 | | | | | |
| 3.2.1 | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት ስታንዳርድ ተግባራዊ ያደረጉ ከተሞች | በቁጥር | 1.5 | 94 | | | | 94 |
| 3.2.2 | በጽዳትና ዉበት አገልግሎት ብቃታቸው በምዘና ተረጋግጦ ወደ ሥራ የተሠማሩ ባለሙያዎች | በቁጥር | 1.5 | 2,000 | | | 1,000 | 1,000 |
| 3.2.3 | ከተሞች ደረጃውን የጠበቀ የቄራ አገልግሎት፣ የእሣት አደጋ መከላከልና መቆጣጠር፣ የዘላቂ ማረፊያ እንዲሁም የገበያ ቦታና የንግድ ቤቶች አገልግሎት በዘመናዊ መንገድ የሚሰጥባቸው ከተሞች ብዛት | በቁጥር | 1.5 | 94 | | | | 94 |
| 3.2.4 | የማዘጋጃቤታዊ አገልግሎት አሰጣጥ አፈፃፀም ምዘና የተካሄደባቸው ከተሞች ብዛት | በቁጥር | 1.5 | 10 | | | 8 | 2 |
| 3.3 | ከተሞች ለመሰረተ-ልማትና አገልግሎት አቅርቦት የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በራሳቸው የመሸፈን አቅም ማሳደግ፤ | | 6.5 | | | | | |
| 3.3.1 | በ752 ከተሞች በህብረተሰቡና በመንግስት በጋራ በሚከናወኑ የአካባቢ ልማት ስራዎች ላይ የህብረተሰብ ተሳትፎ ምጣኔው 52 በመቶ እንዲደርስ ማድረግ፣ | በ% | 0.5 | 52 | 52 | 52 | 52 | 52 |

| የዕቅድ ኮድ | የተግባር ስም | የመለኪያ አሃድ | ክብደት | ዓመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 3.3.2 | ለክልሉ ከተሞች የልማት ፋይናንስ የአሰራር ማሻሻያ ግብአት የሚሆን የጥናት ሰነድ ማዘጋጀት፡፡ | በቁጥር | 2 | 1 | | | 1 | |
| 3.3.3 | ያልተማከለ የፋይናንስ ስርአት በመዘርጋት ማዘጋጃቤት ያላቸው ከተሞች ከወጪያቸው 50 በመቶ በራሳቸው ገቢ መሸፈናቸውን ማረጋገጥ፤ | በ% | 1 | 50 | 50 | 50 | 50 | 50 |
| 3.3.4 | የተመረጡ የክልሉ ከተሞች ከሌላ ሀገር ከተሞች ጋር እህትማማች እንዲፈጥሩ እና የልማት አቅማቸዉ እንዲጎለብት ማድረግ፡፡ | በቁጥር | 3 | 5 | | | | 5 |
| **4** | **የከተሞች ሴፍቲኔትና ምግብ ዋስት** | | **15** | | | | | |
| 4.1 | የከተማ ሴፍትኔትን በማስፋፋት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ | | 15 | | | | | |
| 4.1.1 | የምግብ ዋስትና ስርዓት የተስፋፋባቸው ከተሞችን ማስቀጠል | በቁጥር | 1.5 | 18 | | | | 18 |
| 4.1.2 | በምግብ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ የሆኑ ለምግብ ዋስትና ተጋላጭ የሆኑ ዜጎች ብዛት | በቁጥር | 1.5 | 195,832 | | | | 195,832 |
| 4.1.3 | የከተሞች ሴፍቲኔትና የሥራ ፕሮጀክት ተጠቃሚ ከተሞች ግንዛቤ የተፈጠረለት ህብረተሰብ ብዛት | በቁጥር | 1.5 | 540,507 | 540,507 | | | |
| 4.1.4 | በፕሮግራሙ ተጠቃሚ የሆኑ ልዩ ድጋፍ ለሚሹ የህብረተሰብ ክፍሎች \|(ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚ) | በቁጥር | 1.5 | 36,672 | | | | 36,672 |
| 4.1.5 | በአካባቢ ልማት ስራዎች የተሠማሩ ተጠቃሚዎች | በቁጥር | 2 | 159,160 | | | | 159,160 |
| 4.1.6 | ከከተማ ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ወደ ዘላቂ ኑሮ ለመሸጋገር የተቆጠበ ገንዘብ መጠን million birr | በብር | 2 | 169.84 | 42.46 | 42.46 | 42.46 | 42.46 |
| 4.1.7 | ከፕሮግራሙ የተመረቁና በግል የስራ ዕድል የተፈጠረላቸው ተጠቃሚዎች | በቁጥር | | | | | | |
| 4.1.8 | የማህበራዊ አገልግሎት ትስስር የተፈጠረላቸው የቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች ብዛት | በቁጥር | 1.5 | 36,672 | | | | 36,672 |
| 4.1.9 | በተጨማሪ ገቢ ማስገኛ ስራዎች የተሰማሩ ተጠቃሚዎች ብዛት | በቁጥር | 2 | 51,125 | | | | 51,125 |
| 4.1.10 | ለተጨማሪ ገቢ ማስገኛ የዋለ መሬት በሄ/ር | በሄክታር | 1.5 | 134 | | | | 134 |
| **5** | **የከተሞች ፅዳትና የአረንጓዴ ልማት አገልግሎትን ማሻሻልና ማሳደግ** | | **16** | | | | | |
| 5.1 | የከተሞችን የጽዳትና የአረንጓዴ ልማት ስራ በማሻሻል ከተሞች ለኑሮ ምቹ እንዲሆኑ ለማድረግ የደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ሽፋንን ማሳደግ፤ | | 15 | | | | | |

| የዕቅድ ኮድ | የተግባር ስም | የመለኪያ አሃድ | ክብደት | ዓመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5.1.1 | በጽዳትና አረንጓዴ ልማት ስራ ላይ በቀጥታ የተሳተፈ የከተማ ነዋሪ ብዛት | በቁጥር | 1 | 1 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 0.25 |
| 5.1.2 | ወርሃዊ የጽዳት ቀን ወስነው የተገበሩ ከተሞች | በቁጥር | 1 | 728 | | | | 728 |
| 5.1.3 | የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተሰራላቸው አረንጓዴ ቦታዎች ብዛት | በቁጥር | 2.5 | 1,000 | 250 | 250 | 250 | 250 |
| 5.1.4 | የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብና አወጋገድ ፋይንንስ ስርዓት የዘረጉ ከተሞች | በቁጥር | 1.5 | 15 | | 5 | 5 | 5 |
| 5.1.5 | በአዲስ የለሙ ችግኝ ጣቢያዎች ብዛት | በቁጥር | 1 | 20 | | | 10 | 10 |
| 5.1.6 | በከተሞች በስታንዳርድ ዲዛይን የለሙ አዲስ አረንጓዴ ፓርኮች ብዛት | በቁጥር | 1.5 | 85 | 10 | 30 | 30 | 15 |
| 5.1.7 | በፕላን ላይ ከተቀመጠው የመሬት ድርሻ (30:30:40) የአረንጓዴ መሰረተ ልማት ሽፋን | በ% | 1 | 30 | | | | 30 |
| 5.1.8 | በፕላን ላይ ከተመላከቱ አረንጓዴ ቦታዎች በስታንዳርድ ዲዛይን ያለሙ ከተሞች | በቁጥር | 1.5 | 200 | | | | 200 |
| 5.1.9 | ከመነጨው ቆሻሻ በአግባቡ የተወገደ ቆሻሻ መጠን | በሜትር ኩብ | 1.5 | 1 | 0.25 | 0.25 | 0.25 | 0.25 |
| 5.1.10 | ደረቅ ቆሻሻ የሚያስወግዱ አዲስ ማህበራትን በማደራጀት ቆሻሻን በአግባቡ ያስወገዱ ከተሞች | በቁጥር | 1.5 | 30 | 5 | 10 | 10 | 5 |
| 5.1.11 | እንክብካቤ የተደረገላቸው ነባር አረንጓዴ ቦታዎች | በሄክታር | 1 | 5,000 | | | | 5,000 |
| 5.1.12 | በከተሞች የተገነባ ጊዜያዊ የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ | በቁጥር | 1 | 10 | | | | 10 |
| **6** | **ተደራሽ የቤት ልማትና አስተዳደር** | | **13.5** | | | | | |
| 6.1 | የቤቶች ልማት ስራዎችን ማሻሻል | | 5.5 | | | | | |
| 6.1.1 | በሪል ስቴት የተገነቡ ቤቶች | በቁጥር | 1 | 5,946 | 892 | 2,081 | 2,081 | 892 |
| 6.1.2 | በመኖሪያ ቤት ህ/ስ/ማህበራት የተገነቡ ቤቶች | በቁጥር | 1 | 63,671 | 9,551 | 22,285 | 22,285 | 9,550 |
| 6.1.3 | በግሉ ዘርፍ የተገነቡ የከተማ ቤቶች | በቁጥር | 0.5 | 21,558 | 3,234 | 7,545 | 7,545 | 3,234 |
| 6.1.4 | ለዝቅተኛ ነዋሪዎች የተገነቡ የከተማ ቤቶች | በቁጥር | 1 | 1,500 | 375 | 375 | 375 | 375 |
| 6.1.5 | አዲስ የሪል ስቴት አልሚዎች | በቁጥር | 1 | 18 | | | | 18 |
| 6.1.6 | የቤት ልማት ያጠናቀቁ ነባር የሪል ስተቴት አልሚዎች | በቁጥር | 1 | 17 | | | | 17 |
| 6.2 | የቤቶች አስተዳደር ስራዎችን ማሻሻል | | 8 | | | | | |
| 6.2.1 | በዘመናዊ መረጃ ቋት የተደራጁ የመንግስት ቤቶች | በቁጥር | 1 | 20,879 | 3,132 | 7,308 | 7,308 | 3,131 |
| 6.2.2 | በዘመናዊ መረጃ ቋት የተደራጁ የኮንደምንየም ቤቶች | በቁጥር | 1 | 20,093 | 3,014 | 7,033 | 7,033 | 3,013 |
| 6.2.3 | በዘመናዊ መረጃ ቋት የተደራጁ የግለሰብ ቤቶች | በቁጥር | 1 | 59,028 | 8,854 | 20,660 | 20,660 | 8,854 |

| የዕቅድ ኮድ | የተግባር ስም | የመለኪያ አሃድ | ክብደት | ዓመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6.2.4 | የውል እድሳት የተደረገላቸው ቤቶች | በቁጥር | 1 | 56,292 | 8,444 | 19,702 | 19,702 | 8,444 |
| 6.2.5 | የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ የተዘጋጀላቸው የመንግስት ቤቶች | በቁጥር | 1 | 3,000 | 450 | 1,050 | 1,050 | 450 |
| 6.2.6 | የኪራይ ዋጋቸው የተሻሻለ የመንግስት ቤቶች | በቁጥር | 1 | 5,000 | 750 | 1,750 | 1,750 | 750 |
| 6.2.7 | ያላግባብ የተያዙ ቤቶችን ተነጥቀው ለአዲስ ተከራዮች የተላለፉ የመንግስት ቤቶች | በቁጥር | 1 | 1,200 | 180 | 420 | 420 | 180 |
| 6.2.8 | ጥገና እና ዕድሳት የተደረገላቸው የመንግስት ቤቶች | በቁጥር | 1 | 1,200 | 180 | 420 | 420 | 180 |
| **7** | **የተቀናጀ ምርታማና ዘላቂ የከተማ መሠረተ ልማትን ማስፋፋት** | | **24** | | | | | |
| 7.1 | ጥራቱን የጠበቀ ለረዥም ዘመን አገልግሎት የሚሰጥ የከተማ መሠረተ ልማትን በማስፋፋት | | 24 | | | | | |
| 7.1.1 | በከተሞች የተገነባ ኮብል ስቶን መንገድ | ኪሎ ሜትር | 1.5 | 123 | 2 | 2 | 24 | 95 |
| 7.1.2 | በከተሞች የተገነባ ጠጠር መንገድ | ኪሎ ሜትር | 1.5 | 714 | 43 | 143 | 171 | 357 |
| 7.1.3 | በከተሞች የተገነባ ጥርጊያ መንገድ | ኪሎ ሜትር | 1.5 | 1,000 | 60 | 200 | 240 | 500 |
| 7.1.4 | በከተሞች የተገነባ የአስፓልት መንገድ | ኪሎ ሜትር | 1.5 | 17 | 1 | 3 | 5 | 8 |
| 7.1.5 | በከተሞች የተገነባ ደረጃውን የጠበቀ ጎርፍ ማስወገጃ እና መከላከያ ግንብ | ኪሎ ሜትር | 1 | 199 | 11 | 40 | 48 | 100 |
| 7.1.6 | በከተሞች የተገነባ ደረጃውን የጠበቀ ከፍተኛና መለስተኛ ድልድይ | በቁጥር | 1 | 18 | 5 | 2 | 5 | 6 |
| 7.1.7 | በከተሞች የተገነባ ደረጃውን የጠበቀ ስላብ ከልቨርት | በቁጥር | 1 | 143 | 50 | 30 | 30 | 33 |
| 7.1.8 | በከተሞች የተዘረጋ የመጠጥ ውሃ መስመር | ኪሎ ሜትር | 1 | 673 | 60 | 115 | 162 | 336 |
| 7.1.9 | በከተሞች ለአረንጓዴ ልማት የተዘረጋ የውሃ መስመር | ኪሎ ሜትር | 1 | 200 | 12 | 40 | 48 | 100 |
| 7.1.10 | በከተሞች የተገነባ የውሃ ቦኖ | በቁጥር | 1 | 162 | 10 | 16 | 33 | 103 |
| 7.1.11 | የተዘረጋ የመንገድ መብራት መስመር | ኪሎ ሜትር | 1 | 458 | 60 | 92 | 110 | 196 |
| 7.1.13 | የተገነባ የጋራ መፀዳጃ ቤት | በቁጥር | 1 | 128 | 20 | 20 | 20 | 68 |
| 7.1.14 | የተገነቡ የገበያ ማዕከላት | በቁጥር | 1 | 15 | 3 | 3 | 3 | 6 |
| 7.1.15 | የተገነባ ደረጃውን የጠበቀ የመስሪያና መሸጫ ሸድ | በቁጥር | 1 | 2,032 | 20 | 203 | 480 | 1,329 |
| 7.1.16 | የተጠገነ የጌጠኛ ድንጋይ መንገድ | ኪሎ ሜትር | 1 | 8 | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 7.1.17 | የተጠገነ የጠጠር መንገድ | ኪሎ ሜትር | 1 | 504 | 30 | 100 | 122 | 252 |
| 7.1.18 | የተጠገነ የአስፋልት መንገድ | ኪሎ ሜትር | 1 | 2 | 1 | 1 | 1 | 1 |
| 7.1.19 | ስማርት ሲቲን ተግባራዊ ለማድረግ ምቹ ሁኔታ የፈጠሩ ከተሞች | በቁጥር | 1 | 8 | | | | 8 |
| 7.1.20 | የኮሪደር ልማት በስፋት የቀጠለባቸው ከተሞች ብዛት | በቁጥር | 1 | 8 | | | | 8 |

| የዕቅድ ኮድ | የተግባር ስም | የመለኪያ አሃድ | ክብደት | ዓመታዊ ዕቅድ | 1ኛ ሩብ | 2ኛ ሩብ | 3ኛ ሩብ | 4ኛ ሩብ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 7.1.21 | ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮ የተገነቡ ደረጃቸውን የጠበቁ የወጣት ማዕከላት ብዛት | በቁጥር | 1 | 15 | | 1 | 4 | 10 |
| 7.1.22 | የተገነቡ የመሰረተ ልማት አውታሮችን መዝግበውና አደራጅተው የያዙ ከተሞች ብዛት | በቁጥር | 1 | 85 | | | | 85 |
| 7.1.23 | ተመዝግበው ተያዙ የመሰረተ ልማት አይነቶች ብዛት | በቁጥር | 1 | 18 | | | | 18 |
| | **ጠቅላላ** | | **100** | | | | | |